# የወጣቶች

# አገልግሎት

# አስተዋጽኦዎች



## የሚሲዮን አገልግሎት
ከበድ ሪዲ

**ጭብጥ፡** ወጣቶችን ጨምሮ አማኞች ሁሉ በቤተክርስቲያን የሚሲዮን አገልግሎት ውስጥ መሳተፍ አለባቸው።
**አመቺ ጊዜ፡** ይህ የወጣቶች አገልግሎት አስተዋጽኦ በየትኛውም የሰንበት ምሽት ላይ ሊካሄድ ይችላል። በተጨማሪም፣ በመደበኛ ነት የታቀደ የሚሲዮን አገልግሎት ክፍል አድርጎ መጠቀም ይቻላል።

**ዝግጅት**

1. ከአያሌ ሳምንታት አስቀድመህ ለአገልግሎቱ ጊዜ ወስን። ወጣቶች የመዝሙር፣ የድራማና ሌሎች የፕሮግራም ኃላፊነቶቻቸውን ለመለማመድ የሚበቃቸውን ጊዜ በመስጠት ዝግጅቶችን አጠናቅቅ።
2. ስለ አገልግሎቱ ማስታወቂያ ተናገር።
3. ከአገልግሎቱ በፊት ቢያንስ አንድ ጊዜ ከሁሉም ወጣቶች ጋር በመገናኘት፣ ጠቅላላውን ፕሮግራም (መዝሙሮች፣ ድራማና የመጽሐፍ ቅዱስ ንባቦች) በልምምድ መልክ አካሂድ።
4. ይህንን ጊዜ ጠቃሚ የወጣቶች የአምልኮ አገልግሎት ለማካሄድ የምትችለውን ሁሉ ካደረግህ በኋላ፣ የአገልግሎቱ ተካፋዮች የሆኑት ወጣቶችና የተቀሩት የቤተክርስቲያኒቱ ተሳታፊዎች ልዩ የአምልኮ ጊዜ እንዲያሳልፉ ጸልይ።

**አስተዋጽኦ**
የአቀባበል ሰላምታና ጸሎት - የወጣቶች የአምልኮ መሪ
መዝሙር፡ «እንደተቀበልሁት ምህረት» የተስፋዬ ጋቢሶ ወይም ሌላ ስለ ሚሲዮን አገልግሎት የሚናገር መዝሙር።
ልዩ መዝሙር፡ በወጣቶች ቡድን የሚቀርብ ስለ ሚሲዮን አገልግሎት የሚናገር መዝሙር።
ድራማ፡ «የዮናስ ታሪክ» ከማርታ ቦልተን
(የሚከተለው መነባነብ ከወጣቶች አንዱ በቃሉ አጥንቶ የሚያቀርበው ይሆናል።)

ገጸባሕርይ፡ ዮናስ
(በንግሥ ሆድ ውስጥ የሚካሄድ (ምናባዊ) ትዕይንት።)

(እጆቹን ከአፉ ላይ አድርጎ) ሄይ! ትሰሙኛላችሁ? ሄሎ!... እዚህ አካባቢ ሰው አለ?
(በተበሳጨ ስሜት) አ፣ ምንም ዋጋ የለውም! እዚህ አካባቢ ምንም ሰው የለም:: ቢሰሙኝ እንኳዋን ዓሣው ነው የሚጮኸው ብለው ሊያስቡ ይችላሉ... የዓሣን ጥሪ ደግሞ ማን ይሰማል???
(ምናባዊ አካባቢውን እየተመለከተ) አ! ምን ዓይነት ችግር ነው! ይኼ ፍጥረት ምግቡን እንኳዋን ሳያላምጥ ነው እንዴ የሚውጠው!... እንዴት ይገማል! በዚህ ዓይነት ብቻውን መጓዙ አያስደንቅም::
(አሁንም አካባቢውን ከቃኘ በኋላ፣ አንድ አዲስ ነገር እንዳየ ሁሉ ፈጠን ብሎ) አሃ! ልክ እንዳሰብሁት! ይህ ሰውዬ ሼልፊሽ በልቷል! ይኸው እየሸተተኝ... አሁን ሆዴ እንደ አንዳንድ ቀኑ ምን ዓይነት ስሜት እንደሚሰማው አውቃለሁ!
(በምሬት ወደላይ ያያል::) አ! አይሆንም! እንደገና! (ወደታች ለመጠጋት እየሞከረ) ይኼ ሰውዬ ከመብላት ሌላ አያውቅም እንዴ? (እጆቹን ከአፉ ላይ ጭኖ) ወዳጄ... እዚህ ትርፍ ቦታ የለም! (እግሩን ለማንሣት ቢሞክር አልነቃነቅ ይለዋል) ኡፍፍፍ! ግግ!... እናትህ ግግህን መዋጥ እንደሌለብህ ነግራህ አታውቅም? (በብዙ ጥረት እግሮቹን ይዘረጋል) እስኪ፣ ከዚህ የምወጣበትን መንገድ ሳቅድ:: (ያቅዳል) እምምም... እስኪ... ከጥርሶቹ ላይ ልደንስ እችላለሁ:: ይኼ ግን የሚያዋጣ አይመስልም:: (እንደገና ለአፍታ ያስባል) እንደገና አፉን እስኪከፍት ጠብቄ እየዋኘሁ ብሄድስ? (ስለዚሁ ጉዳይ ትንሽ ያስባል) አይ፣ ይኼ እንኳዋ አይሆንም:: ይኼ ሰውዬ የሚጠጣው ውኃ ሊያሰምጠኝ ይችላል!... አራት መቶ ወይም አምስት መቶ ጊዜ በመዝለል ሆዱን ላሳምም የምችል ይመስለኛል... ግን አሁን ባለሁበት ሁኔታ የሱን መታመም የምፈልግ አይመስለኝም::
(ተስፋ በመቁረጥ) እውነታውን መጋፈጥ ሳይኖርብኝ አይቀርም:: እዚሁ ታስሬአለሁ:: በተጨማሪም፣ የምገባኝን እየተቀበልሁ ነኝ:: ለነገሩ ከጌታ እየኮበለልሁ አልነበር? (ወደ ላይ እየተመለከተ) ግንክ ነኔዌን ያን ያህል እንደምትወዳት አላውቅም ነበር!... የምልህ፣... በኃጢአት የተበላሸች ከተማ ነች! የውዳቂዎች ክምችት! ለነዚህ ሰዎች ለምን ጊዜህን ታባክናለህ? በፍጹም ከኃጢአታቸው ንስሐ ሊገቡ አይችሉም:: መቼም ሊለወጡ አይችሉም! (እግዚአብሔር የሚመልስለት ይመስል ዝም ብሎ) አዎ፣ ጌታ ሆይ፣ ኃጢአቶቼን ሁሉ የተናዘዝሁ ይመስለኛል:: ግን... (ሌላ ዝምታ) አዎ... መቼም የተለወጥሁ ይመስለኛል:: ግን ጌታ ሆይ፣ የነነዌ ሰዎች የተለዩ ናቸው! ኃጢአታቸው አስከፊ ነው፣ ጌታ ሆይ:: (አሁንም ለአፍታ ዝም ይልና) አዎ፣ መቼም ኃጢአት ኃጢአት መሆኑን አውቃለሁ:: ግን... (ዝምታ) የኃጢአት ትንሽ የለውም፣ ግን... (ምንም ቃል ሳይናገር እየተቅበጠበጠ) አዎ፣ ይኸውልህ... ይኼ መቼም የትም አያደርሰንም:: ስለዚህ... እንደሚመስለኝ እኔ ወደ ግብጽ ብሄድ



ሳይሻል አይቀርም:: በዚያም ታላላቅ የድንኳዋን ጉባኤዎችን፣ ጀማ ጉባኤዎችን፣ ሪቫይቫሎችን፣ የክረምት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን... የምትፈልገውን ሁሉ አደርጋለሁ:: በነነዌ ምትክ ይህንን ሁሉ ባደርግ አይበቃም? (ዝምታ) አይሆንም? ትልቅ የወጣቶች ስብሰባ ባደርግስ? አንድ ባዶ አዳራሽ እንከራይና ስብሰባውን እናካሂዳለን:: መቼም ይኼ ነነዌን ያስረሳሃል! (ዝምታ) አሁንም አይሆንም ነው የምትለኝ? ኡፎይ! አንድን ነገር ለማድረግ ስታቅድ ዝንፍ አትል!
እሺ፣ ነነዌ ለአንተ ለምን ይህን ያህል ልዩ እንደሆነች ንገረኝ:: ባለማቋረጥ ገፍተውሃል:: ከቃልህ የትኛውንም አይፈልጉም:: ታዲያ ለምን ዝም ብለህ አትረሳቸውም:: (ለአፍታ ዝም ካለ በኋላ እየተቁነጠነጠ መናገሩን ይቀጥላል) እንዴት ልትወዳቸው ትችላለህ?
(ወደ ላይ ከተመለከተ በኋላ) አ፣ አይሆንም! (እየተማረረ) አሁንም ሲበላ ነው:: ይኼ ሰውዬ ግብግ ቤት ውስጥ ያለ ይመስለዋል እንዴ?
(በዝምታ ተውጦ) እፎይ! ይሄ ለጥቂት ጊዜ ያህል እንደሚያቆየው ተስፋ አደርጋለሁ!
የት ላይ ነበርን?... አዎ፣ ነነዌ፣ እመነኝ፣ ለነሱ ይኼን ሁሉ መቸገር አያስፈልግም!
(ዝምታ) ለዚህ ነው አይደል? አሳብህን አትቀይርም ማለት ነው? ነነዌን ትወዳታለህ:: እናም እኔ መልእክትህን ማድረስ አለብኝ::
እሺ፣ ጌታ ሆይ:: አንተን በመታዘዝ ወደ ነነዌ ልሄድ ወይም እዚሁ ቀርቼ በዓሣ ነባሪው ሆድ ውስጥ ኑሮዬን ልመሠርት እችላለሁ:: (ምንም ያልተደነቀ በመምሰል አካባቢውን ይቃኛል) እዚህ ብዙም የሚሠራ ሥራ የለም:: እውነቱን ልንገርህና ጌታ ሆይ፣ እዚህ ቀይቼ የዓሣ ነባሪው እራት ለመሆን አልፈልግም! በተጨማሪም፣ ከአንተ ለመራቅ አልፈልግም! (እየተማረረ አካባቢውን ይመለከታል) ማለቴ፣ ይኼ የት እንደሚያደርሰኝ ተመልከት! (በምግቡና በቆሻሻው ውስጥ የሚንቦጫረቅ በመምሰል) ነነዌ ያን ያህል መጥፎ ልትሆን አትችልም!
(በኩርፍያ) እሺ፣ ጌታ ሆይ... ብቻ ቶሎ ብለህ ከዚህ አውጣኝና ፈገግ እያልሁ ወደ ነነዌ እሄዳለሁ!
(ወደ ላይ እየተመለከተ) ሄይ፣ ያ ምንድነው? (ያዳምጣል)... ይኼ ሰውዬ ሊያስነጥስ የሚፈልግ ይመስላል! (ደስ ብሎት) የመውጫ ዕድሌ አሁን ነው... (ዓሣ ነባሪውን ያባብለዋል) አህ...አህ... ፈጠን በል፣ አስነጥስ! (አሁንም ማባበሉን በመጨመር) አህ...አህ...ቹ!
(ከዓሣ ነባሪው ሆድ ሲወጣ) እግዚአብሔር ይባርክህ... እንግዲህ ደህና ሁን!! ነነዌ፣ ይኸው መጣሁልሽ... የአየር መልእክት!

ማስታወቂያዎች/መባ .. በወጣቶች አምልኮ መሪ

ልዩ መዝሙር: ስለ ሚሲዮን አገልግሎት የሚናገር መዝሙር።

መልእክት: ሰባኪው ወይም የወጣቶች መሪ ከመረጠው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስለ ሚሲዮን አገልግሎት እንዲሰብክ ጋብዝ።

ጸሎትና ፍጻሜ።



# በዕለተገና ክርስቶስን ማየት ይቻላልን?

ከበድ ሪዲ

**ማውጫ**
**ሰላምታና ጸሎት:** የወጣቶች የአምልኮ መሪ
**የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:** ኢሳይያስ 9:2-7
**መዝሙር:** የልደት መዝመር
**ልዩ መዝሙር:** ስለ ገና ወይም የክርስቶስ ጌትነት የሚናገር መዝሙር
**ማስታወቂያ/መባ:** በወጣቶች የአምልኮ መሪ
**ንድፍ:** «በዕለተገና ክርስቶስን ማየት ይቻላልን?»

ይህ «በዕለተገና ክርስቶስን ማየት ይቻላልን?» ለሚለው ጥያቄ የተዘጋጀ አስተዋጽኦ ነው። ይህም እንደ የመንገድ ላይ ቃለምልልስ ተደርጎ ሊቀርብ ይችላል። ሪፖርተሩ ማይክራፎንና የቴሌቪዥን ካሜራ በመያዝ ለገና በዓል ዕቃ ለመግዛት ወዲያወዲህ የሚሉ የሚመስሉትን ሰዎች ቃለምልልስ ያደርጋል።
ሪፖርተሩ: እንደምን አመሻችሁ? ከቲቪ4 ቤሪ የጎዳና ላይ ሪፖርተራችሁ ቤሪ ሄሪ እባላለሁ። ከዚሁ አካባቢ፣ «ገና ለአንተ ምን ትርጉም ይሰጥሃል?» የሚል ጥያቄ ለተለያዩ ሰዎች በማቅረብ ላይ ነኝ። ዛሬ ተራው ሰው ከገና በዓል ምን እንደሚያይ ለማወቅ እንፈልጋለን። ለመሆኑ ክርስቶስን በዕለተገና ማየት ይቻላልን?
ሪፖርተሩ የተለያዩ ወጣቶች ሲያልፉ፣ «የገና በዓል ለአንተ ምን ትርጉም ይሰጥሃል?» ምላሾቹ የሚከተሉትን ሊመስሉ ይችላሉ።
1. ብርሃናት 2. ስጦታዎች 3. ካርዶች 4. ብዙ ሕዝብ 5. ሙዚቃ 6. የትምህርት ቤት መዘጋት 7. ቤተሰብ 8. ፓርቲዎች 9. አዳዲስ ልብሶች 10. ገንዘብ

ከፈለግህ በዚህ ዝርዝር ውስጥ ሌሎች ነገሮች መጨመር ትችላለህ። እያንዳንዱ ሰው ባሕርዩንና የሚሰጠውን መልስ በሚያንጸባርቅ መልኩ መልበስ አለበት። ለናሙና ያህል የቀረቡትን መልሶች ቀጥለህ ተመልከት።

1. ብርሃን። (የፀሐይ መነጽር ያደረገ ወጣት) «ብርሃናት። የገና ብርሃናት በየቦታው ይታያሉ። ሉቆች፣ ዛፎች፣ መንገዶች፣ ቀይ፣ አረንጓዴ፣ ሰማያይ ብርሃናት። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ አንጸባራቂ ብርሃናት። ሰው ለማሳወር የሚችሉ ብርሃናት።»
2. ስጦታዎች። (ስግብግብ ወጣት፣ እጆቹን እያፋተገ) «ገና ለኔ ምንድነው? ስጦታዎች። ስጦታዎች። ስጦዎች። ብዙ ስጦታዎች። ጥቂት ስጦታዎች።» (ቃሉን እየደጋገመና እየሳቀ ይሰወራል።)

3. ትምህርት የለም። (በጣም የተደሰተ ወጣት) «ትቀልዳለህ? ገና ቀን ትምህርት አይኖርም።»
4. ገንዘብ። (እንደ ነጋዴ ሱቆን ገጭ ያደረገ ወጣት) «ገና ለኔ ምንድነው? ገና ብዙ ገንዘብ ማለት ነው። ዕቃ እየገዙ እኔን ሀብታም ለማድረግ የሚጥሩትን እነዚህን ሁሉ ሰዎች ተመልከት!»

እነዚህ ሁሉ ሰዎች ከተጠየቁ በኋላ፣ ሪፖርተሩ ወደ ካሜራው ተመልሶ፣ «መልካም፣ ነገሩ ልክ እኛ እንዳሰብነው ነው። ዛሬ ዛሬ ማንም ክርስቶስን በዕለተገና ሊያይ አልቻለም።» በዚህ ነጥብ ላይ አንድ መንገደኛ ምን እየሆነ እንዳለ ሊጠይቅ ይችላል። ሪፖርተሩ ለዚሁ ሰውዬ ተመሳሳይ ጥያቄ ያቀርብለታል። ሰውዬውም፣ «ገና ላንተ ምንድነው?» «ለኔ ገና ክርስቶስን ያስታውሰኛል» ሲል ይመልሳል። ሪፖርተሩ በምላሹ ተደንቆ፣ «ዛሬ ክርስቶስን እንዴት በዕለተገና ልትመለከት ትችላለህ?» ይለዋል።
መልሱ፣ «በርሃናትን ላይ የዓለም ብርሃን ሆኖ የመጣውን ጌታ አስባለሁ። ስጦታዎችን ሳይ በሕይወቴ ውስጥ ስለመኖሩና ለዓለም የእግዚአብሔር ስጦታ ሆኖ ስለመምጣቱ አስባለሁ። የገና ካርድ ስቀበል እግዚአብሔር ከሁሉም የላቀውን ስጦታ እስኪልክልኝ ድረስ እኔን መውደዱን አስታውሳለሁ። ሙዚቃ በምሰማበት ጊዜ መላእክት በመጀመሪያው የገና ዕለት ያዜሙትን ዝማሬ አስታውሳለሁ። ክርስቶስ በመከራ ውስጥ ላለች ዓለም ሰላም ማምጣቱን እገነዘባለሁ። ብዙ ሕዝብ ስመለከት፣ እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው በመውደድ ክርስቶስን ለሞት አሳልፎ እንደሰጠው እረዳለሁ። ወደ ፓርቲ ወይም የበዓል ፕሮግራም ስሄድ፣ ክርስቶስን ለመከተል የወሰኑት ሁሉ በሰማይ የሚካፈሉትን ታላቅ በዓል አስባለሁ። እንዲሁም ክርስቶስ፣ 'እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ። እኔም አሳርፋችኋለሁ' ሲል የተናገረውን ቃል አስታውሳለሁ። ከቤተሰቤ ጋር ስሆን በክርስቶስ በኩል የእግዚአብሔር ልጅ የመሆን ሥልጣን ማግኘቴን አስታውሼ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ። ገንዘብ በማወጣበት ጊዜ በሰማይ መዝገብ ይኖረኝ ዘንድ ስለተከፈለልኝ ታላቅ ዋጋ አስባለሁ። እንዲያውም፣ በማየው ነገር ሁሉ ውስጥ ክርስቶስን አየዋለሁ።»
ሪፖርተሩ ወደ ካሜራው ተመልሶ፣ «መልካም! ነገሩ ልክ እኛ እንዳሰብነው ነው። ዓይኖቻችሁን ከከፈታችሁ... በዕለተገና ክርስቶስን ልታዩ ትችላላችሁ» ሲል ይናገራል።
**መዝሙር**፡ "Open My Eyes, That I May See"
**የገና መልእክት፡** በመጋቢው፣ በወጣቶች መጋቢ፣ በወጣቶች መሪ ወይም በበሳል ወጣት የሚቀርብ
ጸሎትና ፍጻሜ።



# የክርስቶስ ዓይነት ፍቅር

ከበድ ሪዲ

**ጭብጥ** - በቅድመሁኔታዎች ላይ ያልተመሠረተ የክርስቶስ ፍቅር
**ዝግጅት** - በዚህ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ «አጠቃላይ የወጣቶች የአምልኮ አገልግሎት» የሚለውን ክፍል ቀደም ብለህ ካላነበብህ አሁኑኑ አንብብ።
**አስተዋጽኦ**

- **ሰላምታና ጸሎት** - በወጣቶች የአምልኮ መሪ
- **መዝሙር ቁ. 219** - "My Savior's Love"
- **ልዩ መዝሙር** - የወጣቶች ቡድን/ሶሎ ዘማሪ
- **ድራማ** - «አንድ ነጭ ጫማ የሚያደርጉ ሰዎች የሚገኙባት ከተማ»
  ይህ በቅድመሁኔታዎች ላይ ስላልተመሠረተ ፍቅር የሚናገር ድራማ በእንቅስቃሴ ብቻ (pantomime) የሚካሄድ ይሆናል። አሳቡ በጣም ቀላል ነው። አንድ ወጣት የሚከተሉትን ቃላት ሲያነብ ከመድረኩ በሌላኛው ጎን ሌሎች በእንቅስቃሴ ያሳያሉ።

| ቃላት | እንቅስቃሴዎች |
|---|---|
| በአንድ ወቅት አንድ ነጭ ጫማ የሚያደርጉ ሰዎች የሚኖሩባት ከተማ ነበረች። | *አንድ ነጭ ጫማ ያደረጉ ወጣቶች ይገባሉ።* |
| እነዚህ ሰዎች፣ መልካም ባሕርይ ነበራቸው። የመንግሥትን ቀረጥ በአግባቡ በመክፈል፣ ለልጆቻቸው ጥሩ ጥሩ ት/ቤቶች በመገንባት፣ ለቀይ መስቀል ብዙ ደም በመስጠት ኃላፊነታቸውን ይወጡ ነበር። | *ወጣቶቹ ኮራ ብለው ይጎማለላሉ (ጸጉራቸውን ያበጥራሉ፣ ጥፍሮቻቸውን ያጸዳሉ፣ ወዘተ.) ሦስት ወጣቶች ራሳቸውን ይስታሉ።* |
| ነገር ግን አንድ አስገራሚ ባሕል ነበራቸው። ይህም ከረዥም ጊዜ በፊት የተጀመረ በመሆኑ እስካሁን ለምን ይህንኑ እንደሚያደርጉ የሚያውቅ ሰው አልነበረም። | *ወጣቶቹ ግራ የተጋቡ በመምሰል ትከሻቸውን ይሰብቃሉ።* |
| ሁላቸውም አንድ ነጭ ጫማ ያደርጋሉ። | *አንድ ጫማ ያደረጉ ወጣቶች በአንድ መስመር ይሰለፋሉ።* |

| | |
|---|---|
| አንድ ቀን አንድ አዲስ ቤተሰብ ወደዚያው ከተማ መጣ:: | *አራት ወጣቶች በሁለቱም እግሮቻቸው ቀያይ ጫማዎችን አድርገው ይገባሉ::* |
| ሰዎቹ መልካም ባሕርይ ያላቸው ይመስሉ ነበር:: የከተማይቱም ሕዝብ ተቀበላቸው:: | *ከመድረኩ ላይ የቆዩት ወጣቶች ወደ አዲሶቹ ሰዎች በመቅረብ፣ «እንኳዋን ደህና መጣችሁ?» ብለው ይጨብጧቸዋል::* |
| በዚህ ጊዜ የከተማይቱ ከንቲባ አንድ ነገር አጤኑ:: | *ከዚያም አንድ ወጣት፣ «አሃ፣ እነዚህ ሰዎች ሁለት ጫማዎችን ነው የሚያደርጉት!» ሲል ይናገራል:: በዚህ ጊዜ ጠቅላላው ቡድን ቀስ በቀስ መሸሽ ይጀምራል::* |
| በዚህም ጊዜ የከተማይቱ ሰዎች በሙሉ ከነሱ ለየት ብለው በሚታዩት በነዚህ ሰዎች ላይ በአንድነት ተነሡ:: | *የቡድኑ አባላት፡ «እነሱ ከማን በልጠው ነው?» «ሁለት ጫማ?» «ደደቦች ይመስላሉ» «ጆኒ፣ ከነሱ ልጆች ጋር እንዳትጫወት»* |
| አዲስ የመጡት ቤተሰቦችም ከቤታቸው ውስጥ ተጨንቀው ያለቅሱ ጀመር:: | *አንዱ በሌላው ትከሻ ላይ እጆቹን ያሳርፋል:: አራቱ ወጣቶቹ በዚህ ዓይነት ተቃቅፈው በመመካከር ከማኅበረእመናኑ እይታ ይርቃሉ::* |
| የከተማይቱ ሕዝቦች እነዚህን ቤተሰቦች ከከተማይቱ ለማስወጣት እያቀዱ ሳለ፣ | *የቡድኑ አባላት እየተመካከሩና እያንሾካሾኩ ሳለ ድንገት የአዲሱን ቤተሰብ አባላት ይመለከታሉ::* |
| አንድ ወጣት ሁለት ጫማዎችን አድርጎ በመምጣት፣ «ለምንድነው ሁለት ጫማዎችን የምታደርጉት?» ሲል ጠየቃቸው:: | *አንድ ወጣት ከአዲሱ ቤተሰብ አባላት አጠገብ ቆሞ በምልክት ይጠይቃቸዋል::* |
| የአዲሱ ቤተሰብ አባወራም፣ | *የከተማይቱ ሰዎች ይህንን* |



| | |
|---|---|
| «በመጣንበት አገር ሰዎች ሁሉ ሁለት ጫማዎችን ነው የሚያደርጉት:: | *ንግግር ሲሰሙ በጉጉት ያዳምጡና፣ በአንድነት፣ «ነው እንዴ?» ሲሉ ይጠይቃሉ::* |
| «በመጣንበት አገር ጫማዎች ጥንድ ጥንድ ተደርገው ነው የሚሸጡት:: ሁለት ጫማዎችን የምናደርገው ጠፍጣፋ እግሮች ስላሉንም ነው» ሲሉ መለሱ:: | *«ነው እንዴ?» የከተማይቱ ሰዎች አሁንም ይጠይቃሉ::*<br>*«ይኼን አናውቅም ነበር» የከተማይቱ ሰዎች::* |
| ከንቲባውም ወደ ሰዎቹ ቀረብ ብለው፣ | *«ጠፍጣፋ እግሮች እንዳሏችሁ አናውቅም ነበር:: እኛ ያሰብነው መቼም...* |
| የከተማይቱም ሰዎች ሁለት ጫማዎችን ወደሚያደርጉት ሰዎች መጥተው ይቅርታ ጠየቋቸው:: | *አንድ በአንድ ይቅርታ ይጠይቋቸውና ከመድረኩ ይወርዳሉ::* |
| ያን ዕለት የከተማይቱ ሰዎች፣ «እያንዳንዱ ወንድ፣ ሴት፣ ወንድ ልጅ፣ ሴት ልጅ ታሪክ እንዳላቸውና ፍቅር ታሪካቸውን ለመስማት ጊዜውን እንደሚሠዋ» ተገነዘቡ:: | |

- **ልዩ መዝሙር**
- **መዝሙር ቁ. 221** - "And Can It Be?"
- **የመልእክቱ አስተዋጽኦ**

**የክርስቶስ ዓይነት ፍቅር**
**ገላትያ 5:22-25**
**መግቢያ**: አንድ አማኝ ለሁለንተናዊ ቅድስና በመንፈስ ቅዱስ በሚሞላበት ጊዜ ፍጹም አዲስ ሕይወት ይጀምራል:: ነገር ግን በመንፈስ መመላለስን መማር በአንድ ጊዜ የሚፈጸም አይደለም:: ይሄ ጊዜ የሚወስድ ሂደት ነው:: በሌላ አገላለጽ፣ አንድ ሰው ሁለንተናዊ ቅድስና አገኘ ማለት ስለ ፍቅር፣ ደስታ፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ የዋህነትና ራስን መግዛት ማወቅ የሚገባውን ሁሉ ያውቃል ማለት አይደለም:: እነዚህን ለመማር

ረኸርም ጊዜን ይጠይቃል:: ዛሬ ከመንፈስ ፍሬ አንዱ ስለሆነው ፍቅር አጽንኦት ሰጥተን እንማራለን:: ከክርስቶስ ሕይወት የክርስቶስ ዓይነት ስለሆነው ፍቅር የሚከተለውን እንማራለን::

1. ክርስቶስ ያለ ምንም ቅድመሁኔታ ሰዎችን ወዷቸዋል (ፍቅሩ እንከንየለሽ ነበር:: ዮሐንስ 3:16-«ሁሉ»)
   ሀ. እርሱ ቅዱሳንንና ኃጢአተኞችን፣ ባሪያዎችንና ነጻ ሰዎችን፣ ሀብታሞችንና ድሆችን፣ አይሁዶችንና ጨዋዎችን ይወዳል::
   ለ. ምናልባትም መንፈስ ቅዱስ፣ «ወደዚህ ወደ ክርስቶስ ሕይወት ድረሱ... ከናንተ ጋር የሚስማሙትን፣ እንደናንተ ያሉትን ሰዎች ውደዱ:: ይኼ ትልቅ ነገር አይደለም!» እያለ ይሆናል (ሉቃስ 6:27-35 አንብብ)::
   ሐ. ክርስቶስ ግን ያለምንም ቅድመሁኔታ ሰዎችን ይወዳል::
   መ. ማብራሪያ:

   ከሌሎች ለየት ያለ በመሆኑ ምክንያት ብዙ ጓደኞች የሌሉት አንድ ተማሪ ነበር:: በቫሌንታይን ቀን ዋዜማ (ፍቅረኞች የሚያከብሩት በዓል) በክፍሉ ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች ሁሉ የሚሰጠውን የቫሌንታይን ስጦታ ለማዘጋጀት ማቀዱን ለእናቱ ነገራት:: ለረኸርም ሰዓታት ወረቀቶችንና ቀለሞችን ተጠቅሞ በክፍሉ ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች ሁሉ የሚበቃ ፖስት ካርድ ሠራ:: የሠራቸውን ካርዶች በወረቀት ቦርሳ ውስጥ ከጨመረ በኋላ የደከመ ገላውን ለማሳረፍ ወደ አልጋው አመራ::
   በሚቀጥለው ቀን እናቱ ልጁ የሰጠውን ያህል ብዙ የቫሌንታይን ስጦታ አያገኝም ይሆናል ብላ ስትሰጋ ቆየች:: ስለሆነም፣ ብዙ ብስኩቶችን ስትሠራለት ዋለች:: 9:30 ላይ አውቶቡሱ ልጇን ይዞ መጣ:: እሷ ቆማ ወደነበረችበት መስኮት፣ «አንድም እንኳዋን፣ አንድም እንኳዋን» እያለ ሲመጣ ሰማችው:: ያንን ሁሉ ስጦታ ሰጥቶ ምንም የቫሌንታይን ስጦታ እንዳላገኘ በመገመት ልቧ ተረበሸ:: በሩን ከፍቶ ሲገባ፣ «እንዴት ነበር?» ስትል ጠየቀችው:: እሱም ፊቱ በፈገግታ ተሞልቶ፣ «እማማ፣ አንዱንም ሰው አልረሳሁም ነበር... አንዱንም እንኳዋን!» ሲል መለሰላት::
   አጋፔ ፍቅር፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ምንም ምላሽ ሳይጠብቅ ይሰጣል::

2. ክርስቶስ በመሥዋዕትነት ሰዎችን ወዷቸዋል (ፍቅሩ ራሱን ለጉዳት ቢያጋልጠውም ይህንኑ ከማድረግ አልተቆጠበም)::
   ሀ. ነቅተው በመጸለይ ሊያግዙት ያልቻሉ ደቀመዛሙርትን ሳይቀር ወዷቸዋል... የሚገድሉትን ሰዎች ወዷቸዋል... ችላ ብለው የሚተውትን ሰዎች ወዷቸዋል:: ሊወደዱ የማይችሉትን



   ሰዎች ወዷቸዋል:: ለኃጢአተኛው የሰው ልጅ የነበረው ፍቅሩ ከእንጨት ላይ አሰቅሉታል::
   በ. ምናልባትም መንፈስ ቅዱስ፣ «እስኪ፣ ወደዚህ ኑና ተመልከቱ:: የሚወዷችሁ ትወዳላችሁ:: የሚጠሏችሁንስ? የመውደድ ስሜት በማይኖራችሁስ ጊዜ? የናንተ ፍቅር ምንም ኪሳራ አያደርስባችሁም:: የርሱ ፍቅር ግን ሁሉንም ነገር እንዲያጣ አድርጎታል» እያለ ይሆናል::
   ሐ. ፍቅር ውድ ዋጋ ያስከፍላል:: ፍቅር ሕይወታችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይጠይቃል (ዮሐንስ 3:16)::
   መ. ኢየሱስ ራሱን በመሠዋት ፍቅሩን ይገልጻል::
   ሠ. ሰዎችን በአጋፔ ፍቅር ብትወዱ...

3. ክርስቶስ ከራስወዳድነት በጸዳ መንፈስ ሰዎችን ወዷቸዋል (የሚያገኘው ትርፍ ባይኖርም ሰዎችን ወዷቸዋል)::
   ሀ. ፊልጵስዩስ 2:1-8::
   ለ. ክርስቶስ የወደደው አስፈላጊ የሆኑትን፣ ሕይወቱን ሊያሻሽሉለት የሚችሉትን ወይም መልሶ የሚወዱትን ሰዎች አልነበረም:: ያፈቀረው ጥቅም ለማግኘት በማሰብ አልነበረም:: ሰውን ሲቀርብ የልብ ፍላጎቶቹ ቅይጥ አልነበሩም:: እኔስ ከዚህ ምን አገኛለሁ? ብሎ አልጠየቀም::
   ሐ. ምናልባት መንፈስ ቅዱስ፣ «ወደዚህ ኑና ተመልከቱ:: የልባችሁ ፍላጎት ምንድነው? ፍቅር/ክብር/ፈውስ/ደኅንነት ለማግኘት ነውን?» እያለ ይሆናል::
   መ. ክርስቶስ ከራስወዳድነት በጸዳ መንፈስ ሰዎችን ወዷቸዋል:: አንተስ ከራስወዳድነት በጸዳ መንፈስ ለማፍቀር ፈቃደኛ ነህን?

ማጠቃለያ: እስኪ ለሰዎች ፍቅርን ከመፍጠርና ከመስጠት የሚመጣውን ደስታ እንድትለማመዱ የሚያግዟችሁን ጥቂት መሠረታዊና ቀላል ዘዴዎች እንመልከት::

1. ሌሎችን አድምጥ:: ክርስቶስ ይህ ብቃት ነበረው:: እኛም ሊኖረን ይገባል::
2. ለሰዎች ደኅንነት/ደስታ ግድ ይበልህ:: (ሰዎች እንዲያደርጉልህ የምትፈልገውን አድርግላቸው::)
3. በመጨረሻም፣ ልትወደው በምትፈልገው ሰው ሕይወት ውስጥ ክርስቶስ በምሥጢራዊ ሁኔታ የሚገኝ መሆኑን ተገንዘብ:: (ከነዚህ ከታናናሾች ለአንዱ የምታደርጉት ለእኔ እንዳደረጋችሁት ነው::)

ኢየሱስ በነሱ ሕይወት እንዳለ ስንገነዘብ፣ ሰዎች ሁሉ ሊወደዱ የሚችሉ ይሆናሉ::

ምላሽ (ወይም መዝጊያ) - ሁሉንም ሰው በአንድ ቡድን ሰብስብ:: «መውደድ ያሉብን ማንን ነው?» ጥቁር ሰሌዳ ወይም ትልቅ ወረቀት በመጠቀም የሚከተለውን አብራራላቸው::

በእንግሊዝኛ ቋንቋ ኢየሱስን ስናስቀድም፣ ሌሎችን ስናስከትልና ራሳችንን ከመጨረሻው ላይ ስናስቀምጥ! ደስታን እንደምናገኝ የሚያመለክት ጽሑፍ እንደሚከተለው ልታዘጋጅ ትችላለህ::

Jesus (ኢየሱስ)
Others (ሌሎች ሰዎች)
Yourself (ራስ)

የክርስቶስ ዓይነቱን ፍቅር በተመለከተ "JOY" የሚለው ቃል ምንን እንደሚያሳይ ጠይቃቸው:: እግዚአብሔር በሕይወታችሁ ውስጥ ያስቀመጧቸው «ሌሎች ሰዎች» እነማናቸው?

እግዚአብሔር የክርስቶስን ዓይነት ፍቅር እንድታሳዩ እንዲያግዛችሁ በመጠየቅ ጸልዩና ከፍለጊዜውን ፈጽሙ::

- *የመዝጊያ መዝሙር* **ቁ. 220**: "Such love"; "It's love that makes the world go round."
- *አማራጭ መዝጊያ*: ለተማሪዎቹ ወረቀት በመስጠት ለእግዚአብሔር የፍቅር ደብዳቤ እንዲጽፉ አድርግ:: አንዳንድ ደብዳቤዎችን በሚቀጥለው የወጣቶች አገልግሎት ወይም የወጣቶች ስብሰባ ላይ አንብብ:: ወይም በቤተክርስቲያን የማስታወቂያ መለጠፊያ ቦርድ ላይ ለጥፍ::

# በወንድማማች መዋደድ እርስበርሳችሁ ተዋደዱ
# ሮ ሜ 1 2 : 1 0



## ይኸው ደስታ በልቤ ውስጥ ፈሷል
ከበድ ሪዲ

**ጭብጥ**: በእማኝ ሕይወት ውስጥ የጌታን መኖር ከሚያሳዩት ነገሮች አንዱ ደስታ ነው:: የክርስቶስ ኢየሱስ ተከታዮች እንደመሆናችን፣ እውነተኛና ዘላቂ ደስታ የሚመጣው ከጌታ ሲሆን፣ ይህም ለሰዎች በምንሰጠው አገልግሎት አማካኝነት የሚገለጥ ነው::

**አስተዋጽኦ**

- **ሰላምታና ጸሎት** - በወጣቶች የአገልግሎት መሪ
- ***መዝሙር* ቁ. 422**-"Joy Unspeakable"; "This Joy Thate I Have"; "I Have Got I Joy Bell in My Heart"
- ***ልዩ መዝሙር*** - ወጣት መዘምራን ወይም ወጣት ሶሎ ዘማሪ
- ***ድራማ*** - «ደስታን ፍለጋ»

**ገጸባሕርያት**

ደስታ የምትባል ፍልቅልቅ ልጅ::
ባለሰደሪያ ሱፍ የለበሰ ነጋዴ የሚባል ኮስታራ ሰውዬ::
በመካከለኛ ሁኔታ ላይ የሚገኝ መካከለኛ የሚባል ሰውዬ::
የመጠጥ ጠርሙስ የያዘ ስሙ «ማንም» የሚባል ሰካራም::

**መድረክ**: 3በ5 ኢንች የደስታና የጠርሙስ ፎቶ ተሰቅሏል:: ከአንድ ወንበርና ጠረጴዛ በስተቀር ሌላ ነገር አይታይም:: *(መጋረጃው ሲከፈት ሁለት ወጣቶች ይታያሉ:: አንደኛው ወጣት ሱፍ ለብሶ ከጠረጴዛው አጠገብ ባለው ወንበር ላይ ተቀምጦአል:: ሥራው ሙሉ ለሙሉ የተቆጣጠረው የሚመስል ነጋዴ መሆኑ ከሁኔታው ያስታውቃል:: ሌላኛው ወጣት! ቡቱቶ ለብሶና ጠርሙስ ይዞ ከመድረኩ ሌላኛው ጠርዝ ባለው ወለል ላይ ተቀምጦዋል:: አንድ መካከለኛ ወጣት የደስታን ፎቶ ይዞ ይገባል:: ወዲያ ወዲያ እያለ አንድ ሰው ይፈልጋል:: ይህም ወንበሩ ላይ የተቀመጠውን ወጣት ይረብሸዋል:)*

**ነጋዴ**: ሄይ፣ ማነህ?
**መካከለኛ**: እ፣ እኔ መካከለኛ እባላለሁ
**ነጋዴ**: እሃ! መካከለኛ የሆነ ሰው የምትፈልግ መሰለኝ
**መካከለኛ**: እዎ *(ፍለጋውን ይቀጥላል - ወዲያ ወዲህ እየቃኘ)*
**ነጋዴ**: *(ፈጠን ብሎ)* ማንን ነው የምትፈልገው?
**መካከለኛ**: ደስታን
**ነጋዴ**: ማን?

**መካከለኛ**: *(ፊራ ተባ እያለ ፎቶውን ከተመለከተ በኋላ)* ደስታ የማይነገር.. እዚህ እንደማገኛት ነግረውኝ ነበር::
**ነጋዴ**: *(ቅጭም ብሎ)* የሰማኸው የተሳሳተ ዜና ነው:: ደስታ እዚህ የለችም::
**መካከለኛ**: *(በጣም ረጋ ብሎ)* አ - - - ስለረበሽኩህ ይቅርታ አድርግልኝ:: (*መካከለኛ መንገድ ከጀመረ በኋላ ቆም ይልና ነጋዴው ወደተቀመጠበት ወንበር ይመለሳል*) እንዴት አወቅህ?
**ነጋዴ**: ምኑን ነው የማውቀው?
**መካከለኛ**: *(በራሱ ይበልጥ እየተማመነ)* ደስታ እዚህ እንደሌለች እንዴት አወቅህ?
**ነጋዴ**: ስሜ ነጋዴ ይባላል:: እዚህ የመጣሁት ደስታን ፍለጋ ነበር:: ነገር ግን አላገኘኋትም::
**መካከለኛ**: *(በመገረም)* ደስታን ለመፈለግ ነው እዚህ ድረስ የመጣኸው? ይህችኛውን ደስታ? *(ፎቶዋን ያሳየዋል)*
**ነጋዴ**: አዎ፣ እሷኑ ነው:: ከአያሌ ዓመታት በፊት እሷን ፍለጋ እዚህ መጣሁ:: ተግቶ በመሥራት ብዙ ገንዘብ ማካበት ከተቻለ ደስታን ፍለጋ መሄድ እንደማያስፈልግ፣ ራሷ ደስታ ሀብታሙን ሰው ፈልጋ እንደምታገኘው አምን ነበር:: ነገር ግን ተግቼ በመሥራት ብዙ ሀብት ባገኝም፣ እስካሁን ደስታን አላገኘኋትም::
**መካከለኛ**: እህ፣ እዚሁ አካባቢ በማንዣበብ ደስታን በተስፋ ብጠብቅ የማገኛት ይመስልሃል? እውነቱን ነው የምልህ ባገኛት በጣም ደስ ይለኛል::
**ነጋዴ**: ትችላለህ:: *(መካከለኛ ለአፍታ ቆም ብሎ እንደ ቆየ ከወዲያኛው ጠርዝ ወለል ላይ የተቀመጠውን 'ማንም'ን ያየዋል:: ማንም ብዙ ጠጥቷል::)*
**መካከለኛ**: አቶ ነጋዴ፣ ያ ማነው?
**ነጋዴ**: ማንም:: (*መካከለኛ ወደዚያው ይሄዳል::*)
**መካከለኛ**: ይቅርታ አድርግልኝና ደስታ የማይነገር የምትባል ልጅ ስፈልግ ነበር:: የት እንደምትገኝ ታውቃለህ?
**ማንም** *(በኃዘን ድምፅ)* የት እንደማትገኝ አውቃለሁ:: እዚህ ውስጥ ልታገኛት አትችልም (ወደ ጠርሙሱ እየጠቆመ)
**መካከለኛ**: ጠርሙስ ውስጥ? በርግጥ እዚህ አትገኝም:: ደስታን ማን ከጠርሙስ ውስጥ አግኝቶ ያውቃል *(ሳቅ ይላል)*
**ማንም**: ብዙ ጓደኞቼ እዚህ እንደምትገኝ ነግረውኝ ነበር:: በቴሌቪዥን ላይ ሲነገርም ሰምቼ ነበር *(ሊያዝን)*:: በመቶዎች የሚቆጠሩ ጠርሙሶች ብጠጣም፣ ደስታን አላገኘኋትም::
**መካከለኛ**: *(በርሕራሔ ስሜት)* አ፣ በጣም ነው የማዝነው:: እንዴ ደግፌ ላስነሣህ:: እንሂድና ቆንጆ ምግብ ልጋብዝህ:: ከብርድ የሚከላከል ኮትም እገዛልሃለሁ:: እስኪሻልህ ድረስ ከኔ ቤት ልትቀመጥ ትችላለህ::



**ማንም**: *(መካከለኛ ደግፎ ሲያስነሣው)* በጣም አመሰግናለሁ:: ሰው እንዲህ ያለ ደግነት ሲያደርግልኝ አይቼ አላውቅም:: *(ወዲያውም በፈገግታ ያሸበረቀች ወጣቷ ደስታ ከመካከለኛና ማንም ኋላ ኋላ ትከተል ጀመረ:: መካከለኛ ዞር ብሎ ያያታል::)*
**መካከለኛ**: በፎቶው ውስጥ ያለሽው ልጅ አንቺ አይደለሽ? አንቺ ደስታ የማይነገር ነሽ! ቢንት ቦታ ፈለግሁሽ!
**ደስታ**: *(ፈገግ ብላ)* በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ይፈልጉኛል:: የሚያገኙኝ ግን ጥቂቶች ናቸው::
**መካከለኛ**: እውነትሽን ነው? ታዲያ አን እንዴት አገኘሁሽ?
**ደስታ**: አንተ አላገኘኸኝም:: እኔ አገኘሁህ እንጂ:: ልክ አንተ ይህን ምስኪን እንደምትረዳው በችግር ላይ ያሉትን ወደሚረዱት ሰዎች እመጣለሁ:: ለሰዎች በሚሰጥ የፍቅር አገልግሎት እንጂ በነዚህ ነገሮች (ወደ ነጋዴው ወንበርና የማንም ጠርሙስ ትመለከታለች) እኔን ማግኘት አይቻልምና::
**መካከለኛ**: ደስታ መቼም እንደማትለይኝ ተስፋ አደርጋለሁ::
**ደስታ**: ደግና ለሌሎች የምታስብ አገልጋይ እስከሆንህ ድረስ ሁልጊዜም ከኋላህ እከተላለሁ:: *(ማንምና መካከለኛ እጅ ለእጅ ተያይዘው ከመድረኩ ሲወጡ፣ ደስታ ከኋላ ኋላቸው ትከተላለች::)*

- ጸሎት /ማስታወቂያዎች/ መባ
- ልዩ መዝሙር
- የስብከቱ አስተዋጽኦ

## ልቤ በደስታ ተሞልቷል

ገላትያ 5:22-25

**መግቢያ**: አንድ ሰው ሁለንተናዊ ቅድስና አገኘ ማለት በመንፈስ ቅዱስ እየተመላለሰ ነው ማለት አይደለም:: ስለ ፍቅር፣ ደስታ፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ የዋህነትና ራስን ስለመግዛት ማወቅ የሚገባውን ሁሉ ያውቃል ማለት አይደለም:: እነዚህን ነገሮች ማወቅ የሚቻለው መንፈሳዊ ዕድገትና ብስለት ሲኖር ነው:: ዛሬ ከመንፈስ ፍሬ አንዱ ስለሆነው ደስታ አጽንኦት ሰጥተን እንማራለን::

1. ክርስቲያናዊ ደስታ ሁሉም አማኞች ሊለማመዱት የሚገባው ነው:: «የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና» (ሮሜ. 14:17)::
2. ሰው ክርስቲያናዊ ደስታን ሊፈጥር አይችልም:: ፍሬ የሚፈጠረው በመንፈስ ቅዱስ ሲሆን፣ በክርስቲያኑና በመንፈስ ቅዱስ መካከል የሚገኝ ተገቢ ግንኙነት ውጤት ነው::

የክርስቲያናዊ ደስታ ምንጩ በኛ ውስጥ ያለው የመንፈስ ቅዱስ ሕይወት ነው። «የተስፋ አምላክም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል . . . ደስታንና ሰላምን ሁሉ ይሙላባችሁ» (ሮሜ.15:13)።

3. ክርስቲያናዊ ደስታ ከስሜት ያለፈ ነው። የላይ ላይ ወይም ግብዝነትም አይደለም። ነገር ግን ክርስቲያናዊ ደስታ በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላ ሕይወት ጥልቅ ምንጮች የሚቀዳ የፍቅር ነፀብራቅ ነው። ደስታ የክርስቲያኖች ተለምዷዊ ባሕርይ ከሆነና የመንፈስ ፍሬ ከሆነ፣ ዛሬ በቤተክርስቲያንና በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉት ሰዎች ሕይወት ውስጥ በብዛት የማይታየው ለምንድነው? ይህ በመንፈስ በመመላለስ ልናድግበት የሚገባው ፍሬ ነው። ስለ ክርስቲያናዊ ደስታ ሦስት ነጥቦች ከዚህ በታች ተገልጸዋል።

1. ክርስቲያናዊ ደስታና እግዚአብሔርን መታዘዝ ጎን ለጎን የሚሄዱ ነገሮች ናቸው።
ሀ. ክርስቲያናዊ ደስታና መሰጠት ጎን ለጎን ይሄዳሉ።
ለ. ጳውሎስ በገላትያ 5 ውስጥ እንደገለጸው፣ እግዚአብሔርን አለመታዘዝ አድመኛነትን፣ በቅንዓት የተሞላ ቁጣን፣ ክርክርን፣ አለመስማማትን፣ ክፍፍልንና ምቀኝነትን ያስከትላል።
ሐ. ነገር ግን ታዛዥነት ደስታን ያስከትላል። ክርስቶስ በሉቃስ 11:28፣ «የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰሙና የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው» ብሏል።
መ. ጆን ዌስሊ ቅድስናና ደስታ እግዚአብሔር በሰው ሕይወት ውስጥ በሚነግሥበት ጊዜ የሚከሰቱ ቅጽበታዊ ፍሬዎች እንደሆኑ አስረድቷል።
ሠ. ደስታ የተጋነነ ስሜታዊ መፍነክነክ ሳይሆን፣ ነፍሳችን በእግዚአብሔር በራሱ ደስ ከመሰኘቱ የተነሣ የሚካሄድ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ሙሉ በሙሉ መታዘዝ ነው።
ረ. ለእግዚአብሔር ታዛዥ ያልሆንክበት የሕይወት ክፍል አለን? በሕይወትህ ውስጥ እውነተኛ ክርስቲያናዊ ደስታ የማይታየው በዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል።
ሰ. በመንፈስ ስትመላለስ እርሱ ደስታውን በውስጥህ ያፈራል።

2. ክርስቲያናዊ ደስታ የሕይወትን መከራዎች የምንጋፈጥበትን ብርታት ይሰጠናል።
ሀ. ኤርምያስ የጌታ ደስታ ብርታታችን መሆኑን አምኗል (8:10)።
ለ. ያእቆብ ልዩ ልዩ መከራ ሲደርስብን እንደ ሙሉ ደስታ እንድንቆጥር ያበረታታናል። (1:2)



ሐ. በሌላ አገላለጽ፣ ደስታ ኃይልን በመስጠት ያበረታታናል። የመንፈስ ቅዱስ የሆነው ደስታ የሌላቸው ሰዎች ወደ ሌሎች የሕይወታችን ገጽታዎች የሚሰራጨውን ብርታት ሊያገኙ አይችሉም።

3. ክርስቲያናዊ ደስታ የቤተክርስቲያን ትልቁ ማስታወቂያ ነው።
ሀ. ካርል ባርት ብዙ ሰባኪዎች በማይደመጡበት ስፍራ ደስታህ ስለክርስቶስ ይመሰክራል ብሏል።
ለ. ማብራሪያ፡ ቢሊ ግርሃም አገልግሎታቸውን በመጀመር ላይ በነበሩበት ወቅት ከተሰወጡት ሰዎች አንዱ የሙዚቃ ፕሮፌሰር ነበር። ስብሰባው ሊያልቅ ሲል ፕሮፌሰሩ ወደ ቢሊ ግርሃም መጥቶ፣ «ችግር አለብኝ። ክርስቲያን የሆንሁ መስሎ አይሰማኝም። ባለቤቴም ሕይወቷን ለክርስቶስ አሳልፋ እንድትሰጥ ላሳምናት አልቻልሁም» አለ። ወጣቱ ግርሃም ፕሮፌሰሩን በመመልከት ችግሩን አወቁ። ሰውዬው ረዥም ጥቁር ካፖርት፣ ጥቁር ክራባት፣ ጥቁር መነጽር አድርጎ ነበር። ከዚህም በላይ ፊቱ ተከሳትሮ ነበር። ግርሃም፣ «እስኪ ምን እንደምትመስል ተመልከት። በክርስቶስ ለሚገኝ ሕይወት መልእክት የምታስተላልፍ ማስታወቂያ አትመስልም። የጌታ ደስታ ያስፈልግሃል» ሲሉ በግልጽ ነገሩት። ከዚያም ጸለዩለት። ከሁለት ዓመታት በኋላ፣ ፕሮፌሰሩና ባለቤቱ ቢሊ ግርሃም ወደሚሰብኩበት መድረክ ወጡ። ፕሮፌሰሩ በተለያዩ ቀለማት ያጌጠ ኮትና ቀይ ክራባት ለብሶ ፈገግ እያለ ሲመጣ ቢሊ ግርሃም ለይተው አላወቁትም። «ወንድሜ ግርሃም፣ ይህቺ ባለቤቴ ናት። በቅርቡ በክርስቶስ አምናለች» ሲል ነገራቸው።

ማጠቃለያ፡ ዛሬ ምን እንደሚያስፈልገን ታውቃላችሁ? የጥንቱ የመንፈስ ቅዱስ ደስታ ያስፈልገናል። ይኼ እንዴት ሊሆን ይችላል?
1. እግዚአብሔርን ታዘዙ።
2. ሁሉንም አጋጣሚ በመጠቀም በሕይወታችሁ ውስጥ ያለውን የጌታ ደስታ ግለጹ። ይህም ምስክርነቶችን፣ ዝማሬን፣ ውይይቶችን (ጌታ በሕይወታችሁ ውስጥ የፈጸማቸውን ግሩም ነገሮች ያጠቃልላል።
3. የደስታ መተላለፊያ አሸንዳ ሁኑ። በዓላማችሁ ውስጥ አዎንታዊ ኃይል ለመሆን ቁረጡ። አሉታዊና ጽልመታዊ ውይይት ካጋጠመህ፣ ወደ አዎንታዊ መልሰው ወይም ወደ አንተ ከመተላለፉ በፊት ከአካባቢው ራቅ።
4. በሌሎች ደስታ ለመደሰት ሞክር። የደስታ ምሥጢሩ ይኼ ነው

5. ደስታ ከነገሮች፣ ከሥልጣን ወይም ከኃይል የሚገኝ እንዳልሆነና መንፈስ ቅዱስ በሰው ሕይወት ውስጥ የሚያፈራው ፍሬ እንደሆነ ተገንዘብ።

**የመዝጊያ አዝማቾች** - «The joy of the lord is my strength», «If you want joy», «I've got the joy- - - Down in my heart», «I've got joy like a fountain»






## ጊዜው አሁን ነው
ከበድ ሬዲ

**ጭብጥ:** የአዲስ ዓመት መጀመሪያ የሕይወት ግቦችን ለመወጠንና በዓለማችን ላይ አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት እጅግ አመቺ ጊዜ ነው። ይህ የአምልኮ ፕሮግራም ወጣቶች ለእግዚአብሔር ፈጣን እርምጃ እንዲወስዱ የሚያሳስብ ጥሪ ነው።

**አስተዋጽኦ**
- **ሰላምታና ጸሎት** - በወጣቶች የአምልኮ መሪ
- **መዝሙር ቁ.372** - «I am resolved»
- **ልዩ መዝሙር** - ወጣት መዘምራን (ዘማሪ)
- **የአንባቢዎች ቲያትር** - «አንድ ቀን በመንገድ ላይ»

**ገጸ ባሕርያት**
አንባቢ1
አንባቢ2
እጩ ደቀመዝሙር1
እጩ ደቀመዝሙር2
እጩ ደቀመዝሙር3

**አንባቢ1:** አንድ ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ በመንገድ ላይ እየሄደ ሳለ ሕዝቡን ለማስተማር ቆመ።
**አንባቢ2:** ይገርማል፣ ክርስቶስ እንዴት ብዙ ሕዝብ ወደራሱ እንደሚስብ ያውቅ ነበር።
**አንባቢ1:** በሚገባ። ነገር ግን ክርስቶስ የፈለገው ተከታዮችን ብቻ አልነበረም።
**ነገር ግን - - -**
**አንባቢ1 እና 2:** ደቀመዛሙርትን ይፈልግ ነበር!
**አንባቢ1:** ንግግሩን ሲጨርስ
**አንባቢ2:** አንድ ወጣት ከሕዝቡ መካከል ብቅ ብሎ፣
**እጩ ደቀመዝሙር1** *(እየተጣደፈ)* እኔ እከተልሃለሁ። ክርስቶስ ሆይ፣ በምትሄድበት ሁሉ እከተልሃለሁ።
**አንባቢ2:** በሚሄድበት ሁሉ?
**እጩ ደቀመዝሙር1:** በሚሄድበት ሁሉ!
**አንባቢ2:** ልጄ፣ ክርስቶስ ምን አለ?
**ሁሉም:** «ቀበሮዎች ጉድጓድ ወፎችም ጎጆ አላቸው - - -»

አንባቢ1: (እያዘነ) «የሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም::»
አንባቢ2: ቦታ የለውም?
አንባቢ1: ቦታ የለውም!
አንባቢ2: ክርስቶስ ይህን ሲል ምን ማለቱ ነው? *(ለእጩ ደቀመዝሙር1)* ከልብህ ልትከተለው የፈለግህ ይመስል ነበር::
እጩ ደቀመዝሙር1: ክርስቶስ የኔ ተከታይ መሆን የሚያስከፍልህን ዋጋ ታውቃለህ ወይ? ብሎ የጠየቀኝ ይመስለኛል:: ሁሉንም ነገር ያስከፍልሃል ማለቱ ነው::
አንባቢ2: ሁሉንም ነገር?
ሁሉም: ሁሉንም ነገር!
አንባቢ1: ከዚያም ኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር መንግሥት ሊጠቅም የሚችል ሌላ ሰው አይቶ «ተከተለኝ» አለው::
እጩ ደቀመዝሙር2: እሺ እከተልሃለሁ:: መጀመሪያ ግን ሄጄ አባቴን እንድቀብር ፍቀድልኝ::
አንባበ2: *(እያዘነ)* በጣም ነው የማዝነው:: ክርስቶስ ምን አለ?
አንባቢ1: ክርስቶስ!
ሁሉም: «ሙታን ሙታናቸውን ይቀበሩ አንተ ግን - - »
አንባቢ1: *(በድፍረት)* «ሂድና በሁሉም ስፍራ የእግዚአብሔርን መንግሥት አውጅ::»
አንባቢ2: አሃ:: ሙታን ሙታናቸውን ይቅበሩ? ክርስቶስ ምን ማለቱ ይመስልሃል?
እጩ ደቀመዝሙር2: ክርስቶስ ዛሬውኑ አድርግ የምልህን ነገር ለነገ አታሳድር ማለቱ ይመስለኛል:: ቅጽበታዊ ምላሽ እፈልጋለሁ ማለቱ ነው::
አንባቢ2: አሁኑኑ?
ሁሉም: አሁኑኑ!
አንባቢ1: ሌላ እጩ ደቀመዝሙር ከሕዝቡ መካከል ብቅ ብሎ፣
እጩ ደቀመዝሙር3: እከተልሃለሁ፣ ጌታ ሆይ:: ነገር ግን መጀመሪያ ቤተሰቦቹን እንድሰናበት ፍቀድልኝ አለው::
አንባቢ2: ጥሩ ምላሽ ይመስለኛል::
እጩ ደቀመዝሙር3: ክርስቶስ ግን «ማንም እርፍ ይዞ ወደኋላ የሚያይ ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይደለም» አለ::
አንባቢ2: እንዴ? ይኼ ትንሽ ጠጣር ያለ አነጋገር አይመስልህም?
እጩ ደቀመዝሙር3: አዎ፣ እኔ መጀመሪያ እንደዚያ መስሎኝ ነበር:: በኋላ ግን ክርስቶስ ሕይወታችንን ሙሉ በሙሉ ለርሱ እንድንሰጠው የሚፈልግ መሆኑን ተረድቼአለሁ::
አንባቢ2: ሁለንተናን ማስረከብ?
ሁሉም: አዎን፣ ሁለንተናን ማስረከብ!
አንባቢ1: ጊዜያችንን!



አንባቢ2: ሀብታችንን!
እጩ ደቀመዝሙር1: ችሎታችንን!
እጩ ደቀመዝሙር2: ብቃታችንን!
እጩ ደቀመዝሙር3: አለመብቃታችንን!
አንባቢ1: መስጠታችን - - -
ሁሉም: የተሟላ መሆን አለበት! ከዚያ ያነሰ ሕይወት ሊኖረን አይገባም!
አንባቢ1: ስለሆነም፣ የክርስቶስ ደቀመዝሙር ለመሆን ከፈለጋችሁ...
አንባቢ2: እኔ የርሱ ደቀመዝሙር ለመሆን እፈልጋለሁ!
አንባቢ1: እንግዲያው - - -
እጩ ደቀመዝሙር1: ዋጋህን መተመን አለብህ::
እጩ ደቀመዝሙር2: ቅጽበታዊ ምላሽ መስጠት አለብህ::
እጩ ደቀመዝሙር3: ሕይወትህን ሙሉ በሙሉ ለርሱ አሳልፈህ መስጠት አለብህ::

- **መዝሙር** - «Give of your best to the master», «Take up your cross and follow Jesus»
- **ጸሎት /ማስታወቂያ/ መባ**
- **የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት: መክብብ 3:1-11**

**አማራጮች:** 1. አንድ ወጣት ክፍሉን እንዲያነብ አድርግ::
2. ክፍሉን አባዝተህ ለሕዝቡ አድልና በአንድ ወጣት መሪነት በአንድነት አንብቡ::

**የመልእክቱ አስተዋጽኦ**

**ጊዜው አሁን ነው**
***መክብብ 3:1-11***

**መግቢያ:** ብዙ ሰዎች በአዲስ ዓመት መጀመሪያ ላይ ዕቅዶችን ያወጣሉ:: የአዲስ ዓመት ዕቅዶችን ማውጣቱ ምንም ክፋት የለውም:: ይህ አንድ ሰው ሕይወቱን ለማሻሻል መፈለጉን የሚያመለክት ጤናማ እርምጃ ነው:: ነገር ግን ሕይወት አንዳንድ ጊዜ እኛ እንደምንፈልገው ቀላል ሆና አትገኝም:: ለዚህም ነው ብዙ የአዲስ ዓመት ዕቅዶች ከወሬ የማያልፉት::
በሰባኪነቱ የምናውቀው የመጽሐፈ መክብብ ጸሐፊ የሕይወትን ውስብስብ ባሕርይ ተገንዝቦ ነበር:: ስለሆነም፣ ከመክብብ ምዕራፍ 3 ውስጥ የምናገኛቸው ጠቃሚ አሳቦች ዓመቱን ፍሬያማ በሆነ መልኩ እንድንጠቀም ሊያግዙን ይችላሉ::

1. **አንዳንድ ሊለወጡ የማይችሉ ነገሮች አሉ::**
   **ሀ. ሰባኪው፣ «ለሁሉ ዘመን አለው፣ ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው::» (መክብብ 3:1) በማለት ጽፏል::**

ለ. ይህ የእግዚአብሔርን ሉአላዊነት መቀበሉን ያሳያል:: እግዚአብሔር ለነገሮች ሥርዓትን ስላበጀ፣ ይህንኑ ማክበር ኃላፊነታችን ይሆናል::
ሐ. ሊለወጥ የማይችለውን ለመለወጥ መጣር ውድ ጊዜያችንንና ጉልበታችንን ከማባከን ያለፈ ፋይዳ የለውም::
መ. አደጋ:: አብዛኞቹ ነገሮች ሊለወጡ የማይችሉ መሆናቸው እውነት ቢሆንም፣ የራሳችንን ኃላፊነት መዘንጋት የለብንም:: የራሱን ኃላፊነት ለመወጣት የማይፈልግ ሰው ሁሉም ነገሮች በእግዚአብሔር ስለታዘዙ የኔ አኗኗር ወይም አሠራር የሚያስከትለው ለውጥ አይኖርም ብሎ ያስባል:: የሚሆን ይሆናል:: የማይሆን አይሆንም ባይ ነው::

2. አንዳንድ ሊለወጡ የሚችሉ ነገሮች አሉ::
ሀ. ሲ.ደብልዩ. ኬይል ከእግዚአብሔር ሉአላዊነት ጋር ተያይዞ የሰውም ኃላፊነት መኖሩን መገንዘብ አለብን ሲሉ ጽፈዋል:: ይህ እውነት ነው:: አንዳንድ ነገሮች ሊለወጡ አይችሉም:: አንዳንዶቹ ግን ሊለወጡ ይችላሉ:: ስለሆነም፣ ኃላፊነታችንን እየተወጣን ልንኖር ይገባል::
ለ. ምናልባት እንደ ኃዘን፣ በሽታ፣ ሥቃይ፣ መከራና ሞት ያሉትን ነገሮች ልንለውጥ አንችልም ይሆናል:: ነገር ግን በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ውስጥ እርምጃ መውሰድ የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ:: «ለማነጽ- - - ድንጋዮችን ለመሰብሰብ. . . ለመተቃቀፍ. . . ለመፈለግ. . . ለመናገር. . .ለማፍቀር ጊዜ አለ» እነዚህን ነገሮች የማከናወን ኃላፊነት አለብን::

3. የእግዚአብሔር ሕዝብ ተግባሩን የሚያከናውንበት ጊዜ አሁን ነው::
ሀ. ሰባኪው፣ «ለመፈለግ ጊዜ አለ» ብሏል:: ጊዜው አሁን ነው:: የጠፉትን ሰዎች የምንፈልግ ቤተክርስቲያን መሆን አለብን:: የጠፉትን የማትፈልግ ቤተክርስቲያን የህልውናዋን ምክንያት ዘንግታለች ማለት ነው:: ጆርጅ ደብልዩ ፒተርስ፣ «ዓለም ክርስቲያኖች ወንጌሉን ሊሰጡ ከሚችሉት በላይ ለመቀበል ተዘጋጅቷል» ብለዋል:: ጊዜው አሁን ነው!
ለ. ሰባኪው በተጨማሪም፣ «ለመናገር ጊዜ አለ» ብሏል:: ቤተክርስቲያናችን በከተማ ውስጥ ብዙም አትታወቅም:: ይህ ማህበረሰብ ማንነታችንንና ተግባራችንን እንዲያውቅ የምንችለውን ጥረት ሁሉ ማድረግ አለብን:: ይህ ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ቀዳሚ አጀንዳ ሊሆን ይገባል:: ጊዜው አሁን ነው
ሐ. ሰባኪው፣ «ለመተቃቀፍ ጊዜ አለ» ብሏል:: ለዚህም ጊዜው አሁን ነው:: ለሰዎች ባዶ ወንበር እያሳየን፣ «ቦታ አለን» ማለት ብቻ ሳይሆን፣ ልባችንን አስፍተን ልንቀበላቸው ይገባል::



ልባችንንና ሕይወታችንን ልንከፍትላቸው ይገባል:: ጊዜው አሁን ነው::
መ. በመጨረሻም ሰባኪው፣ «ለመፋቀር ጊዜ አለ» ብሏል:: ይህ የቅድስና መልእክት ነው:: እግዚአብሔርንና ሰዎችን መውደድ አለብን:: የቤተክርስቲያን የህልውናዋ ምክንያት የቅድስና መልእክት የሆነውን ፍጹም ፍቅር ለማስፋፋት ነው:: «እግዚአብሔርና ጥቂት የተቀደሱ አማኞች ይህንን ሊያደርጉ ይችላሉ::» ጊዜው አሁን ነው::

ማጠቃለያ: ይህንን ሁሉ እንዴት ተግባራዊ ልናደርግ እንችላለን? ማነሳሻችን ምን ሊሆን ይገባል? እርሱ ዘላለማዊነትን በልባችን ውስጥ አኑሯል (ቁ.11):: በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ዘላለማዊ እሴቶች በልባችን ውስጥ ጊዜያዊ ጉዳዮችን ይተካሉ:: የዘላለምን ጨረፍታ ስላገኘን፣ የጠፉትን ልንፈልግ፣ ልናናግር፣ ልናቅፍና ልናፈቅር ይገባል:: የዘላለም ሕይወት ከውስጣችን ስላቆጠቆጠ ለሌሎች ልናካፍለው ይገባል::

- የመዝጊያ እንቅስቃሴ - ለሁሉም ሰው ወረቀት አድልና እግዚአብሔር በመጭው ዓመት በሕይወታቸው ውስጥ እንዲፈጽም የሚፈልጉትን አንድ ነገር እንዲጽፉ ጠይቃቸው::
- የመዝጊያ መዝሙርና ጸሎት

በአእምሯችሁ መታደስ

# ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም

# አትምሰሉ

# ኦፐሬተር፣ ክርስቶስን አገናኘኝ (ጸሎት)

ክበድ ሪዲ

**ጭብጥ- እግዚአብሔር ልጆቹ የጸሎት ሰዎች እንዲሆኑለት ይፈልጋል።**

**ዝግጅት**

1. አራት ወጣቶች በተውኔታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል ውስጥ የተሰጠውን ንባብ እንዲያካሂዱ መድብ።
2. ውይይቱን የሚመሩ አምስት አዋቂዎችን ወይም በሳል ወጣቶችን ምረጥ።
3. ወጣቶች ለመዘመር፡ መባ ለመሰብሰብ፣ ወዘተ. እንዲዘጋጁ አድርግ።

**አስተዋጽኦ**

- ሰላምታና ጸሎት- በወጣቶች የአምልኮ መሪ
- *የመክፈቻ መዝሙር* **ቁ. 472** - «Standing on the promises»
- *መግቢያ* - ይህ የአምልኮ መሪው ቀጥታ በማንበብ፣ በመሸምደድ ወይም በራሱ ቃላት የሚያቀርበው ይሆናል። «Celebration of Discipline» የሚል መጽሐፍ የጻፈው ሪቻርድ ፎስተር ስለ ጸሎት የሚከተለውን ብሏል።

«ጸሎት ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ዳርቻ ያሻግረናል። ይህ አሰሳ ባልተካሄደበት ግዛት ውስጥ የሚካሄድ የመጀመሪያ ምርምር ነው። ጸሎት ወደ ሰብአዊ መንፈስ ጥልቅና ከፍ ያለ ተግባር ያመጣናል። እውነተኛ ጸሎት ሕይወትን ይፈጥራል። ይለውጣልም።» ብዙዎቻችን ጸሎት አስፈላጊ በመሆኑ ጉዳይ ላይ እንስማማለን። እንዲሁም ብዙዎቻችን ይህ መሻሻል የሚገባው የመሰጠታችን አካል እንደሆነ ልንስማማ እንችላለን።

ዛሬ ወጣቶቻችን በጸሎት ጭብጥ ላይ ባተኮረ አምልኮ ላይ በመሪነት ያገለግላሉ። ዓላማቸውም ቤተክርስቲያናችን እግዚአብሔር የሚፈልገውን ያህል የጸሎት ሰዎች የሞሉባት እንድትሆን ማገዝ ነው።

- **ተውኔታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ** - «Sweet Hour of Prayer» የሚለው መዝሙር በካሴት እየተጫወተ ወይም አንድ ዘማሪ ድምፁን ዝቅ አድርጎ እየዘመረ፣ አራት ወጣቶች የሚከተለውን ክፍል እንዲያነቡ አድርግ።

1. **መዝሙር 103**
2. **መዝሙር 51**
3. **ያዕቆብ 5:13-18**



4. ማቴዎስ 6:5-13 ጉባኤው በአባታችን ሆይ ጸሎት ላይ አብሮህ እንዲያነብ ጠይቅ።

- **ልዩ መዝሙር** - ጸሎትን የሚያጎላ መዝሙር ወጣት መዘምራን ወይም ዘማሪ እንዲዘምሩ አድርግ።
- **የመባ ጊዜ መዝሙር በወጣት ዘማሪ።**
- **የመልእክቱ አስተዋጽኦ**

## ኦፐሬተር፣ ክርስቶስን አገናኘኝ

*መግቢያ*: አልጋ በሚያከራይ ሆቴል ውስጥ አድራችሁ ታውቃላችሁ? በተለይ በታላላቅ ሆቴሎች ውስጥ ካደራችሁ ስልክ አንሥታችሁ በመደወል የምትፈልጉት ምግብም ሆነ መጠጥ ወደላችሁበት ክፍል እንዲመጣ ማዘዝ ትችላላችሁ።

አንዳንድ ክርስቲያኖች ስለ ጸሎት የሚያስቡት እንደዚህ ነው። እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን ደወል ሲያቃጭል እየሮጠ የሚመጣ መለኮታዊ መልእክተኛ አድርገው ቀርጸውታል። ለነሱ ጸሎት እንደ የአልጋ ክፍል አገልግሎት ነው። ስልክ ደውለህ የምትፈልገውን ሁሉ ማግኘት። ጸሎት ብዙ ነገሮችን ቢያካትትም፣ ይህ የጸሎት አካል እንዳልሆነ እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን።

ጸሎትን ማካሄድ የሚቻልበት ተገቢ መንገድ አለ። በማደግ ላይ እንደሚገኙ በሳል ክርስቲያኖች ቀላል የጸሎት ማካሄጃ ሂደት መከተል እንዳለብን አምናለሁ። ዛሬ ትርጉም ያለው የጸሎት ሕይወት ለማሳደግ በምታደርጉት ጥረት ውስጥ ጠቃሚ አስተዋጽኦ ሊያበረክትላችሁ የሚችል ቀላል መምሪያ እንመለከታለን።

1. **ትርጉም ያለው ጸሎት ከውዳሴ መጀመር አለበት።**

ሀ. ውዳሴ ማለት እግዚአብሔርን ማምለክና ማመስገን ነው

ለ. እግዚአብሔርን ለምን እናመሰግነዋለን?

1. 1ኛ ዮሐንስ 4:10 - «ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተሰረያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም።» መዳናችንን እንደ ቀላል ነገር መቁጠር የለብንም።
2. የግል ደህንነታችን ራሱ በቂ ምክንያት ነው።
3. እግዚአብሔርን ማመስገን ለእግዚአብሔር ያለህን ባለውለታነት የምትገልጽበት ከሁሉም የተሻለ መንገድ ነው (ፊልጵስዮስ 4:6)

2. **ጸሎት ኑዛዜን ማካተት አለበት።**

ሀ. ኑዛዜ ባለማቋረጥ በእግዚአብሔር ላይ መደገፋችንን ያሳያል።

ለ. ኑዛዜ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድነው?

1. ኢሳይያስ 59:1-2

2. ያልተናዘዝነው ኃጢአት በሕይወታችን ውስጥ ካለ ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ልናደርግ አንችልም። እውነተኛ ኑዛዜ ድክመታችንንና ውድቀታችንን ለማመን መፍቀድ ነው።
   3. ውጤቱ - 1ኛ ዮሐንስ 1:9
   4. ስለ ኑዛዜ አንድ የመጨረሻ ምልከታ፡ የተፈጠሩትን ስሕተቶች ለማረም መጸለዩ ጠቃሚ ቢሆንም አስቀድሞ መጸለዩ ብዙ ስሕተቶችን ከመፈጸም ያድነናል (የመከላከያ መድኃኒት)

3. ጸሎት ምስጋናን ማካተት አለበት።

ሀ.እግዚአብሔርን ማመስገን ያለብን ምን ያህል ጊዜ ነው? (ዕብራውያን 13:15)

ለ. ለምን? (1ኛ ተሰሎንቄ 5:18)

ሐ. ብዙዎቻችን ለቀላል የሕይወት በረከቶች እግዚአብሔርን እምብዛም እናመሰግንም። ለዚህ አንዱ ምክንያት ብዙ ነገር የሌለን መሆናችን ሊሆን ይችላል። ሌላው ምክንያት ብዙ ነገር መልመዳችን ሊሆን ይችላል። የሕይወት መልካም ነገሮች ሁሉ የኛ ሊሆኑ ይገባል ብለን እናስባለን። ሌላው ማመስገን ክብራችንን የሚነካ ሆኖ መታየቱ ነው። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንደሚሰጠን እምነን ለመቀበል እንፈልግም። እኛ የንብረቱ አስተዳዳሪዎች ብቻ ነን። አመስጋኝነት ትሕትናንና በእግዚአብሔር ላይ እምነት መጣልን ይጠይቃል። እነዚህ አመለካከቶች ካሉን፣ እግዚአብሔርን የምናመሰግን ሰዎች ልንሆን እንችላለን።

መ. አመስጋኝነት በሕይወታችን ውስጥ ኃይልን ይጨምራል።

4. በመጨረሻም፣ ጸሎት ምልጃን ማካተት አለበት።

ሀ. ምልጃ፣
   1. ቆላስይስ 1:9 የምልጃ ምሳሌ ነው።
   2. ብዙውን ጊዜ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለመምራት የምናደርገው ጥረት ከንቱ ሆኖ ይቀራል። ለዚህም ምክንያቱ ለነሱ ለመጸለይ መዘንጋታችን ነው። መለኮታዊው ቅደምተከተል ስለ ሰዎች ለእግዚአብሔር መናገርና ከዚያም ስለ እግዚአብሔር ለሰዎች መናገር ነው።

ለ. ምልጃ ልመናን ይጨምራል።
   1. የልመና ጸሎት መለወጥ አለባቸው ብላችሁ የምታምኗቸውን ሁኔታዎችና ችግሮች የሚመለከቱ ናቸው።



   2. ክርስቶስ ስለነዚህ ጸሎቶች በማርቆስ 11:24 ላይ የተናገረው አሳብ አለ።
   3. እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ልመናዎቻችንን አይመልስም። ለምን? ለዚህ ምክንያቶቹ ጸሎቶቻችን ማስተዋል የጎደለባቸው ወይም በተቀላቀለ አሳብ የተጸለዩ መሆናቸው ሊሆን ይችላል (ያዕቆብ 1:5-8፣ 4:1-3)።
   4. ልባችንን በጥንቃቄ መመርመር አለብን።
   5. ምሳሌ - 2ኛ ቆሮንቶስ 12:7-10። እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ያውቃል።

ማጠቃለያ፡

1. የጸሎት ሰዎች ልንሆን ይገባል። ጸሎትን በሥራ፣ በማሰብ፣ በመመልከት፣ በመሠቃየት ወይም በመስጠት ልንተካው አንችልም። ጸሎት ለሌሎች ጥረቶች ሁሉ ድጋፍ ሰጭ ነው።
2. የጸሎት ምሳሌ - የኔ ፈቃድ ሳይሆን ያንተ ፈቃድ ይፈጸም።

- መዝሙር - «Not My Will, but Thine»
- በጸሎት ፈጽም

# የወጣቶች

# ስብሰባዎች

(ጉባኤዎች)
(Youth Rallies)



## እንደገና መጀመር

ከጌሪ ሲቨውራይት

ዓላማ ቀደም ሲል እግዚአብሔርን የበደሉት ወጣቶች እንደገና የሚጀምሩበትን ዕድል ለመስጠት

ተስማሚ ጊዜ ይህ የወጣቶች ጉባኤ በየትኛውም የዓመቱ ወቅት ሊካሄድ ይችላል። ነገር ግን ገና ሲደርስ ሲል (በአውሮፓውያን የአዲስ ዓመት ወቅት) ቢካሄድ የተሻለ ይሆናል።

ዝግጅት

1. ስለ ጉባኤው ማስታወቂያ ተናገር
2. ጉባኤው ከመካሄዱ ከአንድ ሳምንት በፊት የሚከተሉትን የቡድን ውድድር ዝርዝሮች አስታውቅ።

ሀ. «የቁንጅና ውድድር» (ይህንን ለማድረግ ከመረጥህ)

ለ. በጉባኤው ላይ ለሚገኙና እንግዶችን ይዘው ለሚመጡት ነጥቦች ይሰጣሉ። (ለምሳሌ፣ ለእያንዳንዱ የቡድን አባል 100 ነጥቦች፣ ጠቅላላው ቡድን ከተገኘ 1000 ተጨማሪ ነጥቦች፣ ለእያንዳንዱ ቡድን 300 ነጥቦች።)

3. ድራማ የሚያዘጋጅ አንድ አዋቂና አንድ ወጣት ምረጥ።

«ውድድር» የሚለውን የድራማ ጽሑፍ በተቻለ መጠን ቀደም ብለህ ስጣቸው። ልጁ ትልቅ ጫማ፣ ካፖርት፣ ባርኔጣና ስካርፍ ያደረገ ሲሆን፣ ከአንገቱ ላይ ትልቅ ድንጋይ ታስሯል።

4. ዕብራውያን 12፡1ን አንብብ።
5. ወጣቶቹ አዝናኝ ምሽት እንዲኖራቸውና በሕይወታቸው እግዚአብሔርን ከሁሉም ለማስቀደም እንዲበረታቱ ጸልይ።

የቡድን እንቅስቃሴዎች፡ ጉባኤውን ለመጀመር ለሚከተሉት ጨዋታዎች አንዱን ወይም ሁሉንም ተጠቀም።

1. የቁንጅና ውድድር። እያንዳንዱ ቡድን የሚወክለው አንድ ልጅ እንዲመርጥ አድርግ። የቡድን መሪው የተመረጡትን ልጆች ከክፍሉ ውጭ ይዟቸው ይሄዳል። ከዚያም ነጭ አንሶላ በመርፌ ቁልፍ በማያያዝ እንደ ቁምጣ ሱሪ አሽርጦ ያለብሳቸዋል። በመቀጠልም ወደ ክፍሉ ተመልሰው በተመልካቾች ፊት በየተራ እንዲያልፉ ያደርጋል። ነጥብ የሚሰጣቸው በሚከተሉት መሥፈርቶች አማካኝነት ይሆናል። ለዓይን የሚማርክ ምርጥ ልጅ፣ ምርጥ ጨዋኺና ምርጥ ተናጋሪ። የዳኞች ቡድን ከ1ኛ እስከ 3ኛ ድረስ የወጡትን እንዲያስታውቅ አድርግ።
2. በአንድ እግር እየዘለሉ መሮጥ። ቡድኖቹ በአንድ እግራቸው ከክፍሉ አንደኛ ጥግ እስከ ሌላኛው ድረስ እየዘለሉ እንዲሄዱ ንገራቸው። ከጥጉ ላይ ሲደርሱ የግራና የቀኝ እግር ጫማዎቻቸውን አውልቀው ይቀያይራሉ። ከዚያም ቅድም

በዘለሉበት ሳይሆን በሌላኛው እግራቸው እየዘለሉ ወደ ተቃራኒው ጥግ ይመለሳሉ። ቀድሞ የደረሰ ቡድን አሸናፊ ይሆናል።

3. ጓደኞችህን ምን ያህል በሚገባ ታውቃቸዋለህ? እያንዳንዱ ወጣት አንድ ጓደኛ እንዲመርጥ አድርግ። ከጓደኛቸው የሚፈልጉትን መረጃ እንዲጠይቁ ሦስት ደቂቃዎች ስጣቸው። ሦስት ደቂቃዎች ሲጠናቀቁ ከጓደኞቻቸው ጋር ጀርባ ለጀርባ ተሰጣጥተው ይቀመጣሉ (እንዳይተያዩ)። ወረቀትና እርሳስ በማደል ስለ ጓደኞቻቸው የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ጠይቃቸው። አብዛኞዎቹን ጥያቄዎች በትክክል የሚመልስ ወጣት አሸናፊ ይሆናል።

ጥያቄዎቹም የሚከተሉት ናቸው። 1/ የጓደኛህ ጫማ በክር የታሰረ ነው ወይስ ሌላ ዓይነት ማያያዣ አለው? 2/ የጓደኛህን የልብስ ቀለሞች ተናገር። 3/ ጓደኛህ ሰዓት አድርጓል?

4. ብርቱካን ማስተላለፍ። ለእያንዳንዱ ቡድን አንድ ብርቱካን አድል። ቡድኖቹ በሰልፍ መቆም አለባቸው። ከሰልፉ መጀመሪያ ላይ ላለው ሰው አንድ ብርቱካን ስጠው። ግለሰቡ ብርቱካኑን ከአገጩ ሥር አድርጎ ይቆይና ምልክት በሚሰጠው ሰዓት ለቀጣዩ ሰው እጁን ወይም ክንዱን ሳይጠቀም ያስተላልፋል። ብርቱካኑ ከአገጭ ወደ አገጭ እየተላለፈ ሰልፉን አዳርሶ መመለስ አለበት። አንድ ቡድን ብርቱካኑን ከጣለ ወይም በእጁና በክንዱ ከነካ፣ ከእንደገና መጀመር አለበት። ቀድሞ የጨረሰ ቡድን ነጥብ ያገኛል።

5. ቀይና አረንጓዴ መብራት። ሁሉም ሰው ወደ መሪው ፊቱን አዙሮ ይቆማል። መሪው ፊቱን አዙሮ፣ «አረንጓዴ መብራት» ይላል። ይህን በሚልበት ጊዜ ሁሉም ሰው ወደ ፍጻሜው መስመር ለመድረስ መንቀሳቀስ አለበት።። «ቀይ መብራት» በሚልበት ጊዜ ሁሉም ሰው በያለበት ይቆማል። መሪው በፍጥነት ፊቱን አዙሮ ሲመለከት በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ሰውካየ እንደገና እንዲጀምር ይነግረዋል። የቡድን መሪው «አረንጓዴ ጠብ፣ አረንጓዴ ንክሻ- - -» እያለ ቡድኖቹን ሊያሳስት ይችላል። ቀድሞ ለጨረሰ ቡድን ነጥብ ስጠው።

ሽግግር፡ እነዚህ ጨዋታዎች የተዘጋጁትን ከጨዋታዎቹ ወደ መልእክቱ ለመሸጋገር እንዲያግዙ ታስበው ነው።

1. የውድድሮቹ አሸናፊዎች እነማን እንደሆኑ በመግለጽ ለቡድኖቹ ነጥቦችን ስጥ። የነጥቦቹን ድምር አሳውቅ።
2. የቡድን ዝማሬ።
3. ድራማ «ውድድር»። ወጣት ልጅና አዋቂ የስፖርት አሰልጣኝ ይገባሉ። ልጁ ካፖርትና ቦት ጫማ አድርጓል። አዋቂው ሰውዬ የስፖርት ልብስ ለብሷል።

አሠልጣኝ፡ ማርሴሊኖ፣ ስለ ውድድሩ ምን ይሰማሃል?



ማርሴሊኖ፡ የበላይነት ይሰማኛል፣ ውድ አሠልጣኝ እንደዚህ ታላቅ ስሜት ተሰምቶኝ አያውቅም።
አሠልጣኝ፡ የምትችለውን ሁሉ ለማድረግ ቆርጠሃላ?
ማርሴሊኖ፡ አዎ።
አሠልጣኝ፡ እንግዲያው ይኼን ቦት ጫማህን አውልቀው። ፍጥነትህን ሊቀንስብህ ይችላል።
ማርሴሊኖ፡ እሺ (ጫማውን ያወልቃል)
አሠልጣኝ፡ በዚያው ባርኔጣህንና ስካርፍህንም ብታወልቅ መልካም ነው።
ማርሴሊኖ፡ እርግጠኛ ነዎት?
አሠልጣኝ፡ አዎ። አሁን ሊጠሩህ እየተዘጋጁ ናቸው። የነገርሁህን ሁሉ አስታውስ። ከኔ በቀር ሌላ ሰው የሚልህን እንዳትሰማ ተጠንቀቅ። ውድድርህን አከናውን። አሁን ካፖርትህን አውልቅና ጥረትህን ቀጥል። (ማርሴሊኖ ካፖርቱን ሲያውልቅ ከአንገቱ ዙሪያ ያለው ድንጋይ ይታያል።)
ማርሴሊኖ፡ እሺ፣ አሁን ዝግጁ ነኝ።
የውድድሩ አስጀማሪ፡ ተዘጋጅ- - -
አሠልጣኝ፡ ቆየኝ፣ቆየኝ፣ አንዴ ቆየኝ፣ ማርሴሊኖ ከአንገት ላይ ያለው እሱ ምንድነው?
ማርሴሊኖ፡ እሱማ «የገድ ድንጋዬ» ነው።
አሠልጣኝ፡ አውርደው!
ማርሴሊኖ፡ ግን፣ አሠልጣኝ - - -
አሠልጣኝ፡ አውርደው ብዬሃለሁ አውርደው! ድንጋይ አንገትህን እየደቆሰ እንዴት አድርገህ ልትሮጥ ነው። ቶሎ ብለህ አንጣው።
ማርሴሊኖ፡ ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ። ግን የገድ ድንጋዬ ከሌለ ድፍረት አይሰማኝም።
አሠልጣኝ፡ የገድ ድንጋይ፣ ከዚህ በፊት ሁልጊዜም ይህን ድንጋይ እንጠልጥለህ ነበር የምትሮጠው ማለት ነው?
ማርሴሊኖ፡ እሱማ፣ አዎ... ግን ለምን?
አሠልጣኝ፡ ምክንያቱማ ፍጥነትህን ይቀንሰዋል! ባለፉት ሦስት ዓመታት አንድም የሩጫ ውድድር ያልጨረስኸው ለካስ ለዚህ ኖሯል? አሁን ቶሎ እንሥተህ ጣለው!
ማርሴሊኖ፡ እሺ፣ አሠልጣኝ... ድንጋዩን ማንጠልጠል ካልፈቀዱልኝ የገድ ፒያኖዬን እየጎተትሁ መሮጥ እችላለሁ?
መልእክት፡ «እንደገና መጀመር» (ይኼ አስተዋጽኦ ብቻ ነው። መልእክቱን አሟልተህ በራስህ ቃላት አቅርብ።)
እንደ ማርሴሊና የለበሰ ሰው የሩጫ ውድድር ያካሂዳል ማለት አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን በተመሳሳይ መንገድ የክርስትናን ሕይወት ለመኖር የሚሞክሩ አንዳንድ ወጣቶች አሉ። ዕብራውያን 12:1 የሚከበንን ኃጢአት ማስወገድ እንዳለብን ያስገነዝበናል።

ስለሆነም፣ ማርሴሊኖ የተለየ ሰው ነው ብለህ ከማሰብህ በፊት፣ የሚከተለውን አጢን። ሁላችንም የየራሳችን «የገድ ድንጋዮች» ነበሩን። እነዚህም የደህንነት ስሜት ይሰጡናል ብለን የተደገፍንባቸው ነገሮች ናቸው። የበለጠ የሚያሳዝነው ደግሞ የወረወርናቸውን ወይም ለጌታ የተናዘዝናቸውን ነገሮች ተመልሰን ማንሣታችን ነው። እነዚህ ነገሮች ፍጥነታችንን የሚያስቀስሱ ሲሆን፣ አደናቅፈው ሊጥሉንም ይችላሉ። ይህም ሆኖ፣ ማርሴሊኖ እንዳደረገው ተመልሰን እናነሣቸዋለን።

ምናልባትም የሥልጠና ደንቦች ያስፈልጉን ይሆናል። እነዚህም በእምነታችን እንድንፀናና ፈጥነን እንዳንሰናከል የሚያግዙን ደንቦች ናቸው። የዕብራውያን መልእክት እነዚህን ደንቦች ሰጥቶናል።

1. የሚያደናቅፉንን ኃጢአቶች፣ ልማዶችና ግንኙነቶች ማስወገድ (ለእግዚአብሔር መናዘዝ)። ከዚያም ከነዚህ ነገሮች መራቅ።
2. በትዕግሥት መሮጥ - - ሩጫው በአንድ ቀን፣ በአንድ ሳምንት ወይም በሁለት ሳምንታት የሚጠናቀቅ አይደለም። ሩጫው የማራቶን ስለሆነ፣ መዘጋጀትና መሠልጠን አለብን። እንዴት?
   ሀ. እግዚአብሔር ለሕይወትህ የሚሰጠውን ምሪት ለማግኘት መጽሐፍ ቅዱስ አንብብ።
   ለ. ስለ ዕለታዊ የሩጫ ውድድርህ ለእግዚአብሔር ተናገር።
   ሐ. ለሕይወትህ በአሠልጣኙ (በክርስቶስ) ላይ እምነት ጣል።
3. ዓይኖችህን በክርስቶስ ላይ ትከል። ያለፉትን ውድቀቶችና ሽንፈቶች ዞር ብለን በምንመለከትበት ጊዜ፣ ከእምነታችን ለማፈግፈግ እንፈተናለን። ብትሰናከል ወይም ብትሳሳት፣ ስሕተትህን ተቀብለህና ተናዝህ ወደፊት ቀጥል። የትኛውም ስኬታማ ሯጭ መሬት ላይ ቁጭ ብሎ አይተክዝም ወይም ወደ መነሻው መስመር አይመለስም።

ምናልባት እንደ ማርሴሊኖ ከእንገት ላይ ድንጋይ አንጠልጥለህ ይሆናል። ምናልባትም ያንተ ድንጋይ ውድቀት፣ የባሕርይ ችግር፣ ወይም ሩጫህን እንዳትቀጥል የሚከለክል ኃጢአት ሊሆን ይችላል። ይህም ሆኖ፣ ከእንደገና ልትጀምር ትችላለህ። እንደገና መጀመር የሚያስፈልጋቸው በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ያላደጉ - - በሥልጠና ላይ ያልሆኑ ለሩጫው የሚገባቸውን ያህል ትኩረት ያልሰጡ ሰዎች ናቸው። ስለሆነም፣ እንደገና መጀመር ይኖርብሃል። ዝም ብለህ ወደዚህ የጸሎት ስፍራ ናና ውድቀትህን፣ የባሕርይ ችግርህን ወይም ኃጢአትህን ለእግዚአብሔር ተናዘዝ። ድንጋዩን ጣለው። እግዚአብሔር ይቅር እንደሚልህና ሩጫውን ከእንደገና እንደሚያስጀምርህ እመን። (የጸሎት) ግብዣ በማድረግ ስብሰባውን ፈጽም። «የጌታን መንገድ እከተላለሁ - - ወደ ኋላ አልመለስም» የሚለውን ዓይነት የግብዣ አዝማች ዘምሩ።) ከጸሎት በኋላ፣ ጉባኤውን ፈጽም።



# አዳዲስ ጨርቆች፣ አዲስ ዳሰሳ
ከሱዚ ሽለንበርገር

**ዓላማ** ወጣቶች ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው እንዲያምኑና «ፍጹም አዲስ በሆነ መንገድ ይዳስሳቸው ዘንድ» እንዲፈቅድለት ለማበረታታት።

**ተስማሚ የጉባኤው ወቅት** ይህ የወጣቶች ስብሰባ በየትኛውም ወቅት ሊካሄድ ይችላል። ነገር ግን ወጣቶች ከቤት ውጭ የሚካሄድ ጨዋታ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ለማስቻል በበጋ ወራት ቢካሄድ የበለጠ ጠቃሚ ይሆናል።

**ዝግጅት**

1. ከጉባኤው አንድ ሳምንት አስቀድመህ ሁሉም ወጣቶች ጨርቅ ይዘው እንዲመጡ አስታውቅ።
2. የማይቀሩና እንግዶችን የሚያመጡ ቡድኖች ነጥቦችን ያገኛሉ።
3. የኢሳይያስ 43:19፣ 25፣44:21-22፣45:4-5 እሳቦችን ቀረብ ብለህ ተረዳ።

**የቡድን ጨዋታዎች**

የወጣቶቹን ጉባኤ ለመጀመር ከሚከተሉት ጨዋታዎች አንዱን ወይም ሁሉንም ተጠቀም።

1. **የጨርቅ መጎተቻ**። እያንዳንዱ ልጅ ያመጣውን ጨርቅ ጫፍ ከልብሱ ጋር ያያይዛል። አንዱ ሰው አባራሪ ሆኖ ይመረጣል። ምልክት በሚሰጥበት ጊዜ ተመራጩ ሌሎቹን ልጆች ያሳድዳል።

አሳዳጁ ፀአንድን ሰው ጨርቅ በሚወስድበት ጊዜ ጨርቁ የተወሰደበት ሰው አሳዳጅ ይሆናል።

አማራጭ፡ ምልክት በምትሰጥበት ጊዜ ሁሉም ቡድኖች የሌላውን ጨርቅ ለመውሰድ እንዲጥሩ አድርግ። ከሦስት ደቂቃዎች በኋላ ብዙ ጨርቆችን ይዞ የተገኘ ቡድን አሸናፊ ይሆናል።

2. **ጨርቁን መጣል**። ሁሉም ወጣቶች ክብ ሠርተው ይቆማሉ። አንድ ሰው ይመረጥና ጨርቅ ይዞ ከክቡ ውጭ ይዞራል። ጨርቁን ከአንድ ሰው ኋላ ይጥልና ይሮጣል። ጨርቁ የተጣለበት ሰው ያባረዋል። የመጀመሪያው ግለሰብ ሩጦ ከቦታው ሲገባ፣ ጨርቁን የያዘው ግለሰብ ክቡን ሲዞር ቆይቶ ጨርቁን ከአንድ ሰው ኋላ ይጥላል።
3. **የጨርቅ ፋሺን**። ወጣቶቹ በቡድናቸው እንዲሰባሰቡ ንገራቸው። በ10 ደቂቃዎች ውስጥ ለአንድ አባላቸው «የጨርቅ ፋሺን» እንዲሠሩ ንገራቸው። የሁላቸውንም ጨርቆች ሰብስበው ከአባሎቻቸው ለአንዱ ባርኔጣ ወይም ሌላ ዓይነት የፋሺን ልብስ ይሠራሉ። ለእያንዳንዱ ቡድን መቀስ፣ የጨርቅ ማያያዣ፣ ወዘተ. ማዘጋጀት ይኖርብሃል። ከ10 ደቂቃዎች በኋላ የያንዳንዱ

ቡድን ሞዴል የፋሺን ልብሱን ለብሶ ከመድረኩ ላይ እንዲንዝ አድርግ። የዳኞች ቡድን የማን ፈጠራ እንደሚልቅ ይወስናል።

ሽግግር

የምትፈልጋቸውን ያህል ጨዋታዎች ምረጥ። እነዚህ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ከሚታይባቸው የቡድን ጨዋታዎች ወደ መልእክቱ ለመሸጋገር የሚያግዙህ ናቸው።

1. የያንዳንዱ የቡድን ውድድር አሸናፊዎች እነማን እንደሆኑ በመግለጽ የተሻሻለውን የቡድን አጠቃላይ ነጥብ ግለጽ። ይህን ጊዜ ቀጣዮችን አጠቃላይ ክስተቶችም ለማስተዋወቅ ተጠቀም።
2. መባ በሚሰበሰብበት ጊዜ አንድ ወጣት በመሣሪያ ወይም በድምፅ እንዲዘምር አድርግ።
3. የቡድን ዝማሬ።
4. በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኝ ሽምግል ያለ ሰው ለወጣቶች አጭር ምስክርነት እንዲሰጥ አድርግ። ወይም ከክርስቶስ ጋር ስለነበረው መንፈሳዊ ጉዞና እንዴት ወደ ክርስቶስ ሊመጣ እንደቻለ ቃለመጠይቅ አድርግለት። ይህም ወጣቶች በሳል መንፈሳዊ ሕይወት ከሚመሩ አዋቂዎች ጋር እንዲተዋወቁ ያስችላል።
5. የቡድን ውይይት በአነስተኛ ቡድኖች በመከፋፈል ወይም በአንድ ላይ ልታወያያቸው ትችላለህ። ለቡድኑ የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብብላቸው ወይም አያሌ ወጣቶች በየተራ እንዲያነቡ ጠይቃቸው።

ኢሳይያስ 43:19 «እነሆ፣ አዲስ ነገርን አደርጋለሁ እርሱም አሁን ይበቅላል፤እናንተም አታውቁትምን? በምድረ በዳም መንገድን በበረሃም ወንዞችን አደርጋለሁ።»

ቁጥር 25. *«መተላለፍህን፦ ስለ እኔ ስል የምደመስስ እኔ ነኝ ኃጢአትህንም አላስብም።»*

ምዕራፍ 45:4-5 *«ስለ ባሪያዬ ስለ ያዕቆብ፣ ስለ መረጥሁትም ስለ እስራኤል ብዬ በስምህ ጠርቼሃለሁ በቅጽምጫ ስምህ ጠራሁህ፣ አንተ ግን አላወቅኸኝም። እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔም ሌላ ማንም የለም ከእኔም በቀር አምላክ የለም»*

የመወያያ ጥያቄዎች

- እግዚአብሔር ሕይወታችንን በሰጠነው ጊዜ «አዲስን ነገር እንደሚያደርግ» ሲናገር ምን ማለቱ ነው።
- እግዚአብሔር ሕይወታችንን ለርሱ ሳንሰጠው በፊት ሳይቀር እያንዳንዳችንን በየስማችን መጥራቱ ስለ ባሕርዩ ምን ያሳያል?
- በሕይወትህ ፍጹም አዲስ ዳሰሳ እንደሚያስፈልግህ ያሰብህበትን ጊዜ አስታውሰህ አብራራ።



- ፍጹም አዲስ ዳሰሳ ሊገኝ የሚችለው ከእግዚአብሔር ብቻ ሆኖ ሳለ! ሰዎች አዲስነትን የሚፈልጉባቸው ምንጮች ምን ምንድናቸው?
- ፍጹም አዲስነት የሚያስፈልገው ለዓላማውያን ብቻ ነው ወይስ አንዳንዴ ለክርስቲያኖችም ጭምር?

7. ጸሎት ከአዋቂ አገልጋዮች አንዱ ቡድኑን በጸሎት እንዲመራ አድርግ። ከመልእክቱ በፊት አንድ ወጣት ልዩ መዝሙር እንዲያቀርብ ልታደርግ ትችላለህ።

**መልእክት «አዳዲስ ጨርቆች፣ አዲስ ዳሰሳ»**

*(በአገልግሎቱ መጨረሻ ላይ የምትጠቀምበት አዲስ ጨርቅ መድረኩ ላይ በጠረጴዛ ላይ መቀመጥ አለበት።)*

ዓርብ ዕለት ጎህ ሳይቀድ አንድ መልከ መልካም ጠንካራ ወጣት በከተማችን መንገድ ላይ ሲያልፍ አየሁት። ወጣቱ አዳዲስና ደማቅ ልብሶች የተጫኑበትን አሮጌ ሰረገላ እየነዳ ጥርት ባለ ውብ ድምፅ! «ጨርቅ ያለው! ጨርቅ ያለው!» ሲል ይጣራል። ጣፋጭ ሙዚቃ የሚመስል ድምፁ ቆሻሻውን አየርና ደብዛዛውን ብርሃን እያቋረጠ ያልፋል።

«አሮጌ ጨርቆችን በአዲስ የሚለውጥ! የነተቡ ልብሶቻችሁን እወስዳለሁ።»

«ይህ የሚገርም ነገር ነው» ስል አሰብሁ። ወጣቱ ሁለት ሜትር ያህል የሚረዝም ሲሆን፣ ክንዶቹ እንደ ዛፍ ግንዶች የጠነከሩ ነበሩ። ዓይኖቹ አስተዋይነትን ይረጫሉ። ይኼ ወጣት ጨርቅ ከማዞር የተሻለ ሥራ ሊያገኝ አይችልም ኖሯልን? ስል ተደነቅሁ።

በጉጉት ተነድቼ ተከተልሁት። እናም አስገራሚ ነገር ለማየት ቻልሁ ወዲያውም የጨርቅ አሿሪው ከቤቷ ጓሮ የተቀመጠች ሴት ተመለከተ። ሴትዮዋ ከዓይኖቿ መንታ መንታ እየሆኑ የሚወርዱትን እንባዎች በመሐረቧ እየተቀበለች ነበር። እጆቿና እግሮቿ በኃዘን ተኮራምተዋል። ትከሻዎቿ ይንቀጠቀጣሉ። ልቧ ተሰብሯል።

የጨርቅ አሿሪው ሰረገላውን አስቆመው። ከዚያም በአሮጌ ጣሳዎች፣ አሻንጉሊቶችና የልጆች የሽንት ጨርቆች መካከል እየተራመደ ወደ ሴቲቱ አመራ። በለሆሳስ ድምፅ፣ «ጨርቅሽን ስጭኝ» እኔ ሌላ እሰጥሻለሁ። አላት።

ከዓይኖቿ ላይ መሐረቧን አነሣው። ወደ ላይ ቀና ብላ ስትመለከት፣ የሚያብረቀርቅ የሐር ጨርቅ ከእጇ መዳፍ ላይ አስቀመጠላት። ዓይኖቿ ከስጦታው ወደ ሰጭው ተወረወሩ።

የጨርቅ አሿሪው ሰረገላውን መንዳት ሲጀምር አንድ እንግዳ ነገር አደረገ። እንባ የጠገበ መሐረቧን ከዓይኖቹ ላይ በማድረግ ልክ

እንደሷው ማንባት ጀመረ። ትከሻዎቹ ተንቀጠቀጡ። የሴቲቱ ዓይኖች ግን እንባ ርቆት ጥርት አለ።
«ይገርማል» ስል በሰፊው ተነፈስሁ። ከዚያም አንድ የሚያጓጓ ነገር እንዳየ ልጅ አልቃሻውን የጨርቅ አሿሪ ተከትዬ ሄድሁ።
«ጨርቆች! ጨርቆች አሮጌ ጨርቆችን በአዲስ የሚለውጥ!»
ሰማዩ ግራጫ መስሏል። ጥቋቁር መስኮቶች ባሏቸው ትናንሽ ድንኩዋኖች ውስጥ የጨርቅ አሿሪው ራሷ ቆስሎ በጨርቅ የታሰረላትን ልጅ ሲያነጋግር አየሁት። ከራሷ ላይ የታሰረው ጨርቅ ደም እምቋል። ከራሷ የመነጨው ደም ከጉንጯ ላይ እየፈሰሰ ይወርዳል።
ረዥሙ የጨርቅ አሿሪ ልጅቱን በኃዘኔታ አያት። ከሰረገላው ውስጥ አንድ ግሩም ቢጫ ባርኔጣ ስቦ አወጣ።
«ጨርቅሽን ስጭኝ። እኔም የኔን እሰጥሻለሁ» አላት።
ልጅቷ ከራሷ ላይ የታሰረውን ጨርቅ ፈቶ ከራሱ ላይ ሲያስር ዝም ብላ ተመለከተችው። ባርኔጣውን ከራሷ ላይ አስቀመጠ። ከማሸጊያ ጨርቁ ጋር ቁስሉ አብሮ ሲተሳሰፍ አይቼ በመገረም ተነፈስሁ። ጥቁር ወፍራም ደም በቅንድቦቹ ላይ እየፈሰሰ ይወርድ ጀመር። የራሱ ደም!
የሚያነባው፣ ጠንካራውና አዋቂው የጨርቅ አሿሪ ደሙን እየዘራ፣ «ጨርቅ ያላችሁ! ጨርቅ ያላችሁ! አሮጌ ጨርቆችን በአዲስ እለውጣለሁ!» እያለ መጓዙን ቀጠለ። ከመቸኮሉ የተነሣ ይመስላል ፍጥነቱን የበለጠ ጨምሯል። የስልክ እንጨት ተደግፎ የቆመ ሰውዬ ሲያጋጥመው፣ «ወደ ሥራ እየሄድህ ነው?» ሲል ጠየቀው። ሰውዬው ራሱን ነቀነቀ።
የጨርቅ አሿሪው፣ «ሥራ አለህ?» ሲል ደግሞ ጠየቀው።
«እብድ ነህ?» ሰውዬው አላገጠበት። ከስልክ እንጨቱ ፈቀቅ ብሎ ሲሄድ ከኪሱ ውስጥ የከተተው የጃኬቱ ቀኝ እጅጌ ታየ። ቀኝ እጅ አልነበረውም።
«ጃኬትህን ስጠኝ። እኔም የራሴን እሰጥሃለሁ» አለ ታላቅ ሥልጣን ባዘለ ድምፅ።
ጃኬቶቻቸውን በተለዋወጡ ጊዜ የተከሰተው ሁኔታ ሰውነቴን ሰቀጠጠው አንድ እጁ ብቻ የነበረው ሰውዬ የጨርቅ አሿሪውን ጃኬት ሲለብስ እንደ ዛፍ ግንድ ያሉ ሁለት እጆችን ታደለ። የጨርቅ አሿሪውም ቀኝ እጁን አጣ።
«ወደ ሥራ ሂድ» አለው።
ከዚያም አንድ ሽማግሌ በስካር ራሱን ስቶ አገኘው። እርጅና፣ ዝለትና ሕመም አጎሳቁለውታል። በስካር ራሱን የሳተው ሽማግሌ የለበሰውን የወታደር ብርድ ልብስ ወሰደ፣ አዳዲስ ልብሶችን ሰጠው። እኔም ተከትዬው መጓዜን ቀጠልሁ። የጨርቅ አሿሪው በኃይል እያለቀሰ፣ ከግንባሩ ደም እየፈለቀ፣ ሰረገላውን በአንድ እጁ እየነዳ፣



በስካር እየተንገዳገደ፣ ድካሙን፣ እርጅናውንና በሽታውን እየተቋቋመ በከፍተኛ ፍጥነት ይነጉዳል። በከተማችን መንገዶች እስከተወሰነ ስፍራ ከመጣ በኋላ ከመጠን በላይ በረረ።
በዚህ ሰውዬ ሕይወት ውስጥ የተከሰተውን ለውጥ ስመለከት አለቀስሁ። ኃዘኑን ማየቱ ጎዳኝ። ነገር ግን በዚህ ከፍተኛ ፍጥነት ወዴት እንደሚሄድ ማወቅ ነበረብኝ። ይህንን እንዲያደርግ ምን እንደገፋፋው ለማወቅ ጭምር ጓጉቼ ነበር። ምስኪኑ ሽማግሌ ወደ ቆሻሻ ጉድጓዶች መጣ። በዚህ ጊዜ ሳግዘው ፈለግሁ። ነገር ግን ወደኋላ ቀረት ብዬ ተደበቅሁ። ወደ አንድ ኮረብታ ወጣ። በዚህ ጊዜ በሰፊው ተነፈሰ። ከዚያም ቁጭ አለ። ራሱን በመሐረቡና በጃኬቱ ላይ አሳረፈ። አጥንቶቹን በወታደር ብርድ ልብስ ሸፈነ። እናም ሞተ።
መሞቱን ሳይ እጅግ አለቀስሁ። በአሮጌው መኪና ውስጥ ገብቼ ተስፋ እንደሌለው ሰው አነባሁ። ምክንያቱም የጨርቅ አሿሪውን ወድጀው ነበር። ይህን ሰውዬ ሳይ ሌላው ሰው ሁሉ ኮስሶብኝ ነበር። ምን ያደርጋል ሞተ። ሳነባ ቆይቼ እንቅልፍ አሸለበኝ።
ከዓርብ ማታ እስከ ቅዳሜ ማታ ድረስ በእንቅልፍ ውስጥ መቆየቴን አላወቅሁም ነበር። እሑድ ጠዋት ግን በኃይለኛ ሽብር ተቀስቅሼ ተነሣሁ።
ጥርት ያለ ኃይለኛ ብርሃን ከፊቴ ላይ በራ። ዓይኖቼን ስከፍት የድንቆች ሁሉ መጀመሪያና መጨረሻ የሆነው ድንቅ አየሁ። የጨርቅ አሿሪው ብርድ ልብሱን አጥፎ ቆሟል። ከግንባሩ ላይ ጠባሳ ይታያል። ግን ሕያው ሆኗል። ጤናማነቱም በግልጽ ይታያል። የእርጅና ወይም የኃዘን ምልክት አይታይበትም። የሰበሰባቸው ጨርቆች በሙሉ ጸድተው ያብረቀርቃሉ።
ያየሁት ሁሉ አስደንቆኝ እየተንቀጠቀጥሁ ራሴን ዝቅ አደረግሁ። ወደ ጨርቅ አሿሪው ቀረብሁ። ከአጠገቡ የቆምሁ ምስኪን ሰው በመሆኔ እያፈርሁ ስሜን ነገርሁት። ከዚያም ልብሶቼን ሁሉ አወለቅሁና ጉጉቴን በሚያሳብቅ ድምፅ፣ «አልብሰኝ» አልሁት።
እርሱም አለበሰኝ። ጌታዬ አዳዲስ ልብሶችን ስላለበሰኝ ከሱ ቀጥዬ እኔም ድንቅ ሆንሁ። ጨርቅ አሿሪው ክርስቶስ!

*ማጠቃለያ*

የጨርቅ አሿሪው የክርስቶስ ምሳሌ ነው። በትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ ፍጹም አዲስ ነገር ለመፍጠር መሻቱን ይገልጻል። በሌላ አገላለጽ፣ ግራ መጋባታችንን፣ የበደለኛነት ስሜታችንንና ዓላማ ቢስነታችንን ወስዶ በደስታ፣ በሰላምና የሕይወት ዓላማ ሊሞላን ይፈልጋል። በምሳሌው ውስጥ ተራኪው ወደ ክርስቶስ በመሄድ አዲስ «ልብስ»፣ አዲስ አኗኗር ወይም አዲስ ጅማሬ ሲጠይቅ አይተናል። ለእግዚአብሔር ሁሉንም ነገር፣ አሮጌ

መንገዶቻችንንና ልማዶቻችንን ለርሱ አሳልፈን ልንሰጥና ሙሉ ለሙሉ በፈቃዱና በባሕርዩ እንደገና እንዲያለብሰን መፍቀድ አለብን። እንዳንዶቻችሁ ክርስቶስን የመከተሉን ውሳኔ አዘግይታችኋል። ዛሬ ጥሩ የጨዋታና የመዝናኛ ጊዜ ብታሳልፉም፣ ጌታን ለመከተል ከልባችሁ አልቆረጣችሁም። ዛሬ የናንተ ጊዜ አሁን ይችላል። እግዚአብሔር ወደናንተ ሕይወት እንዲገባ አሁኑኑ ትፈቅዱላችሁን? ዛሬ በልባችሁ ውስጥ አዲስና አስደሳች ነገር እንዲያደርግ ትፈቅዱለታላችሁ?

እንዳንዶቻችሁ በክርስቶስ ያመናችሁ ብትሆኑም ከርሱ ጋር ባላችሁ ጉዞ መጠነኛ ዘገምተኝነት አሳይታችኋል። የሕይወት ውጥረት ስለበዛባችሁ፣ መጽሐፍ ቅዱሳችሁን አታነቡም። በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት በመንፈሳዊ ሕይወታችሁ አታድጉም። በአጠቃላይ የክርስትናችሁን ደስታ አጥታችኋል። ከምንም ነገር በላይ ዛሬ ፍጹም አዲስ ለውጥ ያስፈልጋችኋል። ዛሬ አንዳንድ ነገሮቻችሁን ለእግዚአብሔር አሳልፋችሁ በመስጠት ይቅርታውን ልትቀበሉና አዲስ ልትሆኑ ትፈልጋላችሁ? ክርስቶስ አሮጌ ጨርቆቻችሁን በአዳዲሶቹ ሊለውጥ ይፈልጋል። በሌላ አገላለጽ፣ አሁኑኑ አዲስ ጅማሬ ሊሰጣችሁ ፈቃደኛ ነው። አዲስ ጅማሬ ለማግኘት ትፈልጋላችሁ? ክርስቶስ አሁኑኑ እንዲለውጣችሁ ፍቀዱለት።

ሁላችሁም ራሶቻችሁን ዝቅ አድርጋችሁ ዓይኖቻችሁን እንድትጨፍኑ እጠይቃለሁ። እያንዳንዳችሁ ትንሽ ጨርቅ ወደ ቤታችሁ በመውሰድ ዘወትር ሊታያችሁ በሚችል ስፍራ ታስቀምጣላችሁ። ይህም ክርስቶስ በናንተ ሕይወት ውስጥ የፈጸመውን አዲስ ለውጥ ያስታውሳችኋል። ጨርቁን ከመውሰዳችሁ በፊት ግን ተንበርክካችሁ በመጸለይ ከእግዚአብሔር ጋር ያላችሁን ግንኙነት መገምገም ይኖርባችኋል። ክርስቶስ ወደ ሕይወታችሁ እንዲመጣ ካልጠየቃችሁ ይህንኑ ለማድረግ ጊዜው አሁን ነው። ክርስቲያኖች ከሆናችሁና ክርስቶስ በአዲስ መንገድ እንዲዳስሳችሁ የምትፈልጉ ከሆነ፣ ለዳሰሳውም ጊዜው አሁን ነው። ጸሎታችሁን ከጨረሳችሁ በኋላ፣ መጥታችሁ ጨርቁን ትወስዱና በጸሎት መንፈስ ትቆያላችሁ። (የምስጋናና የምስክርነት ጸሎት በማቅረብ ፈጽም።)



## የዓሣ አጥማጅ

ከሱዚ ሽለንበርገር

ዓላማ፡ ወጣቶች 1/ የክርስቶስን መንፈስ ለጠፋውና በሞት ላይ ላለው ዓለም እንዲያካፍሉ፣ 2/ መንፈሱን ለማካፈል የተዘጋጁና የታጠቁ ይሆኑ ዘንድ በየዕለቱ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን እንዲመረምሩ ለማበረታታት።

### ዝግጅት

1. ማስታወቂያ መናገር። ከስብሰባው ጥቂት ሳምንታት ቀደም ብለህ የሚከተሉትን ነገሮች አስታውቅ።
   ሀ. የዓሣ ማጥመጃ መሣሪያዎችን ለሚያመጣ ወይም ዓሣን በሚያስመስል መልኩ ለሚለብስ ሰው የአምስት ሺህ ነጥብ (ወይም የፈለግኸውን) ሽልማት እንደምትሰጥ። (ወጣቶች የፈጠራ ጥበብን እንዲጠቀሙ አበረታታቸው። ይኼ በጣም አዝናኝ ሊሆን ይችላል። የትኛውንም ነገር እንዲያመጡ አበረታታቸው። ለምሳሌ ያህል፣ መንጠቆዎችን፣ የዓሣ ሥዕሎችን፣ ትላትሎችን፣ ወዘተ. ሊያመጡ ይችላሉ።)
   ለ. ከአባላቱ አብዛኛዎቹ ከዓሣ ጋር ተዛማጅነት ያለው ነገር ካመጡ ወይም ከለበሱ፣ ቡድናቸው ሃያ አምስት ሺህ ነጥቦችን
   • እንደሚሸለም ተናገር።
   ሐ. የቡድን ውድድር
2. በስብሰባው ላይ የሚገኙና እንግዶችን የሚያመጡ ቡድኖች ይሸለማሉ
3. ትንቢት ዮናስን አጥና።

### የቡድን ተግባራት

ስብሰባውን ለመጀመር ከሚከተሉት እንቅስቃሴዎች አንዱን ወይም ሁሉንም ተጠቀም።

1. መያያዝ። አንድ ሰው ከጓደኛው ጋር አንድ ክንዱን ያያይዛል። ሁሉም ጥንዶች በትልቅ ክብ ዙሪያ ይቆማሉ። ከዚያም አብረው የተያያዙ ሁለት ልጆች ተፈተው ከመሀል ይገባሉ። አንዱ ሌላኛውን ያሳድደዋል። ተሳዳጁ ልጅ አሳዳጁ ሳይዘው በፊት ተያይዘው ከሚገኙ ሌሎች ጥንዶች ጋር ለመጣመር ይጥራል። ከሌላ ቡድን ጋር በሚጣመርበት ጊዜ፣ ሦስተኛ ሆኖ የሚቀረው ልጅ ሌላ ተጣማሪ መፈለግ አለበት። አሳዳጁ ከያዘው ግን ተሳዳጁ ወደ አሳዳጅነት ይቀየራል።
2. አክተፐስ (Octopus)። የጨዋታውን አካባቢ ለይተህ ምልክት አድርግ። አንደኛው ልጅ አክተፐስ (ስምንት እጆች ያሉት አውሬ) ይሆናል። ሁሉም ልጆች በአንድ መስመር ይሰለፋሉ። አክተፐስ

መሀል ላይ ይቆማል። ኦክተፐስ ከአንድ እስከ ሦስት በሚቆጥርበት ጊዜ ሁሉም በኦክተፐስ ሳይነካ ወደ ሌላኛው የሜዳው ጫፍ ሩጠው መሄድ አለባቸው። ኦክተፐስ የነካው ሁሉ የኦክተፐስ ቡድን አባል ይሆንና ሌሎችን በመንካት «ለመማረክ» ይጥራል። ነገር ግን እግሮቻቸውን ማንቀሳቀስ አይችሉም። በተነኩበት ቦታ መቆም አለባቸው። ከአንድ እስከ ሦስት ሲቆጠር፣ ሁሉም እንደገና ወደ ሌላኛው ጫፍ ይሮጣሉ። ኦክተፐስና «እጆቹም» ሊይዟቸው ይሞክራሉ። (የኦክተፐስ «እጆች»እግሮቻቸውን ሊያንቀሳቅሱ እንደማይችሉ አትዘንጋ!) ሁሉም ሰው ተነክቶ እስኪዳረስ ጨዋታው ይቀጥላል።

3. ከሁሉም እንግዳ የሆነ የዓሣ ታሪክ። ወጣቶቹ ጭራሽ የማይመስል የዓሣ ታሪክ እንዲፈጥሩ ንገራቸው። ከአራት ደቂቃዎች በኋላ የእያንዳንዱ ቡድን ተወካዮች የፈጠሩትን ታሪክ ይናገራሉ። ሁሉም ተራኪዎች በአንድ ላይ ወደ መድረኩ እንዲወጡ አድርግ። ምንም እንኳዋን ትረካውን የሚያቀርቡት ተራ በተራ ቢሆንም፣ አንዱ እየተረከ ሌሎቹ ታሪካቸውን ሲያስተካክሉ መቆየት የለባቸውም። ፍጹም እንግዳ የሆነ ታሪክ ለሚናገር ቡድን ብዙ ነጥቦችን ሸልም። ትረካው ከአንድ ደቂቃ በላይ መፍጀት የለበትም።

## ሽግግር

ከቀረቡት እንቅስቃሴዎች የፈለግኸውን ያህል ምረጥ። እነዚህ ከፍተኛ ፍጥነት የሚታይባቸው የቡድን እንቅስቃሴዎች ወደ መልእክቱ የሚደረገውን ሽግግር ለማገዝ የተዘጋጁ ናቸው።

1. ማስታወቂያ። የእያንዳንዱን የቡድን ውድድር አሸናፊዎች ግለጽና የተሻሻለውን የነጥብ ድምር ተናገር። ዓሣን የሚያስመስል ልብስ በመልበሳቸው የበለጠ ነጥብ ያመጡት ሰዎች እነማን እንደሆኑ ተናገር። በዚህ ጊዜ አጠቃላይ ውጤቶችን ግለጽ።
2. መባ። በዚህ ጊዜ ከወጣቶቹ አንዱ በመሣሪያ ብቻ የተቀነባበረ (ኢንስትሩሜንታል) ሙዚቃ እንዲጫወት ልታደርግ ትችላለህ።
3. የቡድን ዝማሬ። «Share with his spirit» ወይም ሌላ ከመልእክቱ ጋር የሚዛመድ መዝሙር ቡድኑን በመምራት አዘምር።
4. የቡድን ውይይት። ወጣቶቹ ብዙ ከሆኑ፣ በአነስተኛ ቡድኖች ከፋፍላቸው። ጥቂት ከሆኑ ግን በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ። «እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፣ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል? ወደ ውጭ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ወደ ፊት ለምንም አይጠቅምም።» ክርስቲያኖች እንደመሆናችን፣ የዓለም ጨው ነን። ክርስቶስ በልባችን ውስጥ ስለሚኖር፣ ለዚህ ጠማማ ዓለም መፍትሔ አለን። ስለሆነም፣ ጨውነታችንን



በአካባቢያችን ላሉት ሰዎች በማካፈል የተቀረውን ዓለም ማጣፈጡ የኛ ድርሻ ነው።

«እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ። በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም። መብራትንም አብርተው ከዕንቅብ በታች አይደለም እንጂ በመቅረዙ ላይ ያኖሩታል በቤት ላሉት ሁሉም ያበራል። መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።» (ማቴዎስ 5:14-16)። የርሱን ብርሃን በዓለማችን ውስጥ ላሉት ሰዎች የማካፈል ተልዕኮ ተሰጥቶናል። እኛ ክርስቲያኖች ብርሃኑን ካላካፈልን ማን ይህንን ሊያደርግ ይችላል?

*የመወያያ ጥያቄዎች*

1. «የምድር ጨው» ማለት ምን ማለት ነው?
2. ጨውነት ከማጣፈጥ ጋር የተያያዘ ከሆነ፣ የጠፋውንና የሚሞተውን ዓለማችንን እንዴት ልናጣፍጥ እንችላለን?
3. «ብርሃናችሁ ይብራ» ማለት ምን ማለት ነው?
4. አንተ እንደ ግለሰብ ብርሃንህን በትምህርት ቤትህ እንዴት ልታበራው ትችላለህ?
5. ክርስቲያኖች በትምህርት ቤት፣ በሥራ ቦታ ብርሃናቸውን እንዳበሩ የተገነዘብህበት ግልጽ መንገድ አለን?
6. እግዚአብሔር ብርሃናችሁን ለሌሎች እንድታካፍሉ መንፈሳችሁን ያነሣሣበት ሁነኛ ጊዜ ነበር?
7. ለምናገኛቸው ሰዎች ይህንን ብርሃን እንዳናካፍል የሚያስቸግረን ምንድነው?

5. ጸሎት ከትላልቅ ሰዎች አንዱ ስለ ዛሬው መልእክት ቡድኑን በጸሎት እንዲመራ አድርግ።

**መልእክት: «በዓለም እጅግ እንግዳ የሆነ የዓሣ ታሪክ»**

አንዳንዶቻችሁ ዛሬ አንዳንድ አስገራሚ የዓሣ ታሪኮችን ነግራችሁናል» ለሚቀጥሉት ጥቂት ደቂቃዎች እኔ ደግሞ በዓለም አስደናቂ የሆነውን የዓሣ ታሪክ እነግራችኋለሁ፤ አንዳንዶቻችሁ ታሪኩን ታውቁታላችሁ። ይሁንና እንደምታውቁት የዓሣ ታሪኮች ደጋግመው በተነገሩ ቁጥር እየተሻሻሉ ይሄዳሉ። የዛሬውም የተለየ አይሆንም።

ነነዌ ጥንታዊት ከተማ ነበረች። ትልቅም ከተማ ነበረች። እንዲያውም በዚያ አካባቢ በዕድገቷ ተወዳዳሪ የሌላት ከተማ ነበረች። ይህ ታሪክ በተፈጸመበት ወቅት በነነዌ ውስጥ በመቶሺዎች የሚቆጠሩ ነዋሪዎች ነበሩ። በየቀኑ የከተማይቱ ዓቅም ከሚችለው በላይ ብዙ ሕዝብ ይመጣ ነበር። በተጨማሪም ነነዌ በኃጢአት

የረከሰች ከተማ ነበረች። ነገሮች ከቁጥጥር ውጭ ሆነው በመታየታቸው እግዚአብሔር ይህችን ከተማ ለማጥፋት ወሰነ። ቀደም ሲል እግዚአብሔር ከክፋታቸው ቅጥ ማጣት የተነሣ ሰዶምንና ገሞራን እንዳጠፋቸው እናውቃለን። በኖሕ ዘመንም ዓለምን በሙሉ አጥፍቷል። ይህ ነነዌ ምን ያህል ክፋት እንደነገሠባት ያስገነዝበናል።

እግዚአብሔር ፍትሐዊና ጻድቅ ቢሆንም፣ ማንኛውም የሰው ልጅ ለዘላለሙ እንዲጠፋ አይፈልግም። ማንኛውም ሚሲዮናዊ ወይም የእግዚአብሔር ነቢይ በነነዌ ውስጥ አልነበረም። ስለሆነም፣ ሕዝቡ ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ከኃጢአት ነጻ ስለመውጣት ሰምተው አያውቁም ነበር። ከዚህም የተነሣ፣ እግዚአብሔር ለከተማይቱ ሌላ ዕድል ለመስጠት ወሰነ። ዮናስ የተባለ ነቢይ መርጦ ወደ ነነዌ ላከ። ዮናስ ግን «እባክህን፣ እግዚአብሔር፣ እኔን አትላከኝ። ሌላ ሰው ላክ። እኔ ለመሄድ አልፈልግም» አለ።

«ሄደህ ካልነገርካቸው ሊጠፉቸው ነው!» ሲል መለሰለት እግዚአብሔር።

ይህ ዮናስን ብዙም ያሳሰበው አይመስልም። እንዲያውም፣ ዮናስ እግዚአብሔር የነነዌን ሕዝብ እንዲያጠፋ ይፈልግ ነበር። እግዚአብሔር ከዮናስ ጋር መወያየቱን ቀጠለ። የዮናስ ቀጣይ ምላሽ፣ «አገሩ በጣም ሩቅ ነው። ከአገሬ መውጣት አልፈልግም። ጓደኞችና ቤተሰቦች እሉኝ። ከዚህ ንቅንቅ አልልም» የሚል ሆነ።

«ዮናስ፣ መልእክቴን እየጠፋና እየሞተ ላለው ሕዝብ እንድታደርስልኝ እፈልጋለሁ። ይህ ካልሆነ፣ ሕዝቡን ማጥፋቴ ነው።»

ዮናስ ቀላል የማምለጫ መንገድ በመ..ለግ፣ «የሕዝቡን ዝና ሰምቻለሁ። በጣም የተበላሹ ሰዎች ናቸው! ከእንደነዚያ ዓይነት ሰዎች ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንዲኖረኝ አልፈልግም! ሂድና አጥፋቸው» አለ።

እግዚአብሔር ግን ንስሐ ገብተው ይቅርታ ሊያገኙ የሚችሉበትን ዕድል ሳያገኙ በፊት የነነዌን ሰዎች ለማጥፋት አልፈለገም። ለዚህ ሥራ የመረጠው ደግሞ ዮናስን ነበር። ዮናስ ግን ይህንን ሥራ ለማከናወን ስላልፈለገ ኮበለለ። ከእግዚአብሔር መኮብለል ምን እንደሚመስል አንዳንዶቻችሁ ታውቃላችሁ። ምናልባት አንዳንዶቻችሁ አሁንም እየኮበለላችሁ ይሆናል። መኮብለላችሁን ልትቀጥሉ ትችላላችሁ። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ልትደበቁ አትችሉም። እግዚአብሔር ሁልጊዜም የት እንዳላችሁ ያውቃል። ለመሸሽ ከመሞከር ይልቅ መጀመሪያውኑ እግዚአብሔርን መታዘዙ ይቀላል።

ዮናስ ከእግዚአብሔር ለመሸሽ ስለቆረጠ፣ የአንድ ጉዞ ቲኬት ገዝቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ። ዮናስ አጉል አምልኮ የሚከተሉ ሰዎች



በሞሉበት መርከብ ውስጥ ገብቶ ከጥፋተኝነት ስሜቱ ለመገላገል የውስጥኛ ክፍል ተኛ። ከእግዚአብሔር ልንሸሽ አንችልም። እግዚአብሔር ዮናስ ያለበትን ቦታ በትክክል ያውቅ ነበር። በባሕሩ ላይ ኃይለኛ ማዕበል ተነሣ። ውኃው መርከቡን ሲያናውጠው ተጓዦቹ ለመሞት መቃረባቸውን ተገነዘቡ። ዮናስ የእግዚአብሔር ሰው መሆኑን ያውቁ ስለነበር እንዲጸልይላቸው ለመኑት።

ዮናስ ግን ይህንን ለማድረግ አልፈለገም ነበር! ለማንም የመጸለይ ዓቅም አልነበረውም። ሕሊናው አቅሉን አሳጣው። አጉል አምልኮ የተጠናወታቸው ተጓዦች ማን ከመርከቡ መጣል እንዳለበት ዕጣ ጣሉ። ዕጣው ዮናስ ላይ ወደቀ። በዚህ ጊዜ ዮናስ የማዕበሉ ምክንያት ራሱ መሆኑን ነገራቸው። ተጓዦቹ ዮናስን ከመርከቡ አውጥተው ውኃው ውስጥ ሲጥሉ ማዕበሉ ጸጥ አለ። ምንም እንኳዋን ነገሮች ለተጓዦቹ ጥሩ መልክ መያዝ ቢጀምሩም፣ ዮናስ ፍጹም አዲስ ዓሣ የማጥመድ ገጠመኝ ውስጥ ሊገባ በመዘጋጀት ላይ ነበር።

ትልቅ ዓሣ ነባሪ ዋጠው። መጽሐፍ ቅዱስ ምን ዓይነት ዓሣ እንደሆነ ባይናገርም፣ ዓሣ ነባሪ ነው ብለን እንውሰደው። ዓሣ ነባሪ በጣም ትልቅ ዓሣ ነው! ራሳችሁን ሙሉ በሙሉ በዓሣ ነባሪ ሆድ ውስጥ እንደተዋጣችሁ አድርጋችሁ አስቡ። ይኼ ገጠመኝ ምን እንደሚመስል ይታያችኋል? በዓሣ ነባሪ ሆድ ውስጥ መሆን ምን ይመስል ይሆን? መጽሐፍ ቅዱስ ዮናስ ቀጣዮቹን ሦስት ቀናትና ሌሊቶች በዓሣ ነባሪ ሆድ ውስጥ እንዳሳለፈ ይናገራል። ይኼ በጣም ረዥም ጊዜ ነው።

በዓሣ ነባሪ ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ምን ልትሠሩ ትችላላችሁ? በሆድ ፈሳሾች መካከል መንቦጫረቅ? (Back stroke) የጨጓራ አሲዶቹን መቅመስ? ማሰብ? ዮናስ አውጥቶ አውርዶ አሰላሰለ። ዮናስ ለሦስት ቀንና ሌሊት በዓሣ ነባሪው የሆድ ጡንቻዎች ውስጥ እየዋኘ ከእግዚአብሔር ጋር ሕይወቱን ስለማስተካከል አሰበ። ዮናስ እግዚአብሔር ሌላ ዕድል እንዲሰጠው ጠየቀ። ለመሸሽ ከመሞከር ይልቅ መጀመሪያውኑ እግዚአብሔርን ቢያገለግል ኖሮ ምን ያህል በቀለለው ነበር!

ዮናስ ወደ ነነዌ ሄደ። ከከተማይቱ መሀል ቆመ። ለመንገድ ተተላፊዎች የተሟሟቀ ስብከት አደረገ። ስለሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድ አስጠነቀቃቸው። ልጆቹ እንዲሞቱ ስለማይፈልገው አፍቃሪ አምላክ ነገራቸው። ሕዝቡም ቀመው አዳመጡት። ከዚህ በፊት እንዲህ ዓይነት መልእክት ሰምተው አያውቁም ነበር! ከኃጢአት አስራታችን እንፈታለን ብለው አስበው አያውቁም ነበር። ንጉሡ ስለ ዮናስ ስብከት በሰማ ጊዜ ሕዝቡ ከኃጢአታቸው ንስሐ ገብተው አንዱን እውነተኛ አምላክ ብቻ እንዲያመልኩ አዋጅ አወጣ። ዮናስ ሕዝቡ ከክፉ መንገዳቸው

ካልተመለሱ እግዚአብሔር በ40 ቀናት ውስጥ እንደሚያጠፋቸው በመግለጽ ያቀረበውን ተከታታይ ስብከት ፈጸመ።

ዮናስ እግዚአብሔር እንዲያስተላልፍ የፈለገውን መልእክት ካስተላለፈላቸው በኋላ፣ ከከተማይቱ ወጣ ብሎ እግዚአብሔር ከሰማይ እሳት አውርዶ ከተማይቱን ሲያጠፋ ለማየት ይጠባበቅ ጀመር። ዮናስ እግዚአብሔር አንዳች የፍርድ እርምጃ ሲወስድ ለማየት ፈለገ። 40 ቀናት ቢያልፉም የተከሰተ ነገር አልነበረም። ሕዝቡ በንስሐ ስለተመለሱ እግዚአብሔር ሊያጠፋቸው የሚፈልግበት ምክንያት አልነበረውም። ዮናስ ግን በቁጣ ጦፎ እግዚአብሔርን ግደለኝ ሲል ተማጸነ። ዮናስ የተናገረው ትንቢት ፉርሽ ሲሆንበት ተበሳጨ።

የነነዌ ሰዎች ምን ይሉኛል? ሲል ተጨነቀ። ሰዎች ስለኔ ምን ይላሉ? ከሚል ይልቅ ከጥፋት እግዚአብሔርን ወደማወቅ ስለተመለሰችው ከተማ ማሰብ ነበረበት። ባሕርዩ መመርመር ነበረበት። ከትንህ ወይን ሥር ተቀምጦ እግዚአብሔር እንዲገድለው ለመነ። ወይኗ ስትጠወልግ ዮናስ ኃይለኛ የፀሐይ ቃጠሎ ወረደበት። ዮናስ ማማረሩን በመቀጠል አሁኑኑ ለመሞት መፈለጉን ለእግዚአብሔር ተናገረ። እግዚአብሔር ግን ከዮናስ ጋር መሥራቱን ቀጠለ። እግዚአብሔር ዮናስ ሁለት ጠቃሚ ትምህርቶችን እንዲማር ፈልጎ ነበር። እግዚአብሔር እኛም እነዚህን ትምህርቶች እንድንማር ይፈልጋል።

አንደኛ፣ የክርስቶስን ማዳን ለጠፋውና በመሞት ላይ ላለው ዓለም የማካፈል ኃላፊነት አለብን። እግዚአብሔር እያንዳንዳችን ለሚያጋጥሙን ሰዎች መልእክቱን እንድናካፍል ተልዕኮ ሰጥቶናል። ትምህርት ቤትህ የጠፋና በመሞት ላይ ያለ ዓለም ነው። እግዚአብሔር መልእክተኛው እንድትሆንለት ይፈልጋል። ብዙውን ጊዜ ከጌታ ውጭ ስላሉት ወጣቶች በማሰብ ፈንታ እንደ ዮናስ ሰዎች ምን ይሉኛል? እንላለን።

መልእክቱን ለዚህ ለጠፋውና በመሞት ላይ ላለው ዓለም ካላካፈልን፣ ማን ይሆን ይህንን የሚያደርገው? ዓለቶች ድምጽ አውጥተው የሚናገሩ ይመስላችኋል? ይኼ ሊታሰብ የማይችል ነገር ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ የክርስቶስን ወንጌል ባትመሰክሩ ጓደኞቻችሁ ሞተው ወደ ሲኦል እንዲወርዱና ለዘላላም በዚያ እንዲሠቃዩ መፍቀዳችሁ ነው። ይህ ደግሞ ለአእምሮ የሚከብድ ነገር ነው። ለነሱ ወንጌሉን ማካፈል የናንተ ኃላፊነት ነው። ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጡ ጋብዟቸው። እንደዚህ ወዳሉት የወጣቶች ስብሰባዎች አምጧቸው። እስኪ እነሱን ለክርስቶስ እንውደዳቸው።

ምናልባትም እግዚአብሔር አንዳንዶቻችሁ እንደ መጋቢነት፣ የወጣት አገልጋይነት፣ ሚሲዮናዊነት ወይም የመዝሙር ወንጌላዊነት ባሉት የሙሉ ጊዜ አገልግሎቶች መንፈሱን እንድታካፍሉ እየጠራችሁ



ይሆናል። ለዚህ ጥሪ አዎንታዊ ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኞች ናችሁ? እንደ ዮናስ ትሸሻላችሁ ወይስ እንደ ኢሳይያስ፣ «ጌታ ሆይ፣ እኔን ላከኝ» ትላላችሁ?

ሁለተኛ፣ ባሕርያችን መመርመር አለበት። ባለማቋረጥ ቅድሚያ የምንሰጣቸውን ነገሮችና የልባችንን ፍላጎቶች መመርመር አለብን። ሁለተኛ ቆሮንቶስ 13፡5 ራሳችንን መመርመር እንዳለብን ይነግረናል። ክርስቲያኖች እንደመሆናችን፣ ራሳችንን በመንፈሳዊ ሁኔታ የመመርመር ልማድ ሊኖረን ይገባል። አንዳንዶቻችሁ ዛሬ ባሕርያችሁን መመርመር ያስፈልጋችሁ ይሆን? ከሆነ፣ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አብረን እንጸልያለን። አንዳንዶቻችሁ የእግዚአብሔርን መንፈስ ለዓለም የማካፈሉን ኃላፊነት ቸል ብላችሁ ይሆን? እንደ ዮናስ ሌሎች ስለሚያስቡት ጉዳይ ተጨንቃችሁ ይሆን? አንዳንዶቻችሁ አሁንም ከእግዚአብሔር እየሸሻችሁ ይሆናል። ሽሽታችሁ አሁኑኑ ሊቆም ይገባዋል። እግዚአብሔር ዛሬ ፍለጋችሁን ሊያቆም ይችላል። እግዚአብሔር ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት የጠራው ሰው እዚህ ይኖር ይሆን? ምላሻችሁ ምንድነው?

በዓለም እጅግ አስገራሚ በሆነው የዓሣ ታሪክ አማካኝነት እግዚአብሔር ሁላችንም ለዓለማችን ኃላፊነት እንዳለብን አስተምሮናል! እስኪ አንድ ላይ ሆነን፣ («Share his spirit» ወይም ሌላ መዝሙር) እንዘምር። ዛሬ በሕይወታችሁ የሚያስፈልጋችሁ ነገር ካለ ወይም እግዚአብሔር ላሳያችሁ ነገር ምላሽ ለመስጠት ከፈለጋችሁ፣ የግል ጸሎት እንድታደርጉ ይህንን ጊዜ ተጠቀሙ።

*መዝጊያ*

*(መሠውያ ካለ ወጣቶቹ ወደፊት ለጸሎት እንዲመጡ ልትጠይቃቸው ትችላለህ።)*

## አንተና ዳኛው

### ከቴድ ቴይለር

ዓላማ፡ ወጣቶች የፍርድ ቀንን እውነታ እንዲገነዘቡ ለማድረግና ለሕይወታቸው ተጠያቂነትን እንዲማሩ ለማገዝ።

ዝግጅት

1. እነዚህን ጥቅሶች አጥና ማቴዎስ 12፡34፣36-37፣ ምሳሌ 13፡3፣ ያዕቆብ 1፡26፣ ዕብራውያን 9፡27፣ ሮሜ 3፡10፣23፣ ዮሐንስ 3፡17 1ኛ ዮሐንስ 4፡16-17።
2. ለድራማው ወጣቶችን መልምል
3. ስለ ስብሰባው ማስታወቂያ ተናገር።

የቡድን እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ቀርበዋል።)

ለምሽቱ አንድ የማያዳላ ወጣት ዳኛ ሲይም። ወጣቱ አስቂኝ ቢሆን ይመረጣል። ዳኛው ጥቁር ልብስ ለብሶ ባጌጠ ወንበር ላይ እንዲቀመጥ አድርግ። ጠረጴዛውን በመምታት ፀጥታ የሚያስከብርለት ዱላም ይኑረው።

1. የዳኛው ምርጫ። በዚህ ጨዋታ ውስጥ የእያንዳንዱ ቡድን አባላት ዳኛው ወዳለበት ሮጠው ይሄዳሉ። በዚያም አንድን ሰው ወይም እንስሳ ለመኮረጅ ይሞክራሉ። ዳኛው ጥሩ አድርጌ መኮረጃቸውን ሲያረጋግጥ፣ ወደ ቦታቸው ይመለሱና ተረኛው ይመጣል። ለአሸናፊዎቹ ነጥቦችን ስጥ።
2. እማማ። ለእያንዳንዱ ቡድን ሁለት ወይም ሦስት እሽግ የሶፍት ወረቀት አድልና እያንዳንዱ ቡድን ከአባላቱ አንዱን ትልቅ ሴት አድርጎ እንዲለውጥ ጠይቅ። አሸናፊው በዳኛው ምርጫ ይወሰናል።

ሽግግር፡ ከሚከተሉት አንዱን ወይም ሁሉንም በመጠቀም ወደ መልእክቱ ተሸጋገር።

1. የቡድን ዝማሬ።
2. ከወጣቱ ዳኛ ጋር ቃለምልልስ አድርግ። የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቅርብለት።
   ሀ. ዳኝነት ምን ይመስላል?
   ለ. ውሳኔዎችን መስጠት ይከብዳል?
   ሐ. ሰዎች ይጣሉኛል ብለህ ፈርተህ ነበር?
   መ. በፍርድ ቀን የእግዚአብሔርን ድርሻ ለመውጣት ትፈልጋለህ?
3. ድራማ
   አስተዋዋቂ



የዝግጅቱ መሪ ጴጥሮስ
አልፎንስ
አቶ መልካም መሳይ
በረከት ኢማ

አስተዋዋቂ፡ ክቡራንና ክቡራት፣ በዓለም እጅግ ታላቅ የሆነው እውነትን ገላጭ ጨዋታ ወደሚተላለፍበት የቴሌቪዥን ፕሮግራም በአክብሮት እንጋብዛችኋለን። አሁን በክቡር ያህዌ እግዚአብሔር ዳኝነት «የእግዚአብሔር ችሎት» ተግባሩን በማከናወን ላይ ይገኛል። እስኪ ሐዋርያው ጴጥሮስ ወደሚያቀርብላችሁ ዝግጅት እንተላለፍ።

ጴጥሮስ፡ አመሰግናለሁ። «የእግዚአብሔር ችሎት» ወደተባለው ወደዚህ የቴሌቪዥን ፕሮግራም በአክብሮት እንጋብዛችኋለን። በዚህ ችሎት አንድ ሽልማት ካገኛችሁ ለዘላለም የናንተው ይሆናል። ሕጎቻችን ሁሉ ከእግዚአብሔር ቃል የወጡ ናቸው። የዕብራውያን መልእክት፣ «የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና የሚሠራም ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፣ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፣ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል» (4፡12) ይላልና። እስኪ አሁን የመጀመሪያውን ተወዳዳሪ እንመልከት።

አስተዋዋቂ፡ የመጀመሪያው ተወዳዳሪ ከናይሮቢ ኬንያ የመጣ እንጉዳይ በመልቀም ሥራ ላይ የተሰማራ ነው። አልፎንስን በጭብጨባ እንድትቀበሉት እጠይቃለሁ

ጴጥሮስ፡ አልፎንስ እንኳዋን ደህና መጣህ? ዛሬ ምን ዓይነት ስሜት እየተሰማህ ነው?

አልፎንስ፡ እኔ እንጃ። ኃዘን የሚሰማኝ ይመስለኛል።

ጴጥሮስ፡ ፋይልህንስንመለከት፣ የምታዝንባቸው ብዙ ነገሮች አሉ። «የእግዚአብሔር ችሎት» አዲሱ ባለሪከርድ ሆነሃል። ለዚህም ምክንያቱ በሕይወትህ ዘመንህ እግዚአብሔርን በመርገም ወይም የኢየሱስን ስም 621,486 ጊዜያት በመጥራት የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ማንሣትህ ነው። ይህ ደግሞ የቀድሞው ባለ ሪከርድ ከነበረው ከቢሊከሰር 1,208 ጊዜ የበለጠ ነው። አልፎንስ በመንገድ ላይ ለአንዲት አሮጊት ያደረግሁላት ርዳታስ? «እግዚአብሔር ይባርክሽ» ሁሉ ብያት ነበር።

ጴጥሮስ፡ ጥፋትህን እምብዛም የሚቀንሰው አይመስለኝም። እስኪ መጽሐፉን እንመልከት። ፍርዱ የተመሠረተበት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ማቴዎስ 12፡34፣36-37 ነው። «እናንተ የእፉኝት ልጆች ክፉዎች ስትሆኑ መልካም ለመናገር እንዴት ትችላላችሁ? በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና።» «እኔ እላችኋለሁ፣ ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህን ከቃልህም የተነሣ ትኰነናለህ።»

አልፎንስ፡ እንግዲህ ምንድነው የሚፈረድብኝ?

ጴጥሮስ፡ በውድድሩ ላይ ታላቅ ስፖርተኛ ነበርህ። ለማንኛውም እኔ አንተን ባለመሆኔ ደስተኛ ነኝ (አልፎንስ ይወጣል)።
አስተዋዋቂ፡ ቀጣዩ ተወዳዳሪያችን ከሌጎስ ናይጄሪያ ሲሆን፣ መልካም መሳይ ይባላል። መልካም መሳይ የነዳጅ ጉድጓድ ያለው ከበርቴ ነው።
ጴጥሮስ፡ ሁሉም ነገር ወደሚታወቅበትና ወደሚታይበት «የእግዚአብሔር ችሎታ» እንኳዋን ደህና መጣህ?
አቶ መልካም መሳይ፡ እዚህ በመገኘቴ ደስታ ይሰማኛል። ለቤተክርስቲያናችን አዳዲስ አግዳሚ ወንበሮች ለመግዛት ብዙ ገንዘብ አሰባስቤአለሁ።
ጴጥሮስ፡ እስኪ ፋይልህን እንየው። ፋይልህ እንከን የለሽ ባለመሆኑ አዝናለሁ።
መልካም መሳይ፡ ምን ማለትህ ነው?
ጴጥሮስ፡ በየካቲት 30/2001 በካንትሪ ክለብ ውስጥ የተከሰተው ሁኔታ ትዝ ይልሃል? በዚያን ሰዓት ሐሜትና ቆሻሻ ቀልዶችን ስትናገር ነበር።
መልካም መሳይ፡ ይኼኮ ሁሉም የሚያደርገው ነገር ነበር። ሁላችንም እንደዚያ ዓይነት ታሪኮችን እንናገር ነበር- - -
ጴጥሮስ፡ እስኪ መጽሐፍ ቅዱስ የሚልህን እንመልከት። ያዕቆብ1:26፣«እንደበቱን ሳይገታ ልቡን እያሳተ እግዚአብሔርን የሚያመልክ የሚመስለው ማንም ቢኖር የእርሱ አምልኮ ከንቱ ነው።» ይላል።
መልካም መሳይ፡ ያሳዝናል! በየእሑዱ ወደዚያ አሰልቺ ቤተክርስቲያን ስመላለስ ቆይቼ? (አቶ መልካም መሳይ ይወጣል።)
ጴጥሮስ፡ አዝናለሁ። እሱን ለዳኛው ልትናገር ትችላለህ።
አስተዋዋቂ የመጨረሻው ተወዳዳሪ በሉሳካ ዛምቢያ የምግብ መደብር ውስጥ ይሠራል። በረከት ኢማ በጭብጨባ እንድትቀበሉት እጠይቃለሁ።
በረከት ኢማ፡ ጌታ ይመስገን። እዚህ መገኘቴ ለኔ እውነተኛ በረከት ነው። ለረዥም ዘመናት ይህችን ቀን ስናፍቃት ቆይቻለሁ። ጴጥሮስ፣ ሁልጊዜም በውኃ ላይ መሄድን እንድታስተምረኝ ስፈልግ ነበር።
ጴጥሮስ፡ ብዙ ጊዜ ስላለን እሱን በኋላ እናደርገዋለን። እስኪ ፋይልህን እንክፈተው። ፍጹም ባዶ! አንድም ኃጢአት ወይም ጉድፍ የለውም።
በረከት ኢማ፡ ጌታ ይመስገን። ግን ይኼ የራሴ ጽድቅ አይደለም። ወጣት እያለሁ ክርስቶስ ወደ ሕይወቴ እንዲገባ ከጠየቅሁት በኋላ፣ ከርሱ ጋር እጅግ ደስ የሚያሰኝ ሕይወት አሳልፌአለሁ። አየህ፣ የክርስቶስ ደም አጥቦ አነጻኝ። ብዙ ጥፋቶችን ፈጽሜአለሁ። ነገር ግን የርሱ ደም እንዲያነጻኝ ስጠይቅ፣ ምንም ጥፋት እንዳልፈጸምሁ አድርጎ ያነጻኛል።



ጴጥሮስ፡ ስለ አንተ የሚናገር ጥቅስ- - - ራእይ 21:1-2፣4፣«አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ፣ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፣ ባሕርም ወደ ፊት የለም። ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፣ ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ፣ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ።» «እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፣ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፣ ኃዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፣ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ።»
በረከት፡ ጌታ ይመስገን!
ጴጥሮስ፡ ምሳሌ 13:3ን በማንበብ የዛሬውን ዝግጅት እናበቃለን። «አፉን የሚጠብቅ ነፍሱን ይጠብቃል ከንፈሩን የሚያሞጠሙጥ ግን ጥፋት ያገኘዋል።» ከዕንቁዋ ደጅ፣ «ደህና ሁኑ፣ አንድ ቀን በእግዚአብሔር ችሎት እናገኛለን» በማለት የምሰናበታችሁ ሐዋርያው ጴጥሮስ ነኝ።

መልእክት፡ «የፍርድ ቀን»
የፍርድ ቀን- - ብዙዎቻችን ስለዚህ ዕለት ለማሰብ አንፈልግም። ነገር ግን ይህ በምድር ላይ ለተናገርነውና ለፈጸምነው ተግባር ሁሉ በኃላፊነት የምንጠየቅበት ቀን እየቀረ ነው። ዕብራውያን 9:27 እንደሚለው፣ «ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው፣» ከዚህ የፍርድ ቀን የሚያመልጥ ቅዱስ ወይም ኃጢአተኛ አይኖርም።
አስተማሪህ የሰጠህን የቤት ሥራ ተመልሶ የማይጠይቅ ቢሆን፣ ወይም በቤት ሥራው ውስጥ የተነሡት ነጥቦች በፈተና ላይ የማይመጡ ቢሆኑ፣ የቤት ሥራውን ትሠራዋለህ? የፍርድ ቀን ለተማሪው የፈተና ቀን፣ ለገበሬው የመከር ቀን፣ ለአትሌቱ ታላቁ ውድድር ነው። ይህ ሁላችንም ለተግባራችን በኃላፊነት የምንጠየቅበት ዕለት ነው። ሽልማቶችና ቅጣቶች ይሰጣሉ።
ስለዚሁ ጉዳይ ልናውቃቸው የሚገቡ ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ።

1. ሮሜ 3:10 *«አስቀድመን ከሰናቸዋልና እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ»* ሮሜ 3:23 *«ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል»* አሳዛኙ ዜና ስንት ጊዜ ወደ ቤተክርስቲያን ብንመላለስ እንኳዋን ሁላችንም ፈተናውን ስለወደቅን፣ ለዘላለማዊ ቅጣት መጋለጣችን ነው። «አታድርጉ» የሚባሉትን ነገሮች ሁሉ (መጠጥ፣ ሲጋራ፣ ከጋብቻ ውጭ የሚፈጸም ወሲብ፣ ወዘተ.) ብንተው እንኳዋን ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት ብቁዎች አንሆንም። ከክርስቶስ በቀር እግዚአብሔርን ሊያስደስት የሚችል ሕይወት የኖረ ማንም የለም።

2. ዮሐንስ 3:17 *«ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና።»* መልካሙ የምሥራች በራሳችን ጽድቅ ልንቆም ባንችልም ክርስቶስ ቅጣታችንን ስለተቀበለ፣ በርሱ ጽድቅ ልንቆም እንችላለን። እግዚአብሔር ዳግም ላያስታውስ ኃጢአታችንን ይቅር ይለዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአታችንን የሚሸፍነው በመስቀል ላይ የፈሰሰው የክርስቶስ ደም እንደሆነ ይናገራል።

የእግዚአብሔርን ፍርድ ልንፈራ ይገባልን? ክርስቶስ ወደ ልባችን እንዲገባ ካልጋበዝነና እርሱ ባዘዘን መንገድ ካልኖረን፣ በጣም ልንፈራ ይገባል። ክርስቲያኖች ከሆንንና እግዚአብሔር በልባችን ውስጥ ካለ የሚያስፈራን ነገር አይኖርም። 1ኛ ዮሐንስ 4:16-17 እንደሚለው፣ «እኛም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር አውቀናል አምነንማል። እግዚአብሔር ፍቅር ነው፣ በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል። በፍርድ ቀን ድፍረት ይሆንልን ዘንድ ፍቅር በዚህ ከእኛ ጋር ተፈጽሞአል እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነንና።» አንድ ቀን ከዳኛው ጋር ፊት ለፊት እንገናኛለን - አንተና ዳኛው ብቻ! ክርስቶስ በሕይወታችሁ ውስጥ ጎልቶ ይታያል? ካልሆነ፣ አሁኑኑ ፍጹም አዲስ ጅማሬ ልታካሂዱ ትችላላችሁ። ይህም ታላቅና ወደፊትም ይበልጥ እየጎለመሰ የሚሄድ ሕይወት ነው። ክርስቲያኖች የኋላ ታሪክ፣ ዓላማውያን ደግሞ የወደፊት ተስፋ እንደሌላቸው አስታውሱ። (በጸሎት/የመሠውያ ጥሪ ፈጽም።)



# ቤተመቅደስን እንዴት መገንባት ይቻላል?

(ክፍል አንድ)

ክሱዚ ሸለንበርገር

ዓላማ፡ ሰወጣቶች መልካም የንብረት አስተዳዳሪነት በክርስትና ወሳኝ መሆኑን ማስገንዘብ።

ዝግጅት

1. ከስብሰባው አንድ ሳምንት አስቀድመህ ስለ ስብሰባውና ስለሚከተሉት ነገሮች ማስታወቂያ ተናገር።
   ሀ. የቡድን ውድድሮች
   ለ. በስብሰባው ላይ ለሚገኙና እንግዶችን ይዘው ለሚመጡ ሰዎች የነጥብ ሽልማቶች እንደሚሰጡ
2. ትዝቢት ሐጌን አጥና።

የቡድን እንቅስቃሴዎች ስብሰባውን ለመጀመር ከሚከተሉት እንቅስቃሴዎች አንዱን ወይም ሁሉንም ተጠቀም።

1. ማሽን የመፍጠር ጨዋታ። 13 ደቂቃዎችን በመስጠት እያንዳንዱ ቡድን አንድ-ማሽን እንዲፈጥር ጠይቅ። እያንዳንዱ የቡድኑ አባል የማሽኑን የተወሰነ ክፍል ይወክላል። የተሰጠው ጊዜ ሲያልቅ፣ ቡድኖቹ *ሥራዎቻቸውን* እንዲያቀርቡ ጠይቅ። ሌሎቹ የማሽኑን ምንነት እንዲገምቱ አድርግ። ከፍተኛ የፈጠራ ጥበብ ለታየበት ማሽን ሽልማት ወይም ነጥቦችን ሸልም።
2. የጭብጨባ ፈተና። *መሪው* እጆቹን ሲያጣምር ወጣቶቹ ያጨበጭባሉ። ሳያጣምር ካጨበጨቡ ወይም አጣምሮ ሳለ ካላጨበጨቡ ከክፍሉ ይወጣሉ።
3. ሁሉም በክብ መልክ ይቀመጣሉ። *መሪው* አንድ ገለጻ ያነባል። ገለጻው ከሁኔታው ጋር የተመሳሰለበት ሰው ወደ ቀኝ አንድ *መቀመጫ* ይጠጋል። ለምሳሌ፣ *መሪው* ረዥም ጸጉር ካለህ፣ ወደ ቀኝህ አንድ *መቀመጫ* ተጠጋ ሊል ይችላል። እረንጓዴ ካልሲ ያደረገ ሰው ካለ አንድ *መቀመጫ* ወደ ቀኝ ይጠጋል። ከቀኛቸው ባለው ወንበር ላይ ሰው ካለበት ሊያስነሡት አይችሉም። ነገር ግን በተቀመጠው ልጅ ታፋ ላይ ይቀመጣሉ። በአንድ ወንበር ላይ 3፣4፣5 ወይም ከዚያ የሚበዛ ሰው ሊቀመጥ ይችላል። ለእያንዳንዱ ጨዋታ ከ15-20 ገለጻዎችን አንብብ።

ሽግግር፡ (እነዚህ ወደ መልእክቱ የምትሸጋገርባቸው ነገሮች ናቸው።)

1. የቡድን ውድድሮችን አሸናፊዎች አስታውቅና የተሻሻለውን ነጥብ (የእስካሁን ድምር) ስጣቸው።
2. የቡድን ዝማሬ

3. ድራማዎች። የሚከተሉት ድራማዎች ቅጂዎች ከስብሰባው ሁለት ሳምንት አስቀድሞ ለተዋንያኑ መሰጠት አለባቸው።

ድራማ1 ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር
እግዚአብሔር! ዋላሳ
ዋላሳ (ስሜታዊነት ባልታየበት መልኩ)፣ አቤት!
እግዚአብሔር: እኔ እግዚአብሔር ነኝ።
ዋላሳ (ቀና ብሎ) እሺ!
እግዚአብሔር: ገንዘብ የምትሰጥበት ጊዜ አሁን ነው ዋላሳ። በቀጣዩ እሑድ ቤተክርስቲያንህ ለቤተመቅደስ ግንባታ ልዩ መባ ይሰበሰባል። ለዚህ ሥራ ምንድነው የምታደርገው?
ዋላሳ: እሺ፣ ሁሉንም አውቀዋለሁ። ማስታወቂያውን አንብቤአለሁ። ምን እንዳደርግ ነው የምትፈልገው? ያጠራቀምኳትን ሣንቲም አውጥቼ እንድሰጣቸው? ብሰጣቸውም እንኳዋን አንድ ወይ ሁለት ሚስማር ቢገዛላቸው ነው።
እግዚአብሔር: ከልብህ እንድትሰጥ ነው የምፈልገው።
ዋላሳ: መስጠት??? ዋጋ የሚያወጣውና ለቤተክርስቲያን ልስጥ የምችለው ነገር ቢኖር የቅርጫት ኳዋስ መጫወቻ ጫማዬ ብቻ ነው። ይኼ ደግሞ አይሆንም። ማለቴ፣ በሜዳ ውስጥ ቡት ጫማ አድርጌ ምን እንደምመስል አይታይህም? (ለአፍታ ዝም አለና) ሊሆን አይችልም!
እግዚአብሔር: ዋላሳ! እንድትሰጥ እፈልጋለሁ።
ዋላሳ: እሺ። እስኪ ጸጥ ብዬ ላስብ። እሰጣለሁ። አዎ፣ እሰጣለሁ። ጊዜዬን ችሎታዬን - - - ጉልበቴን - - - ራሴን እሰጣለሁ። ሌላ ምን ልሰጥ እችላለሁ?
እግዚአብሔር: ገንዘብህን።
ዋላሳ: (በምፀት እየሣቀ): እሱ ደግሞ ምንድነው?
እግዚአብሔር: ዋላሳ፣ ገንዘብህን እንድትሰጥ እፈልጋለሁ።
ዋላሳ: (እየሳቀ) እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን ገንዘብ እንድሰጥ ይፈልጋል። (እየሳቀ ይቆይና ኮስተር ይላል) ገንዘብ! ውድ እግዚአብሔር ሆይ፣ ብረዳ ደስ ባለኝ። እውነቴን ነው። ግን ግፋ ቢል ሃያ አራት ብር ብሰጥ ነው!
እግዚአብሔር: ሁለት መቶ ብር እንድትሰጥ እፈልጋለሁ።
ዋላሳ: ሁለት መቶ በር? ሁለት መቶ ብር? (ዝም ይልና) እኔ ይኼን ያህል ልሰጥ አልችልም። ከሥራዬ በወር የማገኘው ገቢ ሦስት መቶ ሃያ ብር ብቻ ነው። ሁለት መቶውን ከሰጠሁ ለወር መተዳደሪያዬ የሚቀረኝ አንድ መቶ ሃያ ብር ብቻ ይሆናል። በዚህ ገንዘብ እንዴት ወሩን እዘልቀዋለሁ! በተጨማሪም፣ ለጆሚ የልደት ቀን ገንዘብ ማጠራቀም አለብኝ።



እግዚአብሔር: የምትሰጠው መስጠት እችላለሁ ብለህ የምታስበውን ያህል ከሆነ ሰጠህ ማለት አይቻልም።
ዋላሳ: ምን ማለትህ ነው?
እግዚአብሔር: እውነተኛ መስጠት የሌለህን መስጠት ነው። የመሥዋዕትነት መስጠት። እኔ የሚያስፈልግህን እንደማሟላልህ በማመን እችላለሁ ብለህ ከምታስበው በላይ መስጠት።
ዋላሳ: አዎ፣ የሚያስፈልገኝ እንደምታሟላልኝ ማመኑ ችግር የለውም። ከአንተ ሌላ ማንም ይኼን እንደማያደርግልኝ አውቃለሁ።
እግዚአብሔር: ደስታንና በረከትን ልታጭድ የምትችለው በመሥዋዕትነት ስትሰጥ ነው።
ዋላሳ: ሁለት መቶ ብር? (ዝም ይልና) አዎ - በረከቱን ልጠቀም እችላለሁ!

ድራማ2 - የነፍሳት ጥሪ
ትዕይንት: *በግብዣው ጊዜ አራት ሰዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ ይታያሉ። እያንዳንዱ ሰው የውስጡን አሳብ በንግግር ሲያንፀባርቅ ሌሎቹ ፀጥ ቀጥ ይላሉ (ፍሪዝ ያደርጋሉ)።*
ሰባኪ: መንፈሳዊ ቃል ኪዳን ለመግባት ለምትፈልጉ ሰዎች አሁን መሠውያውን እንከፍታለን።
ቁጥር1: አ፣ ብስኩቶቹ እንደማይበላሹ ተስፋ አደርጋለሁ። ዛሬ ከቤተክርስቲያን መልስ ብዙ ልጆች ከፓርቲው ላይ መገኘታቸው አይቀርም። ብስኩቶቹ ከተበላሹ ችግር እንደሚፈጥሩብኝ አይጠረጠርም። (ዝምታ)
ምድጃውን ያጠፋሁት አይመስለኝም!
ሰባኪ: ለቤተመቅደሱ ዳግም ግንባታ ለምታደርጉት ቃልኪዳን ብዙዎቻችሁ ለመጸለይ እንደምትፈልጉ አውቃለሁ። ቤተመቅደሱ- - - እኛው ነንና።
ቁጥር 2: ፈጠን ብሎ ስብከቱን ካልቋጨ፣ የምወደው የቴሌቪዥን ፕሮግራም ሊያመልጠኝ ነው። (ሰዓቱን ደጋግሞ እያየ ይቅበጠበጣል)። ምን ዓይነት ነገር ነው? ቶሎ ካልጨረሰኮ ላልደርስ ነው ማለት ነው!
ሰባኪ: ወደፊት ኑና ከሁሉም የላቀ አስተዋይነት የታከለበት ውሳኔያችሁን አሁን አስታውቁ። ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወትን ዓላማና ምክንያት ሊሰጣችሁ ይችላል።
ቁጥር3: ወደፊት መሄድ ያለብኝ ይመስለኛል። ነገር ግን ከአጠገቤ ያለው ሰውዬ (ሴትዮ) እግሩን አጣምሮ ስለተቀመጠ እኔን ለማሳለፍ እግሩን ማውረድ ሊኖርበት ነው። ይኼ ደግሞ ብዙ ብጥብጥ ያስከትላል። እኔ ደግሞ እንደዚያ ዓይነት ነገር መፍጠር የለብኝም።
ሰባኪ: ቤተመቅደሱን ለመገንባት ፈቃደኞች ናችሁ?

**ቁጥር4**: (እየዘመረ): «Just as I am, with out one plea...» እኔ ወደፊት እንድሄድ መቼም አይጠብቁም:: እኔ በመዘምራን ቡድን ውስጥ ነው ያለሁት! እኔ ተነሥቼ ወደፊት ብሄድ የመዘምራኑ ድምፅ ይቀንሳል:: የነፍሳት ጥሪው ደግሞ በጠንካራ የመዘምራን ድምፅ ካልታገዘ ዋጋ አይኖረውም:: አይ፣ ባልሄድ ይሻለኛል::
ሰባኪ: ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚህ በፊት አይተህ የማታውቀውን ሰላም ይሞላብሃል:: እርሱ ፍጹም አዲስ ሰው እንዲያደርግህ ፍቀድለት::
**ቁጥር2**: የምወደው ፕሮግራም አመለጠኝ ማለት ነው?
ሰባኪ: ዛሬ ትንሽ እንቆያለን:: ለእግዚአብሔር ጥሪ ምላሽ ለመስጠት እንደምትፈልጉ ይሰማኛል::
**ቁጥር1**: ያንኑ ምድጃ ሳላጠፋ ቀርቼ ከሆነ፣ ቤቱ እንዳለ ሊቃጠል ይችላል:: እንደዚያ ከሆነ ደግሞ አባቴ ለዘላለም ከቤቴ እንዳልወጣ ይፈርድብኛል::
ሰባኪ: ለዘላለም ሕይወታችሁ የሚበጀውን ውሳኔ አሁኑኑ ወስኑ::
**ቁጥር3**: እግዚአብሔርን መታዘዝ ያስፈልገኝ ነበር:: ግን እዚያ ጋ ማርክ ብራውን አለ:: ከኔ በላይ ወደ መድረኩ መሄድ ያለበት እሱ ነው:: አንጉል ፓርቲዎች ላይ እንደሚገኝ ሰምቻለሁ እሱ ካልሄደ እኔም አልሄድም:: ከሱ የትናየት እሻላለሁ!
**ቁጥር4**: ወደ መሠውያው ልሄድ አልችልም:: እኔ ከሄድሁ የመዘምራኑ ድምፅ ስለሚቀንስ ጥሩ አይሆንም:: የለም፣ ይህን በደል በቤተክርስቲያን ላይ አልፈጽምም!
ሰባኪ: ክርስቶስ በሚቀጥሉት አሥር ሰከንዶች ውስጥ ቢመለስ፣ አሁኑኑ በመንፈሳዊ ሕይወታችሁ የት ያገኛችሁ ይሆን?
**ቁጥር1**: ከምድጃዬ አጠገብ? (ፍሪዝ)
**ቁጥር2**: ከቴሌቪዥኑ ፕሮግራም ፊት? (ፍሪዝ
**ቁጥር3**: ከማርክ አጠገብ? (ፍሪዝ)
**ቁጥር4**: ከመዘምራኑ ጋር? (ፍሪዝ)
ሰባኪ (ለሕዝቡ) እናንተስ? እግዚአብሄርን ለመታዘዝ ፈቃደኞች ናችሁ?
**5. ጸሎት::**

**መልእክት**: «ቤተመቅደስን እንዴት ማነጽ ይቻላል? (ክፍል አንድ)
ሐጌ ነቢይ ነበር:: ዋና ኃላፊነቱ የእግዚአብሔርን መልእክት ለሕዝቡ ማስተላለፍ ነበር:: ይህ ከባድ ኃላፊነት ቢሆንም፣ በአገልግሎቱ ደስተኛ ነበር:: ይሁንና፣ በዘመኑ እንዲያስተላልፍ የተሰጠው መልእክት ቀላል አልነበረም:: ሐጌ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ ባለማነጻቸው እንዲገስጻቸው ታዞ ነበር:: በዚህ ዘመን የነበረውን ሁኔታ ቀረብ ብለን ከመመልከታችን በፊት ቤተመቅደስን እንዴት ማነጽ እንደሚቻል በአጭሩ እንረዳ::



ቤተመቅደስን እንዴት ማነጽ ይቻላል? መጀመሪያ የመምሪያ መጽሐፍ ማግኘቱ አስፈላጊ ነው:: አስተማማኝና ጠንካራ ግንባታ ለማካሄድ የመምሪያ መጽሐፍ ማግኘት ያሻል:: ሁለተኛ፣ የመምሪያ መጽሐፉን መረዳት ያሻል:: ለኛ ይህ መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ነው:: ክርስቶስን ለመከተልና ትእዛዛቱን ለመፈጸም፣ ከሁሉ አስቀድሞ መጽሐፍ ቅዱስ ሊኖረን ይገባል:: ሦስተኛ፣ በውስጡ የተጻፈውን ትእዛዝ ፈጽሙ::
የእግዚአብሔG ቃል ቤተመቅደስን ለመገንባት የሚያስፈልጓችሁን ነገሮች በሙሉ ይነግራችኋል::
በሐጌ 1:2 እግዚአብሔር፣ «ይህ ሕዝብ የእግዚአብሔር ቤት የሚሠራበት ዘመን አልደረሰም ይላል» ሲል ይናገራል:: ሰዎች የእግዚአብሔርን ቤት መሥራት አስፈላጊ አይደለም የሚሉት ለምንድነው? ለመሆኑ ቤተመቅደስ ምንድነው? ቤተመቅደስ የክርስቶስ አካል ነው:: እርሱም እኛው ነን:: እኔና አንተ! እኛ ካላደረግነው ይህንን ቤተመቅደስ ማን ሊገነባ ይችላል? ይህ የኛ ኃላፊነት ነው! እኛ ቤተክርስቲያን ነን! የቤተክርስቲያን አካል እንደመሆናችን፣ ቤተክርስቲያን በጥሩ ሁኔታ እንድትቀጥል የማድረግ ኃላፊነት አለብን:: ይህንን የምናደርገው እንዴት ነው? የመምሪያ መጽሐፉን በመከተል ነው::

1. የክርስቶስን አካል ክፍሎች በማነጽ:: በወጣት ቡድናችን ውስጥ አንድነትና መስማማት እንዲኖር ጣሩ:: ሌሎች የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚያገኙበት መጠጊያ ልንሆን ይገባል::
2. የመምሪያ መጽሐፉን በማንበብ:: በየቀኑ የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት ራሳችንን ማሰልጠን አለብን::

በሐጌ ዘመን እንደነበሩት ሰዎች፣ አንዳንዶቻችሁ መጽሐፍ ቅዱስ ሳለማጥናት የተለያዩ ምክንያቶችን ታቀርባላችሁ:: የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት ጊዜ የማናጠፋ ከሆነ፣ ቤተመቅደሱን እያነጽን አይደለንም:: የሐጌ ዘመን ሰዎች ማመኻኛዎችን በማቅረብና የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ ከመገንባት ውጭ ያሉትን ተግባራት በማከናወን የተካኑ ነበሩ:: ቤተመቅደሱን ለመገንባት ጊዜ እንደሌላቸው ለሐጌ ገለጹለት:: የሚፈልጓቸውን ሌሎች ተግባራት ለማከናወን ግን ብዙ ጊዜ ነበራቸው:: ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር ተፈጥሯዊ በረከቶችን ነፈጋቸው::
«በውኑ ይህ ቤት ፈርሶ ስለ እናንተ ራሳችሁ በተሸለሙ ቤቶቻችሁ ለመኖር ጊዜው ነውን?» (ቁ.4):: እግዚአብሔር በመቀጠልም፣ «ልባችሁን በመንገዳችሁ ላይ አድርጉ:: ብዙ ዘራችሁ ጥቂትም አገባችሁ» (ቁ. 5-6):: ወደ ቤተክርስቲያን መጥታችሁ ትክክለኛ ነገሮችን ታደርጋላችሁ:: ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ስታነቡ ስሜት አይሰጣችሁም:: ስትጸልዩ፣ ጸሎታችሁ ጣሪያው ላይ ነጥሮ ይመለሳል:: ችግሩ ምንድነው? ልንሰጥ የሚገባንን ለእግዚአብሔር

አለመስጠታችን ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳችንን ለማንበብና ከሰማያዊ አባታችን ጋር በጸሎት ለማሳለፍ ጊዜ ስንወስድ፣ የመምሪያ መጽሐፉ የሚያስተላልፈውን መልእክት እንድንረዳ በማገዝ ይባርከናል፡፡ አሥራታችንንና ምጽዋታችንን በምንሰጥበት ጊዜ፣ እርሱ ሊገለጽ በማይችል መንገድ ይባርከናል፡፡

ለእግዚአብሔር ከገቢያችን አሥር እጅ መስጠት የክርስቲያኖች ግዴታ ነው፡፡ ለእግዚአብሔር የምንሰጠው ከትርፋችን ሊሆን አይችልም፡፡ ገቢያችን ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ንብረት ነው፡፡ ንብረትነቱ የርሱ ስለሆነ፣ የመስጠት ወይም ያለመስጠት ምርጫ የለንም፡፡ አሥሩን እጅ ሳንሰጥ ስንቀር እግዚአብሔርን መስረቃችን ነው፡፡ መባዎቻችን ለኛ ግድ የሚለው አምላካችን የምናቀርባቸው የፍቅር መግለጫዎች ናቸው፡፡

ከሕዝቡ መካከል ጥቂቶቹ የሐጌን አመራር ተቀበሉ፡፡ ከልባቸው ተነቃቅተው ያመልኩ፣ ለሌሎች እጆቻቸውን ይዘረጉ፣ እርስ በርሳቸው ይደጋገፉ፣ አሥራታቸውን ይከፍሉና የፍቅርና የልግስና መባዎች ይሰጡ ጀመር፡፡

በዚህም ቤተመቅደሱን ማነጽ ጀመሩ! እጅግ አስደሳች ነገር ተከሰተ! እግዚአብሔርም ሕዝቡን ባረከ! ብዙ እህል ሰጣቸው፡፡ ከሁሉም በላይ፣ ቤተመቅደሱን ዳግም ለመገንባት እንዲነሣሡ ረዳቸው፡፡

ይህ የኋልዮሽ ጉዞ ነው ብለን ልናስብ እንችላለን፡፡ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ የማጥናትና በልግስና የመስጠት ፍላጎት እንዲያሳድርብን እንጸልያለን፡፡ እግዚአብሔር ጥሩ ስሜት ቢኖረንም ባይኖረንም እንድንታዘዘው እየጠየቀን፣ በልባችን ውስጥ ፍላጎትን እንዲያሳድር አጥብቀን እንሻለን፡፡ እርሱ ስንታዘዘው ይባርከናል፡፡ አሥራታችሁንና መባችሁን የመስጠት ፍላጎት ላይኖራችሁ ይችላል፡፡ አንዳንዶቻችሁ በሥራ ወይም በትምህርት ላይ ደክማችሁ ስለምትውሉ መጽሐፍ ቅዱሳችሁን የማንበብ ፍላጎት ላይኖራችሁ ይችላል፡፡ ስለሆነም ፍላጎቱ ይመጣል ብላችሁ ከምትጠብቁ እግዚአብሔርን ታዘዙትና ማንበባችሁን ቀጥሉ፡፡ ትእዛዙን ስትከተሉ ፍላጎቱ እንደሚመጣ እመኑ፡፡

እግዚአብሔር ቤተመቅደሱን እንድንሠራ ያዘናል፡፡ ይህንኑ እያደረጋችሁ ነውን? ወይስ በሐጌ ዘመን እንደነበሩት ሰዎች ቁጭ ብላችሁ ማመኻኛዎችን እየፈጠራችሁ ነው? ለመሆኑ ቤተመቅደሱን የምትሠሩት እንዴት ነው? አስፈላጊዎቹ ነጥቦች ከዚህ በታች ተሰጥተዋል?

1. የምትረዱትንና የምትከሩበትን የመምሪያ መጽሐፍ (መጽሐፍ ቅዱስ) አግኙ፡፡
2. አንብቡት! በውስጡ ያሉትን ትእዛዛት ፈጽሙ፡፡
3. ቤተመቅደሱን ለመገንባት ትእዛዛቱን ከተከተላችሁ፣
   ሀ. በክርስቶስ አካል ውስጥ ያሉትን ታንጻላችሁ፡፡



   ለ. አሥራታችሁን ትከፍላላችሁ፡፡
   ሐ. መባዎችን በልግስና ትሰጣላችሁ፡፡

እኛ የርሱ ቤተመቅደስ ነን፡፡ ቤተመቅደሱንም እንድንሠራ አዞናል፡፡ ይህን ተግባር ካላከናወንን፣ ሥራው ከዳር ሊደርስ አይችልም፡፡ ቤተመቅደሱን ትገነባላችሁ? በየዕለቱ በቃሉ ውስጥ ጊዜ በቂ ጊዜ ታሳልፋላችሁ? አሥራታችሁንና የልግስና መባዎችን ትሰጣላችሁ? እስኪ አሁኑኑ ቤተመቅደሱን ለማነጽ ቃል ኪዳን እናድርግ፡፡ (በቃል ኪዳን ጸሎት ፈጽም፡፡)

# የጥፋት ቤተመቅደስ

## (ክፍል ሁለት)

## ከሱዚ ሽለንበርገር

**ዓላማ፡** ወጣቶች የክርስቶስን አካል መንከባከብና ማነጽ አስፈላጊ መሆኑን እንዲገነዘቡ ለማገዝ።

**ዝግጅት**

1. ከስብሰባው አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ ስለሚከተሉት ነገሮች ማስታወቂያ ተናገር።
   ሀ. የቡድን ውድድሮች
   ለ. እያንዳንዱ ተሳታፊ ትራስና የትራስ ልብስ እንዲያመጣ።
   ሐ. በስብሰባው ላይ ለሚገኙና እንግዶችን ይዘው ለሚመጡ ቡድኖች ነጥቦች እንደሚሰጡ።
3. ትንቢተ ሐጌን፣ 1ኛ ዜና 28:10፣20፣29:1፣1ኛ ቆሮንቶስ 3:10-15 አጥና።

**የቡድን እንቅስቃሴዎች** - ስብሰባውን ለመጀመር ከሚከተሉት እንቅስቃሴዎች አንዱን ወይም ሁሉንም ተጠቀም።

1. **በትራስ መደባደብ።** ስብሰባው ከመጀመሩ ቀደም ብለህ ሁለት ልጆች ከወለሉ ከፍ ብለህ የሚቆሙበትን ጣውላ አዘጋጅ። ከእያንዳንዱ ቡድን አንዳንድ ተወዳዳሪ ምረጥ። በአንድ ጊዜ ሁለት ሰዎች ከጣውላው ላይ እንዲወዳደሩ አድርግ። ምልክት ስትሰጥ፣ ሁለቱ ተጋጣሚዎች በትራስ መደባደብ ይጀምራሉ። የጨዋታው ዓላማ አንዱ ልጅ ሌላውን ከጣውላው ወደ መሬት እንዲጥለው ማድረግ ነው። የየምድቡን አሸናፊ እያጋጠምህ የኋላ ኋላ አንድ አሸናፊ እንዲቀር አድርግ።
2. **እግርን ከትራስ ልብስ ውስጥ አድርጎ የመሮጥ ውድድር።** ቡድኖቹን በአንድ መስመር አሰልፋቸው። ምልክት ስትሰጥ፣ ከእያንዳንዱ ቡድን የመጀመሪያው ልጅ እግሩ ከትራስ ልብስ ውስጥ እንደገባ እየዘለለ ወደ ክፍሉ (ሜዳው) ሌላኛው ጫፍ ይሄዳል። የመጀመሪያው ልጅ ውድድሩን ሲጨርስ የቡድኑ ተረኛ የትራስ ልብሱን ተቀብሎ ውድድሩን ይቀጥላል ከሁሉም በፊት ውድድሩን የሚጨርስ ቡድን አሸናፊ ይሆናል።
3. **እንቁላል በማንኪያ ይዞ የመሄድ ውድድር።** ለእያንዳንዱ ቡድን የተቀቀለ እንቁላልና ማንኪያ አድል። ቡድኖቹን በአንድ መስመር አሳልፋቸው። ምልክት በምትሰጥበት ጊዜ፣ ከእያንዳንዱ ቡድን እያንዳንዱ ልጅ እንቁላሉን በማንኪያ ይዞ ወደ ግብ መስመሩ ይደርስና ይመለሳል። እንቁላሉ ከወደቀበት ልጁ ከእንደገና ይጀምራል። ከሁሉ አስቀድሞ የጨረሰ ቡድን አሸናፊ ይሆናል።



ለዓይነት ያህል ጥሬ እንቁላል መጠቀም፣ ልጆቹ ከመሳመድ ይልቅ በፍጥነት እንዲሄዱ ወይም ዘለል ዘለል እያሉ እንዲጓዙ ልታደርግ ትችላለህ።

**ሽግግር፡** (እነዚህ ወደ መልእክቱ እንድትሸጋገር የሚያግዙህ ናቸው።)

1. **ማስታወቂያዎች።** በያንዳንዱ ውድድር አሸናፊ የሆኑትን ቡድኖች ተናገር። ለአሸናፊዎቹ ቡድኖች ብዙ ነጥቦች ወይም አነስተኛ ነገር ሸልም። የተሻሻለውን የቡድን ነጥብ ድምር ስጥ።
2. **የቡድን ዝማሬ።**
3. **ትውውቅ።** ወጣቶቹ ቢያውቁት ይጠቅማቸዋል ብለህ የምታስበው የቆየ የቤተክርስቲያን አባል ካለ፣ የአምስት ደቂቃ ምስክርነት ወይም ቃለምልልስ እንዲሰጥ አድርግ። ይህ ወጣቶች በሌላ መንገድ ሳያውቁ የማይችሏቸውን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የበሰሉ አዋቂዎች እንዲያውቁ ይረዳቸዋል።
4. **የቡድን ውይይት**

*«የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ተሰጠኝ መጠን እንደ ብልሃተኛ የአናጺ አለቃ መሠረትን መሠረትሁ፣ ሌላውም በላዩ ያንጻል። እያንዳንዱ ግን በእርሱ ላይ እንዴት እንዲያንጽ ይጠንቀቅ። ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ማንም ግን በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ቢሆን በብርም በከበረ ድንጋይም በእንጨትም በሣርም ወይም በአገዳ ቢያንጽ፣ የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል በእሳት ስለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና፣ የእያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል። ማንም በእርሱ ላይ ያነጸው ሥራ ቢጸናለት ደመወዙን ይቀበላል የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን ይጎዳበታል እርሱ ራሱ ግን ይድናል ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል።»* (1ኛ ቆሮንቶስ 3:10-15)። ጳውሎስ ቤተመቅደሱን ስንገነባ ወይም ከክርስቶስ አካል ጋር ስንሠራ በጣም መጠንቀቅ እንዳለብን ያስጠነቅቀናል። ሁላችንም የጌታን ቤተመቅደስ የመገንባት ተልዕኮ ተሰጥቶናል። ነገር ግን ንጹሕ ልቦና ኖሮን በትክክለኛ ቁሳቁሶች በመጠቀም ይህንኑ ልናደርግ ይገባል። ብዙ ሰዎች ለራሳቸው ጥቅም ወይም የሕዝቡን እውቅና ለማግኘት ሲሉ የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ ይገነባሉ። ለቤተክርስቲያንም የተለያዩ ነገሮችን ያደርጋሉ። ሌሎች ደግሞ ትክክለኛ ያልሆኑትን ቁሳቁሶች ይጠቀማሉ። በ1ኛ ዜና ንጉሥ ዳዊት ልጁ ሰሎሞን የጌታን ቤተመቅደስ እንዲገነባ በማዘዝ ከራሱ መዝገብ ጠቃሚ ቁሳቁሶችን ሲሰጠው እንመለከታለን። ክርስቶስን ከልባችን የምንከተል ከሆን አንዳንድ መሥዋዕቶችን መክፈል አለብን። ዓላማዊ ተግባራትን እያካሄድን የጌታን ቤተመቅደስ ልንገነባ አንችልም።

**የመወያያ ጥያቄዎች:** ወጣቶቹን በአነስተኛ ቡድኖች ከፋፍለህ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ አወያያቸው::

1. የቤተክርስቲያን መሠረት ምንድነው?
2. በቤተክርስቲያን መሠረት ላይ መገንባት የሚቻለው እንዴት ነው?
3. የሥራችን ጥራት የሚገለጠው እንዴት ነው?
4. የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ማነው?
5. የቤተመቅደሱ ዓላማ ምንድነው?
6. የሚያጠፋት ምን ይሆናሉ?
7. ከክርስቶስ ሌላ ሰዎች ለግንባታ መሠረትነት ለመጠቀም የሚሞክሯቸው ሌሎች ነገሮች ምን ምንድናቸው?

7. **ጸሎት:** ከመልእክቱ በፊት አንድ ሰው እንዲጸልይ ጋብዝ::

**መልእክት: «የጥፋት ቤተመቅደስ» (ክፍል ሁለት)**

*(ለእያንዳንዱ ልጅና ለሌሎች ሰዎች የእንጨት ጡቦችን አዘጋጅ::)*

ባለፈው ስብሰባችን፣ ስለ ጌታ መቅደስና ይህንኑ መቅደስ እንዴት መገንባት እንደሚቻል ተመልክተናል:: ዛሬ የቤተመቅደሱን ግንባታ ስለመቀጠልና ቤተመቅደሱን በማይገነቡ ሰዎች ላይ ምን እንደሚደርስ እንማራለን::

በ1ኛ ዜና፣ እግዚአብሔር ሰሎሞን ቤተመቅደሱን እንዲገነባ ይጠራዋል:: በእግዚአብሔር የተቀደሰ ቤተመቅደሱን ለመገንባት መጠራቱ ምንኛ ታላቅ ክብር ነው! ዛሬ እግዚአብሔር ቤተመቅደሱን እንድትገነቡለት ይጠራችኋል:: እስኪ ከ1ኛ ዜና 28:10 ይህንን ጥሪያችንን እንመልከት:: *«አሁንም፣ እነሆ፣ እግዚአብሔር ለመቅደስ የሚሆን ቤትን ትሠራ ዘንድ መርጦሃልና ጠንክረህ ፈጽመው::»*

ሰሎሞን፣ አንተ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ነህ:: መስፍን አንተ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ነህ:: አ-ን-ተ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ነህ! ይህ የቡድንም የግልም ተልዕኮ ነው:: የወጣት ቡድናችን የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ነው:: እያንዳንዱ ሰው ደግሞ በግል ደረጃ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ነው:: የማዕዘን ድንጋይ፣ራስ፣ መሠረት የሆነው ክርስቶስ የቤተመቅደሱ ዋንኛ አካል ነው::

በየቡድናችሁ ተከፋፍላችሁ በፍጥነት የፒራሚድ ቅርጽ እንድትሠሩ ብጠይቃችሁ፣ እያንዳንዳችሁ የፒራሚዱ ሕያው አካል ትሆናላችሁ:: በክርስቶስ አካል ውስጥም ሁኔታው ተመሳሳይ ነው:: እኛ የክርስቶስ አካል፣ ቤተመቅደስ ነን:: እያንዳንዳችን በእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ውስጥ ሕያው ድንጋዮች ነን::

*«ዳዊትም ልጁን ሰሎሞንን:-ጠንክር፣ አይዞህ፣ አድርገውም አምላኬ እግዚአብሔር አምላክ ከአንተ ጋር ነውና አትፍራ፣አትደንግጥም ለእግዚአብሔርም ቤት አገልግሎት የሚሆነው ሥራ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ እርሱ አይተውህም፣ አይጥልህምም::»* (1ኛ ዜና 28:20)::

እግዚአብሔር የማይቻለውን እንድናደርግ እየጠየቀን አይደለም:: የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ ልንገነባ እንችላለን! እኛ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ሕያዋን ድንጋዮች ነን:: እኛ - የወጣት ቡድናችን:: የጌታ ቤተመቅደስ ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያገኙበት ስፍራ ነው:: ይህ የደስታና የመበረታቻ ስፍራ ነው:: ይህ መታነጽ፣ ፍቅርና ዋስትና ተትረፍርፎ የሚገኝበት ቦታ ሊሆን ይገባል:: የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ማለትም ይኸው ነው:: እኛም ይኸው ነን:: እኛ እንደዚህ ነንን? የወጣት ቡድናችን ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያገኙ ብት፣ የደስታና የመታነጽ ስፍራ መሆን አለበት:: እኛ እንደዚህ ዓይነት ቤተመቅደስ ነንን? ንጉሥ ዳዊት ልጁ ሰሎሞን ቤተመቅደሱን እንደሚገነባ እንዳወጀ ሁሉ፣ እግዚአብሔር ዛሬ እኛ ቤተመቅደሱን እንደምንሠራ አውጇል:: እግዚአብሔር በናንተ ያምናል! እግዚአብሔር በዚህ ታላቅ ተግባር ውስጥ እንድትሳተፉ ይጠይቃችኋል:: ሥራውን በሚገባ ለማከናወን የሚያስችላችሁን ነገሮች በሙሉ ያሟላላችኋል:: የምታገለግሉት የሚያስችላችሁን አምላክ ነው:: እርሱ ይህንን ተግባር ለማከናወን እንደምትችሉ ያውቃል::

በሕዝብ ፊት ወላጆቻችሁ ስለ ችሎታችሁ መናገራቸው ሊያሳፍራችሁ ይችላል:: ንጉሥ ዳዊት በሰሎሞን ላይ ያደረገው ይህንኑ ነው:: ዛሬም እግዚአብሔር በናንተ ላይ እያደረገ ያለው ይህንኑ ነው:: ይህንን ጥቅስ ሳነብላችሁ በልባችሁ የሰሎሞን ስም በተጻፈበት ስፍራ ስማችሁን አስገቡ:: «ንጉሡም ዳዊት ለጉባኤው ሁሉ እንዲህ አለ:- እግዚአብሔር ብቻውን የመረጠው ልጄ ሰሎሞን ገና ብላቴና ለጋ ነው ሕንጻው ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክ ነው እንጂ ለሰው አይደለምና ሥራው ታላቅ ነው::» (1ኛ ዜና 29:1)::

ይህ ምንኛ ታላቅ ክብር ነው! ምንኛ አስደሳች ኃላፊነት ነው! እግዚአብሔር ቤተመቅደሱን እንድትሠሩ መርጧችኋል! እግዚአብሔር ቤተመቅደሱ እንድትሆኑ መርጧችኋል! ይኼ ከእግዚአብሔር የተሰጠን አስደሳች ትእዛዝ ነው:: ይኼ ትእዛዝ እንጂ ምርጫ አይደለም:: ቤተመቅደሱን ሥሩ ተብለናል:: አለቀ:: «ከተመቻችሁ»፣ «ትርፍ ጊዜ ካላችሁ» ቤተመቅደሱን ሥሩ አልተባልንም:: ነገር ግን «ቤተመቅደሱን ሥሩ» ተብለን ቅድመ ሁኔታ በሌለው መልኩ ታዘናል!

ቤተመቅደሱን እንዴት ትገነባላችሁ? ምን ዓይነት መሣሪያዎች አሏችሁ? መዘመር ትችላላችሁ? ምስክርነት መስጠት ትችላላችሁ? ደህና አድርጋችሁ ማዳመጥ ትችላላችሁ? አንዳንዶቻችሁ መልካም ለዛ ያለው ቀልድ የመናገር ችሎታ አላችሁ:: ሌሎቻችሁ ዝምተኛ፣ አፍቃሪና ልበ ስሉ ናችሁ::

ሁሉም ሰው ቤተመቅደሱን ሊያንጽ ይችላል። ቤተመቅደሱን ለመገንባት ሀብታችንን መጠቀም አለብን። ቤተመቅደሱን ለመገንባት የድርሻችንን እየተወጣን ነን? የግል ንብረቶቻችሁን እየተጠቀማችሁ ነውን? ንብረቶቻችንን ስለመጠቀም ንጉሥ ዳዊት የተናገረውን አንብብ። «እኔም እንደ ጉልበቴ ሁሉ ለአምላኬ ቤት ለወርቁ ዕቃ ወርቁን፣ ለብሩም ዕቃ ብሩን፣ ለናሱም ዕቃ ናሱን፣ ለብረቱም ዕቃ ብረቱን፣ ለእንጨቱም ዕቃ እንጨቱን፣ ደግሞም መረግድንና በፈርጥ የሚገባ ድንጋይን፣ የሚለጠፍ ድንጋይን፣ ልዩ ልዩመልክ ያለውንም ድንጋይ፣ የከበረውንም ድንጋይ ከየዓይነቱ፣ ብዙም እብነበረድ አዘጋጅቻለሁ። ከዚህም በላይ ደግሞ የአምላኬን ቤት ስለወደድሁ፣ ለመቅደሱ ካዘጋጀሁት ሁሉ ሌላ የግል ገንዘቤ የሚሆን ወርቅና ብር አለኝና ለአምላኬ ቤት ሰጥቼዋለሁ።» (1ኛ ዜና 29:2-3)።
የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ መገንባት መሥዋዕትነትን ይጠይቃል። እግዚአብሔርን ለማስከበር የግል ስጦታዎቻችንንና ችሎታዎቻችንን መጠቀም አለብን። እርሱ የሰጠንን ችሎታና ብቃት መልሰን ልንሰጠው ይገባል። ሀብቶቻችንንና ራሳችንን ለእግዚአብሔር አሳልፈን ልንሰጥ ይገባል። ብዙዎቻችሁ ለእግዚአብሔር ራሳችሁን ሰጥታችኋል። ነገር ግን አንዳንዶቻችሁ ለእግዚአብሔር ሁለንተናችሁን ለመስጠት እየታገላችሁ ይሆናል።
ዛሬ መምረጥ ትችላላችሁ። የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ ለመገንባት ከመረጣችሁ፣ መንፈሳዊ ቤተመቅደስ ትሆናላችሁ። ቤተመቅደሱን ለማፍረስ ከመረጣችሁ፣ የጥፋት ቤተመቅደስ ትሆናላችሁ። ቤተመቅደሱን ለመገንባትና በዙሪያችሁ ላሉት ሰዎች አምንታዊና የሚያንጽ ምሳሌነት ለማሳየት የምትፈልጉ ሁሉ፣ መንፈሳዊ ቤተመቅደስ እንዲኖረን ታደርጋላችሁ። በክርስቶስ አካል ውስጥም ሆነ በዓለም ላሉት ወገኖች እጆቻችሁን በመዘርጋት፣ የቆሰሉትን ልቦች ታክማላችሁ። የወጣት ቡድናችን መንፈሳዊ ቤተመቅደስ ሊሆን የሚችለው በዚህ መልኩ ነው። እያንዳንዳችን እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ልናንጸባርቅ የምንችለው በዚህ መልኩ ነው።
ነገር ግን ለሌሎች እጆቻችሁን ሳለመዘርጋት በመምረጥ የአጥፊነትን ሚና የምትጫወቱ፣ በራሳችሁ ዓለም ተሸፍናችሁ በአሉታዊነታችሁ የምትጸኑ፣ እግዚአብሔር ያጠፋችኋል። ስጦታዎቻችሁን ለራሳችሁ ጥቅም በማዋል፣ ወይም ቡድኑን በመከፋፈል፣ መንፈሳዊውን ቤተመቅደስ ወደ ጥፋት ቤተመቅደስነት እየለወጣችሁት ነውና።
«በመዘምራን ቡድን ውስጥ አልዘምርም።»
«የለበሰችውን እስቀያሚ ቀሚስ ታየዋለህ?»
«ይኼ ደደብነት ነው!»
«በቁሙ ቀርቶ በሞቱም ከሱ ራሳ ጋር አልገኝም።»
አሉታዊ አስተያየቶችና መጥፎ ባሕርያት የእግዚአብሔርን ቅዱስ ቤተ መቅደስ ያፈርሳሉ። 1ኛ ቆሮንቶስ 3:16-17 እንዳስጠነቀቀው፣



«የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፣ ያውም እናንተ ናችሁ።»
በሕይወታችሁ ውስጥ እግዚአብሔር የሚያደርበት ስፍራ የሚያኮራችሁ ነውን? ቤቱን ለማጽዳት ትፈልጋላችሁ? እኛ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ነን። እኛ ሕያዋን ድንጋዮች ነን። በቤተመቅደሱ ላይ መገንባት የኛ ኃላፊነት ነው። ስለሆነም፣ ቤተመቅደሱን እንጹት። በንጽሕናም ጠብቁት።

## ቤተመቅደሱን የምታንጹት እንዴት ነው?

1. የመምሪያውን መጽሐፍ (መጽሐፍ ቅዱስ) በማግኘት
2. በየዕለቱ ሳታቋርጡ በማንበብ
3. ትእዛዛቱን በመፈጸም
4. እግዚአብሔር የሰጣችሁን ችሎታ፣ ብቃትና ራሳችሁን ጭምር በመጠቀም ምርጫው የናንተው ነው። ይኸውም ቤተ መቅደሱን ለመገንባት የድርሻችሁን መወጣትና መንፈሳዊ ቤተመቅደስ ለመሥራት መምረጥ ወይም የጥፋት ቤተመቅደስ ለመሥራት የበኩላችሁን አሉታዊ ሚና ለመጫወት መምረጥ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ብናፈርስ እግዚአብሔር እንደሚያፈርሰን በመግለጽ ያስጠነቅቀናል። ለመዝጊያ ያህል አንድ ጥቅስ አነብላችኋለሁ። *(1ኛ ቆሮንቶስ 3:10-17ን አንብብላቸው።)*

አሁኑኑ ራሶቻችሁን ዝቅ አድርጋችሁና ዓይኖቻችሁን ጨፍናችሁ ከክርስቶስ ጋር ያላችሁን ግንኙነት እንድትመረምሩ እጠይቃችኋለሁ። ቤተመቅደሱን ለመገንባት ምን እያደረጋችሁ ነው? ቅዱስ፣ መንፈሳዊና ሕያው ድንጋይ ናችሁ? በየቀኑ የመምሪያ መጽሐፉን ለማንበብ ራሳችሁን አሠልጥናችኋልን? ትእዛዛቱን እየፈጸማችሁ ነው? ምን ዓይነት የቤተመቅደስ ድንጋዮች ናችሁ? ሰዎች እግዚአብሔርን በሚያገኙበት ስፍራ ነው ያላችሁ? የደስታና የመበረታቻ ምንጮች ናችሁ? ሀብቶቻችሁን እየተጠቀማችሁ ነው? ራሳችሁን ጭምር? እግዚአብሔር ሁለንተናችሁን ተቆጣጥሮታል? እናንተ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ናችሁ። የጽዳት ተግባር ለማካሄድ ትፈልጋላችሁ? ዓይኖቻችሁን ጨፍናችሁ እንዳቀረቀራችሁ፣ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ዓይነት ሕያዋን ድንጋዮች እንድትሆኑ እጋብዛችኋለሁ።
ዛሬ ጥቂት ጡቦችን ይዤ መጥቻለሁ። ጡቦቹም እዚህ መድረኩ አካባቢ ተቀምጠዋል። ሁላችሁም ወደዚህ መጥታችሁ አንዳንድ ጡብ እንድትወስዱና ለእግዚአብሔር ሕያዋን ድንጋዮች ለመሆናችሁ ማስታወሻ አድርጋችሁ እንድትጠቀሙበት እፈልጋለሁ። ጡቦቹን

ዘወትር በምታዮዋቸው ስፍራ እንድታስቀምጧቸው እጠይቃችኋለሁ። ጡቦቹን ይዛችሁ ከመሄዳችሁ በፊት ግን ተንበርከካችሁ ብቻችሁን ከእግዚአብሔር ጋር እንድትነጋገሩ እፈልጋለሁ። ቅድሚያ የምትሰጧቸው ነገሮች ትክክለኛ ስፍራዎቻቸውን መያዛቸውን አረጋግጡ። አስፈላጊ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ሕይወታችሁን እንዲያጠራ ፍቀዱለት። አሁን መጥታችሁ ጡቦቹን ተቀበሉ። *(መልእክቱን ከማቅረብህ በፊት ጡቦቹ ከመድረኩ አካባቢ መድረሳቸውን አረጋግጥ።)*

*መዝጊያ (ሁሉም ጡቦቹን ከወሰዱ በኋላ፣ በጸሎት ፈጽም ወይም ምስክርነት የሚሰጥ ሰው ካለ ጠይቅ።)*



# ታላቅ ሁን
## ከቴድ ቴይለር

**ዓላማ:** በእግዚአብሔር እይታ ታላቅነት አገልጋይነት መሆኑን ለማስተማር።

**ተስማሚ ጊዜ:** ወጣቶች አገልግሎት ከመጀመራቸው በፊት ቢማሩት መልካም ነው። ቤቶችን ማጽዳት፣ ቀለም መቀባት፣ ወይም የአካል ጉዳተኞችንና የአዛውንቶችን ግቢዎች ማሳመር እምነታችሁን ከሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል መልካም አጋጣሚ ሊሆን ይችላል።

**ዝግጅት**

1. ስብሰባው ከመካሄዱ አንድ ሳምንት አስቀድመህ ስለሚከተሉት ነገሮች ማስታወቂያ ተናገር።
   ሀ. እያንዳንዱ ቡድን ወይም የቡድን አባል ከሚከተሉት ነገሮች አንዱን ይዞ መምጣት አለበት።
   - በአካባቢው ወይም በአገሪቱ ወይም በቴሌቪዥን ላይ በጣም ገኖ የሚታወቅ ሰው ፎቶ።
   - በትምህርት ቤት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠውን ነገር።
   - በዓለም ከፍተኛ ግምት የሚሰጠውን ነገር።
   - ቡድኖቹ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ለማግኘት ከቻሉ ነጥብ እንደሚሰጣቸው ንገራቸው።

   ለ. እንግዶችን ይዞ ለሚመጣ ወጣት ሁሉ ነጥብ ይሰጠዋል።
   ሐ. ስለ አገልጋይነት የሚናገሩትን እነዚህን ጥቅሶች አጥና፡ ማቴዎስ 18:1-6፣ 19:25-28፣ 23:11-12፣ ሉቃስ 22:24-26፣ ዮሐንስ 13:1-15።

**የቡድን እንቅስቃሴዎች:** ወጣቶቹ ከሚከተሉት ነገሮች አንዱን ወይም ሁሉንም በማከናወን በእንቅስቃሴዎቹ ላይ ይሳተፉ።

1. የሰረገላ ውድድር። ይህ ውድድር በክፍሉ ውስጥ ወይም ከክፍሉ ውጭ ሊካሄድ ይችላል። ሁለት ልጆች እጆቻቸውን አይይዘው እንዲቆሙና ሦስተኛው ልጅ በሁለቱ ልጆች ላይ እንዲወጣ አድርግ። ከዚያም ቡድኖቹ የሩጫ ውድድር ያካሂዳሉ።
2. በቡድን ሰው ተሸክሞ የመሮጥ ውድድር። እያንዳንዱ ቡድን ከአባሉቱ አንዱን ከራሱ ላይ በማውጣት አሥር ሜትር ያህል ይሮጣል። (የመጨረሻው ስፍራ ምልክት ሊደረግበት እንደሚገባ አስታውስ።) የቡድኖቹ አባላት ብዙ ከሆኑ፣ 8

ልጆች አንዱን ልጅ ተሸክመው እንዲሄዱና እንዲመለሱ፣ ከዚያም ቀሪዎቹ የቡድኑ አባላት ተመሳሳይ ተግባር እንዲፈጽሙ አድርግ። ምልክት እስከተደረገበት ስፍራ ድረስ በቀዳሚነት አሥር ሰዎችን ተሸክሞ ያደረሰ ቡድን አሸናፊ ይሆናል። ቡድኑ አሥር አባላት ከሌሉት አንዱን ልጅ ከአንድ ጊዜ በላይ ሊሸከም ይችላል።

3. የሥዕል ውድድር። እያንዳንዱ ቡድን አንድ ተወካይ ወደ መሪው ይልካል። መሪውም የአንድን ዕቃ ስም ወይም ቃል ይነግራቸዋል። ምልክት በሚሰጥበት ጊዜ፣ ወደየቡድኖቻቸው ሮጠው በመሄድ የተነገራቸውን ነገር ይሥላሉ። ቃላት መጠቀም አይችሉም። የቡድኑ አባላት የተሣለው ነገር ምን እንደሆነ ይገምታሉ። የሣለው ልጅ መልሱን እስኪያውቁት ድረስ ምንም አይናገርም። ከሁሉ አስቀድሞ በግምት ያወቀ ቡድን ነጥብ ይሰጠዋል። በቀዳሚነት 10 ወይም 15 ጊዜ ያወቀ ቡድን አሸናፊ ይሆናል።
4. የአገልጋይ ፍለጋ ዓረፍተነገሮች ውድድር። ለሁሉም ልጆች ከታች ያለውን ዓረፍተነገር ስጣቸው። እያንዳንዱ ልጅ በትክክል ራሱን ከሚገልጸው ዓረፍተነገር ጎን ፊርማውን ያስቀምጣል። በቀዳሚነት ሁሉም ወይም አብዛኞቹ ዓረፍተነገሮቹ የተፈረሙለት ቡድን አሸናፊ ይሆናል። ልጆቹ በትክክል የነሱን ሁኔታ የሚገልጹ ሆነው ካገኟቸው ከአንድ የሚበዙትን ፊርማዎች ሊያሰፍሩ ይችላሉ።
   የአገልጋይ ፍለጋ ዓረፍተነገሮች፡ 1) ዛሬ ለአንድ ሰው አልጋ አንጥፌአለሁ። 2) ዛሬ አንድ ሰው ወደ ወጣቶች ስብሰባ ጋብዣለሁ። 3) ዛሬ ጓደኛዬ ታሪክ ሲተርክ ሰምቻለሁ። 4) ዛሬ እማማን ወይም አባባን «አመሰግናለሁ» ብያለሁ። 5) አብዛኞቹን እንግዶች አነጋግራለሁ። 6) መስኮቶችን መወልወል ያስደስተኛል። 7) ጨለማ እፈራለሁ። 8) ከወንድሜ/እህቴ ጋር ብዙ እጣላለሁ። 9) ልብስ ማጠብ ያስደስተኛል። 10) ዛሬ ምግብ የተበላበትን ዕቃ አጥቤአለሁ። 11) ባለፈው ጊዜ ከጓደኞቼ ጋር አንድ ነገር ሳደርግ በጣም ተቸግሬ ነበር። 12) ዛሬ መጽሐፍ ቅዱሴን አንብቤአለሁ።

ሽግግር፡ እነዚህ ከፍተኛ ፍጥነት ከሚታይባቸው እንቅስቃሴዎች ወደ መልእክቱ ለመሸጋገር የሚረዱህ ናቸው። የፈለግሃቸውን ያህል ተጠቅመህ ወደ መልእክቱ ተሻገር።

1. የቡድን ዝማሬ።
2. መባ የምትሰበስብ ከሆነ፣ ይህንን ጊዜ ተጠቀም። ይህንን በቡድኖች መካከል እንደሚካሄድ ውድድር አድርገህ ልትጠቀም ትችላለህ። መባው ለአካባቢው የአገልግሎት



ፕሮጀክት ወይም ለችግርተኛ አካባቢዎች ምግብና መድኃኒት ለሚያድል የረሃብና የእርዳታ መዋስንዋይ እንዲሰጥ አድርግ። ይህንን ለማድረግ ካሰብህ፣ በዚህ ላይ ስለሚካሄደው ውድድር ከአንድ ወይም ከሁለት ሳምንታት በፊት ማስታወቂያ መናገር ይኖርብሃል።
3. እያንዳንዱ ቡድን ትልቅና አስፈላጊ ነው ብሎ ያመጣውን ዕቃ አንተ ዘንድ እንዲያቀርብ አድርግ። ሁሉም ምርጥ ዕቃዎች እንዳመጡ እንድትመሰክርላቸው ይፈልጋሉ። አንተ ግን ዕቃዎቹን ለማምጣታቸው ነጥቦችን ስጣቸውና ዕቃዎቹን ለማስተማሪያ መሣሪያነት ተጠቀም።

**መልእክት፡ «እጅግ ውድ ነገር»**

*(ማስተማር ስትጀምር፣ ፎጣ አንሥተህ አንገትህ ላይ እሰር።)*
*(ወጣቶቹ በትምህርት ቤት ውስጥ እጅግ ጠቃሚዎች ናቸው ብለው ያመጧቸውን ነገሮች ተራ በተራ አንሣ። እግር ኳስ፣ ልብስ፣ የመማሪያ መጽሐፍ፣ ወዘተ. ስለ እያንዳንዱ ነገር የተለያዩ ነገሮችን ተናገር። የሚከተለው በምሳሌነት ሊያገለግልህ ይችላል።)*
ሁሉም ሰው ለመወደድና ተቀባይነት ለማግኘት ይፈልጋል። የትምህርት ቤት ኮከብ ተጨዋች መሆን ትልቅ ክብር ሊሆን ይችላል። ከ10 ዓመታት በኋላ ግን ያ ኮከብ ተጨዋች የነበረው ልጅ ሸበቶና ጥርስ ወላቃ ሆኖ ሊገኝ ይችላል። የትምህርት ቤት ክብር ብልጭ ብሎ የሚጠፋ በመሆኑ ዘለቄታዊ አይደለም።
*(እጅግ የተደነቁትን ሰዎች ፎቶ አንሣ።)* በማኅበረሰባችን ውስጥ ሰዎች ለሀብትና ለዝና ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ። በተቃራኒው የቴሌቪዥን መስኮት አጨናንቀው የሚታዩትን ሰዎች መከራዎች፣ ፍቺዎች፣ የፍርድ ቤት ክሶች፣ የአልኮልና የዕፅ ሱሶች፣ በግብረሥጋ ግንኙነቶች የሚተላለፉ በሽታዎችና ራስን የማጥፋት ሁኔታዎች ስንመለከት፣ አሳዛኝ ሆኖ እናገኘዋለን።
*(እንደ ገንዘብ፣ በዓለም እጅግ የተወደዱትን ነገሮች በማስመልከት የሚከተለውን ልትናገር ትችላለህ።)* ገንዘብ ኖሮኝ ሳይኖረኝም ኖሬ አውቃሁ። ገንዘብ ሲኖር ጥሩ ነው። ነገር ግን ሕይወታችሁን የሚቆጣጠር ከሆነ ባይኖራችሁ ይመረጣል። በሕይወታችን ውስጥ እጅግ ጠቃሚ የሆኑት ነገሮች በነጻ የምናገኛቸው ናቸው። ለምሳሌ ያህል ዓይኖቻችሁን ውሰዱ። በቅርቡ አንዲት ሴት ዓይኖቿን ለማጌጥ በተጠቀመችበት ሜክአፕ ሰበብ ለዓይነስውርነት ተዳርጋለች። ሜክአፑን በሠራው ኩባንያ ላይ በመሠረተችው ክስ ፍርድ ቤቱ የአንድ ሚሊዮን ዶላር ካሳ እንዲከፈላት አዟል። ይህች ሴት አንድ ሚሊዮን ዶላሯን ብትሰጣችሁ ዓይናችሁን ልትሰጧት ትፈቅዱላችሁ? እንደ እውነቱ ከሆነ፣ እጅግ ውድ ነገሮችን ያገኛችሁት

በነጻ ነው። ከአይታችሁ፣ ከማሽተት፣ ከመስማት ዓቅማችሁ፣ ወዘተ. ጋር ሲነጻጸሩ፣ ገንዘብና ሀብት ብዙ ትርጉም አይኖራቸውም።
*(ኃይልና ሥልጣንም ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ነገሮች ረግተው የማይቆዩ የጠዋት ጤዛዎች መሆናቸውን አብራራ። ቢያንስ ከተማሪዎችህ አንዱ መጽሐፍ ቅዱስ አምጥቶ ሊሆን ይችላል። ካልሆነም፣ የራስህን መጽሐፍ ቅዱስ ተጠቀም።)*
ከሁሉም የሚበልጠው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። ጌታችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተናገረው፣ «ሰማይና ምድር ያልፋሉ። ቃሌ ግን አያልፍም» (ሉቃስ 21:33)።

*የመወያያ ጥያቄዎች*

1. *አንተ የምታውቀው ታላቅ ሰው ማነው? ለምን?*
2. *እንድን ሰው ታላቅ የሚያደርገው ምንድነው?*
3. *ሰዎች ጊዜያቸውን ለሌሎች ሰዎች ለመስጠት የሚቸገሩት ለምንድነው?*
4. ክርስቶስ በከተማችን ውስጥ ቢኖርና ወደ ትምህርት ቤታችን ቢሄድ፣ በጊዜው ተጠቅሞ ምን ዓይነት ተግባራትን የሚፈጽም ይመስላችኋል?

እግዚአብሔር ነገሮችን የሚመለከተው ሙሉ በሙሉ ከኛ በተለየ መንገድ ነው። እግዚአብሔር የታላላቅ ሰዎቹን ዝና መዝግቦ የሚያሰፍርበትና የሚያሳይበት አዳራሽ ቢኖረው፣ በዚያ እነማን የሚገኙበት ይመስልሃል? ዝነኞች? ኮከብ አቀንቃኞች? በዚህ አዳራሽ ውስጥ የሚቀመጡት የግድ እውቅ ወንጌላውያን ወይም ክርስቲያን አገልጋዮች ሳይሆኑ ይችላሉ። በእግዚአብሔር የክብር አዳራሽ ውስጥ የሚገኙት አንድን ሰው ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ሕይወታቸውን ሙሉ ለሙሉ አሳልፈው የሰጡ ያልታወቁ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። አሁንም ጌታችን፣ «ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን» ብሏል (ማርቆስ 10:43)። *(አንተን ወደ ክርስቶስ ያመጣህንና በሕይወትህ ታላቅ የሆነውን ሰው ምሳሌ እዚህ ጋ መጠቀሙ ተገቢ ሊሆን ይችላል።)*
ዓለም ዋናው ብዙ ነገሮችን ማግኘታችን ነው ትለናለች። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ዋናው ብዙ ነገሮችን መስጠታችን እንደሆነ ይናገራል። ክርስቲያኖችን ጨምሮ፣ አብዛኞቹ ወጣቶች ራስወዳዶች ናቸው። ትኩረት የሚሰጡት ስለሚያስፈልጓቸው፣ ስለሚፈልጓቸውና ስለሚመኟቸው ነገሮች ነው። ክርስቶስ ግን፣ «ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል?» ሲል ጠይቋል (ማቴዎስ 16:26)። ታላቅ መሆን ማለት አገልጋይ መሆን ማለት ነው። ይህም ከሰዎች ዓይን ውስጥ የማይገቡትን ነገሮች ማድረግን፣



ሰዎች ሁሉ የሚያፌዙበትን እንግዳ ማስተናገድን የሚያጠቃልል ነው።
ማቴዎስ 20:25-26 እንደሚነግረን፣ ዓለም ከላይ በመሆን ሥልጣኗን ለማሳየት ትሞክራለች። ይህም ሰዎች ለገንዘብ፣ ለሥልጣንና ለታዋቂነት እንዲጋደሉ አድርጓቸዋል። የእግዚአብሔር መንግሥት ግን የዚህ ተቃራኒ ነው። ታላቅ የሚሆነው የሚያገለግለው ነው። ለዚህ ክርስቶስ ታላቅ ምሳሌ ነው። እርሱ የመጣው በቤተመንግሥት ውስጥ ተደላድሎ ለመቀመጥ ወይም ሰዎችን እያዘዘ ለማዋከብ አልነበረም። በዓለም ላይ ያለውን ሀብት ሁሉ ሊያገኝ ሲችል፣ እርሱ ግን ሌሎችን ለማገልገል መረጠ። እንዲያውም ጌታችን ከመሞቱ አስቀድሞ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ባሳለፉት ሌሊት ታላቅ ትምህርት አስተምሯቸዋል። ደቀመዛሙርቱ ከመካከላቸው ታላቁና ከክርስቶስ አጠገብ የሚቀመጠው ማን እንደሆነ ሲከራከሩ፣ ክርስቶስ የባሪያን ተግባር በመፈጸም የደቀመዛሙርቱን እግር አጥቧል። ቀጥሎም እርስ በርሳቸው እንዲተጣጠቡ አዘዛቸው። በቅርቡ የሰው እግር አጥባችሁ ታውቃላችሁ? ይኼ ሁልጊዜም ጨዋታ ላይሆን ይችላል። የሚሸት እግር ሊያጋጥማችሁ ይችላል። ነገር ግን ክርስቶስን የምትመስሉት የአንድን ሰው ፍላጎቶች ከራሳችሁ ስታስቀድሙና ለማለሰቡ ግድ እንደሚላችሁ ስታሳዩት ነው። (ፎጣውን ከአንገትህ ላይ አንሣና ስጣቸው።) በሉ ቀጥሉ። ታላቅ ሁኑ።

*መዝጊያ*
ተማሪዎቹ ራሳቸውን ዝቅ ሲያደርጉ፣ ስንቶቻችሁ ራስወዳዶች እንደነበራችሁ ትገነዘባላችሁ? አብዛኛውን ጊዜያችሁን ለራሳችሁ ብቻ ስትጠቀሙ ኖራችኋል። አሁን በእግዚአብሔር እርዳታ እውነተኛ አገልጋዮች ለመሆን ትሻላችሁ? (እጆቻቸውን እንዲያነሡ ጠይቃቸው። በጸሎት ፈጽምና ስለ ቀጣዮቹ የአገልግሎት ፕሮጀክቶች ማስታወቂያ ተናገር።)

## የእግዚአብሔር አሸናፊ ቡድን

### ከቴድ ቴይለር

ዓላማ: ወጣቶች እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ እንዴት ሊወዳደሩ እንደሚችሉ ለማሳየት::

ተስማሚ ጊዜ: ይህን ትምህርት የጨዋታ ውድድሮች ከመካሄዳቸው በፊት መጠቀሙ ጠቃሚ ይሆናል::

ዝግጅት

1. ማስታወቂያ ተናገር::
   ሀ. እያንዳንዱ ሰው በጨዋታ ሳይ እንደ ቲፎዞ፣ አሠልጣኝ፣ ተጨዋች፣ ጋዜጠኛ ሆኖ መልበስ አለበት:: በዚህ መልኩ ለብሰው ለሚመጡ ወጣቶችና አዋቂዎች ነጥቦችን ስጥ:: ከፍተኛ የፈጠራ ጥበብ ለታየበት አለባበስ የጉርሻ ነጥብ ጨምር::
   ለ. ቆላስይስ 3:23፣ ፊልጵስዩስ 3:7-8 አጥና::
   ሐ. ድራማውን የሚያጠና ሰው አግኝ::

የቡድን እንቅስቃሴ

1. ማበረታቻ:: ተማሪዎቹ ለየቡድናቸው የማበረታቻ ዘዴዎችን እንዲያዘጋጁ ጠይቃቸው:: የድሮዎቹን ብቻ ሳይሆን አዳዲስ የማበረታቻ ዘዴዎችን እንዲፈጥሩ ንገራቸው:: ዳኞች አሸናፊዎቹን እንዲመርጡ አድርግ::
2. ኪስን ከተቃራኒ ቡድን ግብ ወርውሮ የማስገባት ውድድር:: ሁለት ቡድኖችን መሥርት:: የጨዋታው ዓላማ ኪስን ከተቃራኒ ግብ ውስጥ ማስገባት ነው:: ይህም የሚከናወነው ኪሱን በመወርወር ብቻ ነው:: የአንድ ቡድን አባል ኪሱን ከተቀበለ በኋላ ሁለት እርምጃዎች ይሄድና (የተቃራኒው ቡድን ተጨዋች ሊነጥቀው እየሞከረ) ለጓደኛው ያቀብላል:: ኪሷ ከወደቀች ቀረብ ብሎ ላለው የተቃራኒ ቡድን ተጨዋች ትሰጣለች:: ግብ ከተቆጠረ በኋላ፣ ኪሷ ለተቃራኒው ቡድን ትሰጥና ለማስገባት ይሞክራሉ:: ብዙ ግብ ያስቆጠረ ቡድን የጨዋታው አሸናፊ ይሆናል::
3. አሳዶ መያዝ:: ሰፊ የጨዋታ ስፍራ አዘጋጅ:: አንድ ሰው ይመረጥና ሌሎችን እንዲያሳድድ ይደረጋል:: አንድን ልጅ አሳዶ በሚይዝበት ጊዜ ከልጁ ጋር ግንባር ይፈጥሩና ሌሎችን ለመያዝ ይሞክራሉ:: የተያዘው ሰው ሁሉ የነሱ አባል በመሆን ሌሎችን ያሳድዳል:: አሳዳጆቹ እየበዙ ሲሄዱ በፍጥነት ለመሮጥ ሊያስቸግር ይችላል:: ግን ያልተያዙትን ልጆች በቀላሉ ሊይዙ ይችላሉ:: የጨዋታው ዓላማ አሳዳጆቹ ተሳዳጆቹን ሁሉ እንዲይዙ ማድረግ ነው:: መጨረሻ ላይ የተያዘው ልጅ የጨዋታው አሸናፊ ይሆናል::

ሽግግር: የምትፈልጋቸውን ያህል እንቅስቃሴዎች ተጠቅመህ ወደ መልእክቱ ተሸጋገር::

1. ልዩ መዝሙር:: ወጣቶቹ በግልና በቡድን እንዲዘምሩ አድርግ::
2. መባ የመሰብሰብ አሳብ ካለህ ይህን ጊዜ ለዚያ ተግባር አውል::
3. ድራማ:: ይህን ድራማ መሪው፣ ከወጣቶች መካከል አንዱ ወይም ሌላ ትልቅ ሰው ሊጫወት ይችላል:: ድራማውን በጥሩ ሁኔታ ለማካሄድ በጨለማ ውስጥ አሠልጣኙ ላይ ብርሃን እንዲያንጣጥር ማድረጉ መልካም ይሆናል::
   *(አንድ ሰውዬ ከደረቱ ላይ «አሠልጣኝ» የሚል ጽሑፍ ያረፈበትን ሸሚዝ (ቲ-ሸርት) ለብሶ ይገባል:: ሕዝቡን የራሱ ቡድን አድርጎ በመቁጠር መናገር ይጀምራል:: የስፖርት ቦርሳ አዝሏል::)*
   ስሜ አሠልጣኝ ይባላል:: አሠ-ል-ጣኝ:: እዚሁ ከቲ-ሸርቴ ላይ ስላለ እንዳትረሱት:: እኔ አሠልጣኛችሁ ነኝ:: አሁን የእኔ ማንነት ስለተረጋገጠ፣ ስለናንተ ማንነት እንነጋገር:: እናንተ ምንም አይደላችሁም! አዎ:: እኔ አሠልጣኝ ነኝ:: እናንተ ግን ምንም አይደላችሁም:: ምንም የሚታይ ነገር የላችሁም:: ለማንም አትጠቅሙም:: እናንተ ልክ እንደ መሠረት ናችሁ:: ነገር ግን አንድ ታላቅ ነገር ከውስጣችሁ እናወጣለን:: በግል ደረጃ ይኼ ቡድን ምንም ዋጋ የለውም:: ነገር ግን አብራችሁ ከሠራችሁና አሠልጣኛችሁ የሚነግራችሁን ካደረጋችሁ፣ አንድ ለማየት የሚያምር ነገር ልትፈጥሩ ትችላላችሁ::
   አሁን አንድ ነገር ማስታወስ አለባችሁ *(ከስፖርት ቦርሳው ውስጥ ቆሻሻ ካልሲዎች፣ ሸሚዞች፣ ቁምጣዎች፣ ወዘተ. አውጥቶ ከወረወረ በኋላ፣ መጽሐፍ ቅዱሱን ያወጣል::)* የጨዋታ ዕቅዳችሁ ያለው እዚህ ውስጥ ነው:: እሱን ሳትከተሉ ቀርታችሁ እንዳላገኛችሁ:: እሱ ማድረግ ያለባችሁን ሁሉ ይነግራችኋል:: «ወደ ግራ አትበሉ» ይላችኋል:: በዚህ ጊዜ ወደ ግራ ዘንበል ብላችሁ እንዳላገኛችሁ:: «ወደ ግራም አትበሉ» እያላችሁ ወደ ቀኝ ከሄዳችሁ፣ ቀኙን ባላወቃሁት ብላችሁ ትጸጸታላችሁ:: ይህ የጨዋታ ዕቅድ ተቃውሞውን ለመጋፈጥ ማወቅ ያለባችሁን ሁሉ ይነግራችኋል:: ማሸነፋችሁ ወይም መሸነፋችሁ የሚወሰነው የጨዋታ ዕቅዱን በመከተላችሁ ወይም ባለመከተላችሁ ነው!

ተጋጣሚያችሁ ሊረታችሁ ተዘጋጅቶ ይጠባበቃል፡፡ የጨዋታ ዕቅዳችሁን ካልተከተላችሁ፣ ልታሸንፏቸው አትችሉም፡፡ የውድድሩ ሰዓት አሁን ነው፡፡ ይህን ነገር አስታውሱ፡፡ *(መጽሐፉን ወደ ላይ ከፍ አድርጎ ያሳያል፡፡)* የአሠልጣኞችሁን ምክር ስሙ፡፡ እንደ ቡድን አብራችሁ ተጫወቱ፡፡ የጨዋታ ዕቅዳችሁን ተከተሉ፡፡ አሁን ውጡና ግጠሟቸው፡፡
*(የቡድኑ አባላት በሚወጡበት ጊዜ አሠልጣኙ የሚያበረታታቸው መስሎ ይታያል፡፡ ቆም ብሎ ወደ ሰማይ ይመለከታል፡፡)* እንዴት ነበር ያደረግሁት፣ አሠልጣኝ? አንተ ልትነግራቸው የምትፈልገውን ይሆን የተናገርሁት? የጨዋታ ዕቅድህን ተከትያለሁ? ልክ አንተ እንዳስተማርኸኝ ሳስተምራቸው እሞክራለሁ፡፡ (መብራቱ ይጠፋና ይበራል፡፡)

የመወያያ ጥያቄዎች፡ (መጀመሪያ በትናንሽ ቡድኖች ተከፋፍላችሁ፣ ከዚያም በአንድ ላይ ተወያዩ፡፡)

1. በስፖርት አሸናፊ ለመሆን የሚያስፈልገው ነገር ምንድነው?
2. ከተሸነፋችሁ በኋላ አሸናፊዎች ልትሆኑ ትችላላችሁ?
3. በስፖርት ማሸነፍና መሸነፍ ከክርስትና ጋር የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?
4. ክርስቲያን ለመሆን መጣር ታላቅ አትሌት፣ ሙዚቀኛ፣ ተማሪ፣ ወዘተ. ለመሆን ከመጣር ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?
5. ቤተክርስቲያናችንና የወጣት አገልግሎታችን እንደ አንድ ቡድን ተባብረው ቢሠሩ ምን የሚከሰት ይመስላችኋል?
6. የወጣት ቡድናችን ዓላማ ምን መሆን አለበት?

መልእክት፡ «መንፈሳዊ ሻምፒዮኖች»
ክርስቲያን መሆን ማለት በሁሉም ነገር የምትችለውን ሁሉ ታደርጋለህ ማለት ነው፡፡ «ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ፣ የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉት» (ቆላስይስ 3:23)፡፡
ሁላችንም የዓለም ዋንጫ አሸናፊዎች ላንሆን ብንችልም፣ አሸናፊ ክርስቲያኖች የመሆን ዕቅድ መወጠን አለብን፡፡ 65,000 ተመልካቾች፣ ሁለት ቡድኖች፣ ዳኞችና ኳስ የተገኙበት የእግር ኳስ ጨዋታ ያለ ግብ ቢጠናቀቅ ተመልካቹ ምን ይሰማዋል? እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ስሜት ሊሰጥ አይችልም፡፡ ተጨዋቾቹ ላይ ታች ሲሉ ውለው ግብ አለመቆጠሩ አሳዛኝ ነገር ነው የሚሆነው፡፡ ለክርስቲያኖችም ግባቸውን አለመወጠን ተገቢ አይሆንም፡፡ ፊልጵስዩስ 3:7-8 የክርስቶስን የሚመስል አስተሳሰብ ምን እንደሚመስል ያብራራል፡፡ «ነገር ግን ለእኔ ረብ የነበረውን ሁሉ ስለ ክርስቶስ እንደ ጉዳት ቆጥሬዋለሁ፡፡ አዎን፣ በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለ



ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ጌታዬ እውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቆጥራለሁ፡፡ ስለ እርሱ ሁሉን ተጎዳሁ፡፡»
ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ ከየትኞቹም ስኬቶችና ክብሮች እንደሚልቅ ያውቅ ነበር፡፡

1. በምታደርጉት ነገር ሁሉ አሸናፊ ለመሆን ጣሩ፡፡ ዋናው ነገር ማሸነፉ ሳይሆን ለማሸነፍ መጣሩ ነው፡፡ በምናደርገው ነገር ሁሉ ላይ ከፍተኛ ጥረት ማሳየት አለብን፡፡ ከሁሉም የላቅን አትሌቶች፣ ሠራተኞችና የቤተሰብ አባላት ለመሆን መጣር አለብን፡፡ የምንሠራው ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ምስጋና ለማግኘት መሆኑን አትዘንጉ፡፡
2. ስታሸንፉ፣ ክብሩን ለእግዚአብሔር ስጡ፡፡ ችሎታውን፣ ብርታቱንና ብቃቱን የሰጣችሁ እርሱ ስለሆነ፣ ክብሩ ሁሉ የሚገባው ለርሱ ነው፡፡ እግዚአብሔር እግር ባይሰጣችሁ ኖሮ የማሸነፊያዋን ግብ ልታስቆጥሩ አትችሉም ነበር፡፡ ሳንባ ወይም ጣቶች ባይኖሯችሁ ኖሮ የሙዚቃ መሣሪያዎቹን ልትጫወቱ አትችሉም ነበር፡፡ ክብርና ምስጋና የሚገባው ለጌታ ነው፡፡ እኛ ያለርሱ ምንም ልናደርግ አንችልም (ዮሐንስ 15:5)፡፡
3. ምንም ያህል የከፋ ሽንፈት ቢደርስባችሁ፣ የምትችሉትን ሁሉ ከማድረግ ወደኋላ አትበሉ፡፡ የምትችሉትን ሁሉ አድርጋችሁ ባይሳካላችሁ፣ መጥፎ ስሜት ሊሰማችሁ አይገባም፡፡ የእግዚአብሔርን ምስጋና በመፈለግ ለእግዚአብሔር ቡድን በምትጫወቱበት ጊዜ፣ የምትችሉትን ሁሉ ካደረጋችሁ ዘንዳ ውጤቱ ምንም ይሁን ምንም አሸናፊዎች ናችሁ፡፡ ሽንፈቶች ሊመጡ ቢችሉም፣ ባሕርያችንና መንፈሳችን ትክክል ከሆነ የሽንፈት ስሜት ሊሰማን አይገባም፡፡

በአንድ ወቅት አስገራሚ የፒያኖ ችሎታ የነበረው ልጅ ነበር፡፡ የፒያኖ ጨዋታ የተካኑ አንድ አዛውንትም ነበሩ፡፡ አዛውንቱ ልጁን ለማስተማር ተስማሙ፡፡ ለሦስት ዓመታት አዛውንቱ ልጁን በየቀኑ ማስተማራቸውን ቀጠሉ፡፡ ከሦስት ዓመታቱ ፍጻሜ በኋላ አንድ ኮንሰርት ተዘጋጀ፡፡ በትልቅ አዳራሽ ውስጥ ዝግጅቱ ሲካሄድ፣ የልጁን ችሎታ ለመመልከት የቋመጡ ሰዎች ወደዚያው ጎረፉ፡፡ ከሰገነቱ ላይ አዛውንቱ ብቻቸውን ቁጭ አሉ፡፡ ልጁ ሙዚቃውን ግሩም አድርጎ በመጫወቱ ወደ መጨረሻ አካባቢ አድምተኞቹ እየዘለሉ ይጨፍሩ ጀመር፡፡ ልጁ ግን ዓይኖቹን በአዛውንቱ ላይ ተክሎ ድርቅ ብሎ ቀረ፡፡ ሕዝቡ ጩኸቱን ሲቀጥል አዛውንቱ ዝም ብለው አዳመጡ፡፡ በመጨረሻም፣ አዛውንቱ ግሩም ተግባር እንዳከናወነ በመግለጽ ራሳቸውን ሲነቀንቁ፣ ልጁ ከመቀመጫው ዘሎ በመነሣት እጅ ነሣ፡፡
ይህ ታሪክ የዓለም ጭብጨባ ሊመጣና ሊሄድ የሚችል መሆኑን፣ ነገር ግን ምስጋናችን ከሰማያዊ አባታችን ዘንድ እንደሚመጣ

ያስረዳል። በጨዋታ ብናሸንፍ ወይም በትምህርታችን ትልቅ ውጤት ብናመጣ፣ ዋናው ነገር እኛ የምንፈልገውን ማግኘታችን አይደለም። የእግዚአብሔርን ምስጋና በመፈለጋችሁ፣ ሁልጊዜም የአሸናፊው ቡድን አባላት ሆናችሁ ልትኖሩ ትችላላችሁ።

*መዝጊያ (በጸሎት ፈጽም። የእግዚአብሔር ቡድን አባላት ለመሆን የሚፈልጉ ሰዎች አብረውህ እንዲጸልዩ ጋብዛቸው። በዚህ የማሸነፍና የመሸነፍ ጉዳይ ላይ የእግዚአብሔርን እርዳታ የሚፈልጉ ሰዎች እጆቻቸውን እንዲያነሡ ልትጠይቃቸው ትችላለህ። በጸጥታ ወደነዚህ ሰዎች ሄደ የሚጸልይ ወይም ከስብሰባው በኋላ ለየብቻ የሚያነጋግራቸው መሪ ያስፈልግሃል። ሕይወታቸውን ለኢየሱስ ክርስቶስ አሳልፈው በመስጠት፣ ኃጢአታቸውን ይቅር እንዲላቸውና በልባቸው ውስጥ ገብቶ እንዲኖር በመጋበዝ፣ የዚህ የአሸናፊ ቡድን አባላት ሊሆኑ እንደሚችሉ በመግለጽ አበረታታቸው።)*



# የለውጥ በዓል

## ከኬንዶል ፍራንክሊን

**ዓላማ:** ወጣቶች እንዲለወጡ ለማበረታታት። ክርስቶስን ለመከተል ለውጥ አስፈላጊ ነው።

**ተስማሚ ጊዜ:** ይህ መልእክት በትምህርት ቤት መክፈቻ ወቅት ቢቀርብ መልካም ነው።

**ዝግጅት**

1. ቀጣይ እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ ማስታወቂያ ተናገር።
2. የሐዋርያት ሥራ 9:1-19፣ 1ኛ ሳሙኤል 10:6 አጥና።
3. ጸልይ።

**የቡድን እንቅስቃሴዎች**

1. የሚያስፈልጉ ነገሮች: ለእያንዳንዱ ሰው እርሳስ ወይም እስክብሪቶ። ይህን ተግባር ከሌሎቹ ቀደም የጨረሰ ልጅ ሽልማት ሊሰጠው ይገባል።

   ሀ. ሦስት ሰዎችን በመምረጥ የኢትዮጵያን ብሔራዊ መዝሙር አብራችሁ ዘምሩ። ሰዎቹ እዚህ ጋ እንዲፈርሙ አድርግ:——————

   ለ. ሌሎች ሁለት ሰዎች ምረጥና ከአንተ ጋር እየዘመሩ በክፍሉ ውስጥ እንዲመላለሱ አድርግ። ፊርማ: ——————

   ሐ. በአካባቢያችሁ አንድ ታዋቂ የእግር ኳስ ተጫዋች ለየትኛው ቡድን እንደሚጫወት የሚያውቅ ሰው አግኝ። ፍርማ: ——————

   መ. ሌሎች ሦስት ሰዎች ምረጥና፣ በጣም ጮክ ብለህ፣ «እኛ ብርቱዎች ነን። አዎን፣ እኛ ጠንካሮች ነን። እናንተስ?» እያልህ ጮኽ። ሌሎች ቡድኖች ምላሽ እስኪሰጡ ድረስ ማበረታታትህን ቀጥል። ፊርማ: ——————

   ሠ. ሌሎች አምስት ሰዎች ምረጥና አብረሃቸው አምስት ፑሽአፕ ሥራ።

   ለዓይነት:

   - ከወጣቶቹ ትምህርት ቤቶች ወይም አካባቢዎች ጋር የሚጣጣሙትን ሌሎች ሁለት ወይም ሦስት ነገሮች ጨምር።
   - ያሉህ ወጣቶች ጥቂቶች ከሆኑ፣ ሁሉንም እንቅስቃሴዎች አንዳንድ ሰው ብቻ እንዲሠራ አድርግ።
2. ላስቲክን ከፊት ወደ አንገት የማውረድ ውድድር። ከእያንዳንዱ ቡድን አንዳንድ ተወካዮችን ወይም ከ3-4 የሚደርሱ ፈቃደኛ ልጆችን አግኝ። እያንዳንዱ ተወዳዳሪ አንድ የሚለጠጥ ሲባጎ (ላስቲክ) ከራሱ እስከ አፍንጫው ጫፍ እንዲያደርግ ጠይቅ።

(ከጀርባ ላይ ማድረግም ይቻላል።) ምልክት በምትሰጥበት ጊዜ፣ ሳስቲኩን ከራሱ አውርዶ ከአንገቱ ላይ ለማሳረፍ የቻለ ልጅ ያሸንፋል። ሳስቲኩን ከፊቱ አካባቢ ወደ አንገቱ ለማውረድ እጁን ሊጠቀም አይችልም። ነገር ግን በግድግዳ፣ በወለል፣ በእጠና ሊታገዝ ይችላል። ለአሸናፊዎቹ ነጥቦችን ሸልም።

3. የእግር ኳስን ማስተላለፍ፡ የሚያስፈልገው ነገር፡ ለእያንዳንዱ ቡድን አንዳንድ የእግር ኳስ። ቡድኖቹን እኩል ቁጥር እንዲኖራቸው አድርገህ በቀጥተኛ መስመር አሰልፋቸው። በሰልፉ መጀመሪያ ላይ ላለው ልጅ ኳስ ይሰጠዋል። ኳሱ የተሰጠው ልጅ በቴስታ ይመልሳል (ትመልሳለች)። ቀጣዩ ልጅ በእግሮቹ መሀል ያሽልካል። እንዲህ እያሉ ኳሷን በመጀመሪያ ከመጨረሻው ተሰላፊ ዘንድ ያደረሱ ልጆች አሸናፊዎች ይሆናሉ።

   ለዓይነት፡

   ሀ. የተለያዩ መጠኖች ያሏቸውን የተለያዩ የእግር ኳሶች ተጠቀም

   ለ. የሌሎች ስፖርቶችን የተለያዩ ኳሶች ተጠቀም።

4. የሚያስፈልጉ ነገሮች፡ እያንዳንዱ ሰው ከጉልበቱ ላይ የሚያስራቸው ቁርጥራጭ ጨርቆችና ኳስ። እያንዳንዱ ልጅ ጨርቁን ከጉልበቱ ላይ አጥብቆ ያስራል። መሮጥ አይፈቀድም። ጨርቆቹ እዚያ ከጉልበቶቻቸው ላይ እያሉ የእግር ኳስ ይጫወታሉ።

ሽግግር፡ ከእንቅስቃሴዎቹ ወደ መልእክቱ ለመተላለፍ ከሚከተሉት አንዱን ወይም ሁሉንም ተጠቀም።

1. ለእያንዳንዱ ቡድን አንድ ቅጠል፣ ቀርቀሮና እግር ኳስ በመስጠት በአምስት ደቂቃ ውስጥ አንድ ጭውውት እንዲያዘጋጁ ንገራቸው።
2. አሸናፊዎቹ ቡድኖች እነማን እንደሆኑ ግለጽና አጠቃላይ ነጥቦችን ስጥ።
3. የቡድን ዝማሬ፣ ወይም በአንድ ግለሰብም ሆነ በቡድን የሚቀርብ ልዩ ዝማሬ።
4. መባ።

መልእክት፡ «የለውጥ ጊዜ»

*(ከዓመት ዓመት መጠኑን ወይም ቅርጹን እየለወጠ የሚሄድ ነገር ወይም ዕቃ አዘጋጅ።)*

ትምህርት ቤቶች የሚከፈቱበት ወቅት የለውጥ ጊዜ ነው። ይህ ወቅት የዓመቱ ታላቅ ጊዜ ሊሆን ይችላል። ነገሮች ይለወጣሉ። *(ያመጣኸውን ነገር አውጣው።)* ይኼ ነገር የለውጥን እውነትነት ያስረዳል። ከጥቂት ጊዜ በፊት ይህ ዕቃ የተለየ ነበር። አሁን ደግሞ ይኼን ይመስላል። ዛሬ ስለ ለውጥ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ።



በአንድ ወቅት ሳውል የሚባል ረዥምና ከሰው ዓይን የማይሞላ ቀውላላ ልጅ ነበር። እግዚአብሔር ይህ ልጅ በእስራኤል ላይ እንዲነግሥ መረጠው። *(1ኛ ሳሙኤል 10፡6-7 አንብብ።)* ሳውል ያን ያህል ማራኪ ወጣት ባይሆንም፣ እግዚአብሔር ነገሮችን ሊለውጥ ይችል ነበር። እግዚአብሔር ሳውልን ሌላ ሰው አድርጎ ለወጠው። ውጤታማ መሪና ወታደራዊ አዛዥ አደረገው። እግዚአብሔር ከለወጠው በኋላ ሳውል ተራ ሰው አልነበረም።

ከብዙ ዓመታት በኋላ በሐዋርያት ሥራ 9:1-19 ውስጥ እንደተጠቀሰው ይህንኑ ተመሳሳይ ስም የያዘ ሌላ ሰው አስገራሚ የሕይወት ለውጥ ገጥሞታል። *(ክፍሉን አንብብላቸው ወይም በራስህ አገላለጽ አብራራላቸው።)* ሳውል ለፈሪሳዊነት ራሱን የሰጠ ሰው በመሆኑ፣ እስጢፋኖስ በተወገረ ጊዜ በስፍራው ነበረ። ሳውል አጅግ የተማረ አይሁዳዊ ሲሆን፣ ሰዎች ስለ ክርስቲያኖች በሚናገሩበት ጊዜ ደሙ ይፈላ ነበር። ሳውል ለሙሴ ሕግ በጥብቅ መገዛት አስፈላጊ መሆኑን ያምን የነበረ ሲሆን፣ ክርስቶስና ተከታዮቹ ይህንን ሕግ ተላልፈዋል የሚል ግምት ነበረው። የሙሴን ሕግ መተላለፍ ደግሞ ወንጀል ነበር። የፈሪሳውያንን እምነት የማይከተሉትን ሰዎች ሁሉ መደብደብ፣ መግደል ወይም ማሰር በጣም ያስደስተው ነበር።

ይህ ሳውል የተባለው ጠንካራና ቁጡ ግለሰብ ክርስቲያኖችን ሐሰተኞች ናቸው ብሎ በማሰቡ እየደበደበ ያሰቃያቸው ነበር። ሳውል ክርስቶስን የሚከተሉትን ሰዎች ሕይወት በሥቃይ ለማጀብ የሚችለውን ሁሉ ከማድረግ ወደኋላ አይልም ነበር። ክርስትና እንደ ሰደድ እሳት በአገሪቱ ሁሉ እየተስፋፋ የመሄዱ ዜና የሳውል መዲና ወደሆነችው ኢየሩሳሌም ደረሰ። የአይሁድ መሪዎች ሊያዳፍኑት በሞከሩ መጠን፣ የክርስቶስ ወንጌል በፍጥነት ይስፋፋ ነበር። ጳውሎስ! «ይህን የዕብዶች ሃይማኖት ካልገታሁ እኔ አይደለሁም!» ሲል በግልፍተኝነት ዛተ። ስለሆነም፣ ወደ ደማስቆ ሄዶ ክርስቲያኖች የሚባሉትን ሰዎች ለማሳደድ የሚያስችለውን ፈቃድ ከሊቀካህናቱ አገኘ። ሳውል እነዚህን ሰዎች ለመግደል ወይም ለማሳሰር ነበር ያቀደው። የፈሪሳውያን አለቃ የሆነው ሊቀካህን ሳውል ክርስቲያኖችን ሁሉ እያሳደደ እንዲያጠፋ የሚያዝ የጽሑፍ ድጋፍ ሰጠው። የአይሁድ ምኩራቦች ሁሉ ክርስቲያኖችን ለማጥፋት በሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ ድጋፋቸውን እንዲሰጡ አዘዘ።

እናም ሳውል ክርስቲያኖችን ለማደን ተዘጋጀ። ሳውል ጉዞውን ከመጀመሩ በፊት በጣም ስለተደሰተ ሥራውን ለመጀመር ጓጓ። በመጨረሻም የተቆረጠው ቀን ደረሰ። ሳውል ከጥቂት የጥፋት ተባባሪዎቹ ጋር መንገዱን ቀጠለ። ወደ ቀትር አካባቢ፣ ቡድኑ ወደ አገሪቱ በመቅረቡ የደማስቆን ከተማ ቅጥር ሊያይ ከሚችልበት ስፍራ ላይ ደረሰ። ወዲያውኑ ግን ጳውሎስ ከመሬት ላይ ተዘረረ! ከሰማይ የወረደው ታላቅ ብርሃን ዓይኖቹን አሳወረ። ሳውል፣ «ሳውል፣

ሳውል፣ ለምን ታሳድደኛለህ?» የሚል ድምፅ ሰማ። «አንተ ማነህ፣ ጌታ ሆይ?» ሲል ሳውል ጠየቀ። አሁን ገና ገባው። ሳውል ትክክለኛውን ነገር ለመፈጸም የሚዋጋ ቢመስለውም፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነበር የሚዋጋው። ሳውል ተለወጠ። በኋላም፣ ሐናንያ የተባለ ሰው በክርስቶስ ታዞ በመምጣት ከሳውል ላይ እጁን ጭኖ ጸለየለት። በዚህም ጊዜ ሳውል መንፈስ ቅዱስን ተቀበለ። ዓይኖቹም ተከፈቱ።
ይህ ሰው ሊለወጥ እንደሚችል የሚያሳይ ግሩም ምሳሌ ነው። ሳውል ስሙ ተቀይሮ ጳውሎስ መባሉ ብቻ ሳይሆን፣ የክርስቶስ ጠላት ከነበረበት ሁኔታ ተለውጦ እጅግ ፍሬያማ ሐዋርያ ሊሆን በቅቷል። እግዚአብሔር ብዙ ሰዎችን ለመለወጥ ስለተጠቀመበት፣ ጳውሎስ የሜድትራኒያንን አካባቢ ሙሉ ለሙሉ ሊለውጥ በቅቷል። ጳውሎስ ክርስቶስን በመከተሉ ምክንያት ድብደባ፣ በድንጋይ መወገርና መተፋት ደርሶበታል። እርሱ ፍጹም የተለወጠ ሰው ሆነ።
እነዚህ ታሪኮች የሚያስተላልፉት መልእክት ይኼ ነው። እግዚአብሔር ለኔ ካለው ፍቅርሩና አሳቢነቱ የተነሣ ሊለውጠኝ ይችላል። *እናንተንም ሊለውጣችሁ ይችላል። (እዚህ ጋ እግዚአብሔር እንዴት እንደለወጠህ በመጠኑ ልትመሰክርላቸው ትችላለህ።)* በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ብትሆኑ ወይም ምንም ዓይነት ጥፋት ብትፈጽሙ፣ እርሱ ሊለውጣችሁ ዝግጁ ነው። ሱስ አስያዥ ዕፅ ተጠቅማችሁ ወይም ዝሙት ፈጽማችሁ የምታውቁ ብትሆኑ እንኳዋን፣ ፍጹም የተለየ ሰው አድርጎ ሊለውጣችሁ ይችላል። *እጅግ ስለሚወዳችሁ!* ይጠራችኋል። ሰዎችን ጎድታችሁ ከሆነና አሁንም ይህንኑ የምታደርጉ ብትሆኑ፣ እግዚአብሔር ሊለውጣችሁ ይችላል። እግዚአብሔር ከግድየለሽነት ማኅበረሰባችሁን የምትለውጡ ሰዎች አድርጎ ሊለውጣችሁ ይችላል። ካመናችሁብትና እንዲለውጣችሁ ከፈቀዳችሁለት፣ እርሱ ባሕርያችሁን፣ አኗኗራችሁንና እምነታችሁን ሊለውጥ ይችላል። ይህ የለውጥ ዕድል እያምልጣችሁ። አሁን ክርስቶስ እንዲለውጣችሁ ትፈቅዱለት ዘንድ እጋብዛችኋለሁ።
(እግዚአብሔር ሕይወታቸውን እንዲለውጥ ራሳችሁን አሳልፈው እንዲሰጡ ጋብዛቸው። የግብዣ መዝሙር ቢኖር መልካም ነው። በጸሎት ፈጽም።)

መሠረቱ የጸናው

# የማዕዘን ድንጋይ

ኢሳይያስ 28:56



## ዋስትና
### ከሱዚ ሽለንበርገር

ዓላማ፡ እውነተኛው የዋስትናችን ምንጭ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን ለወጣቶች ለማስገንዘብና በርሱ እንዲታመኑ ለማበረታታት።

**ዝግጅት**
1. ከስብሰባው ጥቂት ሳምንታት አስቀድመህ ስለሚከተሉት ነገሮች ዝርዝር ጉዳዮችን በተመለከተ ማስታወቂያ ተናገር።
   ሀ. የቡድን ውድድሮች
   ለ. በስብሰባው ላይ ለሚገኙና እንግዶችን ይዘው ለሚመጡ ልጆች የነጥብ ሽልማት ይሰጣቸዋል።
   ሐ. መክብብ ምዕራፍ 1 እና 2፣ ሮሜ 8:38-39 አጥና።

የቡድን እንቅስቃሴዎች፡ ከሚከተሉት እንቅስቃሴዎች አንዱን ወይም ሁሉንም ተጠቅመህ ስብሰባውን ጀምር።
1. የፍራፍሬ ስም በመጥራት የሚካሄድ ውድድር። ልጆቹ በክብ ዙሪያ እንዲቀመጡ አድርግ። የብዙ ፍራፍሬዎች ስሞች ይመረጡና የአንድ ፍራፍሬ ስም ከ3-4 ለሚሆኑ ተጫዋቾች ይሰጣል። ለእያንዳንዱ ተጫዋች የአንድ ፍራፍሬ ስም ይሰጠዋል። የፍራፍሬዎቹን ስም የሚጠራ አንድ ሰው ከክቡ መሀል ይገባል። ልጁ የአንድን ፍራፍሬ ስም በሚጠራበት ጊዜ፣ የተጠራው የፍራፍሬ ስም የተሰጣቸው ተጫዋቾች ከክቡ መሀል ያለው ልጅ ወንበር ከማግኘቱ በፊት ሌላ መቀመጫ ማግኘት ይኖርባቸዋል። ከተጫዋቾቹ መካከል ወንበር ሳያገኝ የቀረው ልጅ መሀል ይገባል። መሀል ያለው ልጅ «የፍራፍሬ ቅርጫት ገልብጡ» ካለ፣ ሁሉም ተጫዋቾች ወንበር ይቀይራሉ።
2. የጭራቅ እርምጃ። ወጣቶቹ ብዙ ከሆኑ፣ በተለመደው ቡድናችሁ ውስጥ እንዲገቡ ንገራቸው። ወጣቶቹ ብዙ ካልሆኑ ግን ሁለት ቡድኖችን አንድ ላይ ልታዋህድ ትችላለህ። የመነሻና የመድረሻ መስመሮች ከ5-10 ሜትሮች መራራቅ አለባቸው። የእያንዳንዱ ቡድን አባላት እጆቻቸውን በማያያዝ፣ ክንዶቻቸውን በማጠላለፍ፣ አንዱ ከሌላው ጀርባ ላይ በመሆን ወይም በሌሎች መንገዶች ሊጣመሩ ይችላሉ። ብቸኛው ገደብ ቡድኖቹ ለጉዞው ሊጠቀሙ የሚችሏቸው የእግሮችና እጆች ብዛት ብቻ ነው። በጉዞው ሂደት ውስጥ ቡድኖቹ ሊጠቀሙባቸው የሚችሏቸው እግሮችና እጆች በቡድኑ ውስት ካሉት ሰዎች ሁለት ከተቀነሰ በኋላ የሚቀሩትን ይሆናል። ለምሳሌ፣ በቡድኑ ውስጥ ስድስት ሰዎች ካሉ በአንድ ላይ ተጣምረው የጭራቅ እርምጃ ሊያካሂዱ የሚችሉት አራት

አግሮችንና አራት እጆችን በመጠቀም ይሆናል:: በመነሻው መስመር ላይ ቡድኖቹን ካሰባሰብህ በኋላ የማስጀመሪያ ምልክት ስትሰጣቸው ውድድሩ ይጀመራል::

3. ሙዚቃዊ ፊኛዎች:: ወጣቶቹ በክብ ዙሪያ እንዲቆሙ ንገራቸው:: ከአንደኛው በስተቀር ለሁሉም ልጆች ፊኛ ትሰጣቸዋለህ:: ሙዚቃውን የሚከፍትና የሚዘጋ አንድ ሰው አዘጋጅ:: ሙዚቃው በሚከፈትበት ጊዜ ልጆቹ ፊኛውን ከአንዱ ወደ ሌላው ማስተላለፍ ይጀምራሉ:: ሙዚቃው በሚቆምበት ጊዜ ፊኛ ይዞ ያልተገኘ ልጅ ከጨዋታው ይወጣል:: ተጨዋቹ ከወጣ በኋላ ሁልጊዜም አንዳንድ ፊኛ ይቀነሳል::
4. ፊኛ ማፈንዳት:: ከእያንዳንዱ ቡድን አንድ ልጅ የተነፋ ፊኛ ይሰጠዋል:: ምልክት በሚሰጥበት ጊዜ፣ የግራ እጃቸውን ብቻ በመጠቀም ፊኛዎቹን ለማፈንዳት ይሞክራሉ:: መጀመሪያ ፊኛውን ያፈነዳው ልጅ አሸናፊ ይሆናል:: እሱ የወከለው ቡድን ብዙ ነጥብ ያገኛል::

ሽግግር: የሚከተሉት ነገሮች ወደ መልእክት እንድትሸጋገር የሚያግዙህ ናቸው::

1. በእያንዳንዱ የቡድን ውድድር ላይ አሸናፊዎች የነበሩትን ቡድኖች በመግለጽ፣ የተሻሻሉትን ነጥቦች (የእስካሁኑን ድምር) ስጥ::
2. የቡድን ዝማሬ::
3. የቡድን ውይይት::

ሮሜ 8:38-39:: ብዙ የዋስትና አቅጣጫዎችን እንፈልጋለን:: ከፋሽን፣ ከወዳጆች፣ ወዘተ. ዋስትና ለማግኘት እንፈልጋለን:: እውነተኛ የዋስትና ምንጭ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው:: ፍቅሩ ምን ጊዜም ከኛ ሊወሰድ አይችልም:: በዚህ ስብሰባ ላይ ወጣቶች እግዚአብሔር የዋስትናቸው ምንጭ መሆን እንዳለበት እንዲገነዘቡ እንፈልጋለን:: በሌላ ነገር ላይ የሚደገፍ ዋስትና ዘለቄታ የለውም::

*የመወያያ ጥያቄዎች*

1. የዋስትና ስሜት እንዲሰማህ የሚያደርጉ አንዳንድ ነገሮች ምን ምንድናቸው? (ዝርዝሩን ልትጽፍ ትችላለህ::)
2. ዋስትና ምንድነው?
3. አብዛኞቹ የትምህርት ቤት ጓደኞቻችሁ ዋስትናቸውን የሚያሳርፉት በምን ላይ ነው?
4. ከተነጋገርናቸው ነገሮች አንዳንዶቹን ብናጣቸው፣ ዋስትናችን ምን ይሆናል?



4. ጸሎት::

***መልእክት: «ዋስትና»***

*(አንድ ሰው ለማስቀመጥ የሚችል ሣጥን በማግኘት ለዚህ ጭውውት ቀደም ብለህ መዘጋጀት አለብህ:: ወይም ደግሞ ትልቅ ልብስ ልትጠቀም ትችላለህ:: ከሣጥኑ ውስጥ የምትገባው ልጅ የምትናገራቸውን ቃላት ማጥናት ይኖርባታል::)*

ሣጥን: እንደምናችሁ? ትሰሙኛላችሁ?

*መሪው (ድምፁ የሚመጣበትን አቅጣጫ ለማወቅ ይሞክራል:: በመጨረሻም ወደ ሣጥኑ በመሄድ)*: ቆይ እንጂ ከሣጥኑ ላስወጣሽ::

ሣጥን: አይቻልም! ይኼን ሣጥን እንዳትወስድ! *(ድምፅዋን ቀንሳ)* እዚህ በጣም ተመችቶኛል::

*መሪው*: እውነትሽን ነው? እስኪ ንገሪኝ:: ምን ይመስላል?

ሣጥን *(በመጀመሪያ መደሰቷን የሚገልጽ ድምፅ ብታሰማም፣ ቦታውን እንደማትወደው በሚያመለክት ቃና)*: እዚህ የሚጎረብጥ ነገር አለ:: ትንሽና ሸካራ ጠርዞች፣ ብዙ ካርቶን፣ ክዳን፣ ከጥጉ ጋ የሸረሪት ድር አለ...

*መሪው*: ቦታውን አትወጅውም አይደል?

ሣጥን: አዎ::

*መሪው*: እዚያ ከገባሽ ምን ያህል ቆየሽ? ቀኑን ሙሉ?

ሣጥን: ከዚያ በላይ ነው:: ሁለት ወይም ሦስት ዓመት የቆየሁ ይመስለኛል::

*መሪው*: ሁለት ወይም ሦስት ዓመታት? እዚያ እንድትቀመጪ ያስገደደሽ አለ?

ሣጥን: በምርጫዬ ነው የገባሁት::

*መሪው*: ማንም ሣጥኑ ውስጥ እንድትቀመጪ ካላስገደደሽና ቦታውንም ካልወደድሽው፣ ለምን አትወጪም?

ሣጥን: እንደዚያ ማድረግ ያለብኝ ይመስለኛል! *(ብርታትን እያገኘች በመሄድ)* አሁኑኑ ተንከባልዬ እወጣለሁ:: ከዚህ ወጥቼ ይኼን ሣጥን እተረትረዋለሁ! (ሣጥኑን ካንቃነቀች በኋላ ዝም ትላለች::) ግን ደግሞ እዚሁ ተቀምጬ አካባቢዬን ማድነቅ ሳይኖርብኝ አይቀርም::

*መሪው*: እንዴት እዚያ ልትገቢ ቻልሽ?

ሣጥን: ይኼን ልናገር አልችልም::

*መሪው*: ለምን?

ሣጥን: አልችልማ:: እንዴት እንደገባሁማ የማውቅ አይመስለኝም::

*መሪው*: ምናልባት ማንነትሽን ካወቅሁ እንዴት እዚያ እንደገባሽ አውቅ ይሆናል:: እስኪ ስለራስሽ ንገሪኝ:: ምን ትመስያለሽ?

ሣጥን: ይኼ እንደ ሁኔታው ነው::

*መሪው*: ምን ዓይነት ባሕርይ ነው ያለሽ? ቀልደኛ ነሽ? ጭምት? ደስተኛ? ሙክ እያልሽ የምትጫወቺ? ምን ዓይነት ነሽ?

ሣጥን: እንደሚመስለኝ... ይኼ እንደ ሁኔታው ነው።
መሪው: ቢያንስ ስለ ፀጉርሽ ንገሪኝ!
ሣጥን: እነግርህ ነበር... ግን እንደ ሁኔታው ነው።
መሪው: እንደ ሁኔታው ስትይ ምን ማለትሽ ነው?
ሣጥን: አብሮኝ ካለ ሰው አንጻር ማለቴ ነው። ከሰሬን ቡድን ውስጥ ስሆን፣ ጂንስ፣ ቲ-ሸርትና ነጠላ ጫማ እለብሳለሁ። በእግር ጣቶቼ ለመራመድ ስለምሞክር ትንሽ ረዘም እላለሁ። ፀጉሬን ለቀቅ አድርጌ የማስታውሰውን ቀልድ ሁሉ እነግራቸዋለሁ። ከነ ጁሊ ቡድን ጋር በምሆንበት ጊዜ፣ አዲሱን ቀሚሴንና ምርጥ የቆዳ ጫማዬን እለብሳለሁ። ፀጉሬን ፍርዝ (ከርል) አደርገዋለሁ። አሁን ቀልድ መናገሬ ይቀርና በሱዛን ቦይ ፍሬንድ ቀልዶች ስስቅ እውላለሁ። የልጁን ታላቅነት የሚያሳዩ አስተያየቶችም እሰነዝራለሁ።
መሪው: አሁን እዚያ ሣጥን ውስጥ ለምን እንደታሸግሽ እየገባኝ ይመስለኛል።
ሣጥን: የፓሌሳ ቡድን በሚመጣበት ጊዜ ግን የስፖርት ልብሴን እለብሳለሁ። ፀጉሬ ለሁለት ይከፈላል። ለስላሳ የቆዳ ጫማ አደርጋለሁ። ለቀልድ ጊዜ አይኖረኝም። ወጣ ብለን ወንድ ስናባርር ወይም ቴኒስ ስንጫወት እንውላለን።
መሪው: ችግርሽ ምን እንደሆነ የተረዳሁ ይመስለኛል። ነገር ግን ከዚያ ሣጥን ውስጥ ወጥተሽ ብትመጪ መነጋገሩ ይቀል ነበር።
ሣጥን: አይ፣ ይኼን ሳደርግ አልችልም!
መሪው: ምን ማለትሽ ነው? ትችያለሽ! እኔና አንቺ ብቻ ነን ያለን!
ሣጥን: በአፍንጫዬ ላለመቀለድ ቃል ትገባልኛለህ? አፍንጫዬ ትልቅ ነው።
መሪው: ላለመቀለድ ቃል እገባልሻለሁ።
ሣጥን *(ቀስ እያለች ትወጣለች። መጀመሪያ ሕዝቡን አታይም። ሕዝቡን ስታይ ግን ጩኸቷን አቅልጣ ወደ ሣጥኑ ተመልሳ ለመግባት ትሞክራለች።)*
መሪው: እነሱን ተያቸው። እነሱ ንግግራችንን አልሰሙም።
ሣጥን: እዚህ መውጣቱ ደስ ይላል። ለምን ይሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ታሽጎ የመኖር ፍላጎት ያደረብኝ?
መሪው: ይኼ ዋስትና ማጣት ይባላል። ዋስትና ማጣት ምን እንደሆነ በቀላሉ ላስረዳሽ። ዋስትና ማጣት የሚከሰተው ፍላጎትሽን፣ ፍቅርሽን፣ ወይም አኗኗርሽን ሊጠፋ በሚችል ነገር ላይ ስትመሠርቺ ነው። (ዝምታ) ሕይወትሽን ስትመሪ የኖርሽው ሌሎች ሰዎችን ለማስደሰት በማሰብ ይመስላል። ያ ደግሞ ዋስትና እንዳይኖርሽ አድርጓል። ሌሎችም ሰዎች ሕይወታቸውን የሚመሠርቱባቸውና ዋስትና እንዳይኖራቸው የሚያደርጉ ነገሮች አሉ። አንዳንድ ጊዜ ቦይፍሬንዶች ወይም ገርልፍሬንዶች ለሰዎች ሐሰተኛ ዋስትና ይሰጣሉ። ወንዱ ወይም ሴቷ ፈቀቅ እስኪሉ ድረስ ሁሉም ነገር



ጥሩ ይሆናል። መለያየት ሲከሰት ግን ዋስትናችንን እናጣለን። እንደ ቤተሰብ፣ ወላጆች፣ ሥራ ያሉ ሌሎች መልካም ነገሮችም የዋስትና ምንጮች ተደርገው ሊወሰዱና በኋላ ግን ዋስትና እንዳይኖረን ሊያደርጉ ይችላሉ።
ሣጥን: ታዲያ መፍትሔው ምንድነው? ዝም ብሎ መሠቃየት?
መሪው: አይደለም። ሕይወትሽን ሊጠፋ በማይችል ነገር ላይ መመሥረት ይኖርብሻል። ይኼን ስሚ። «ሞት ቢሆን፣ ሕይወትም ቢሆን፣ መላእክትም ቢሆኑ፣ ግዛትም ቢሆን፣ ያለውም ቢሆን፣ የሚመጣውም ቢሆን፣ ኃይላትም ቢሆኑ፣ ከፍታም ቢሆን፣ ዝቅታም ቢሆን፣ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ» (ሮሜ 8:38-39)።
ሣጥን: በአንድ ወቅት ክርስቶስን ለመከተል ሞክሬ ነበር! በበጋ ካምፕ ጊዜ አንዳንድ ልጆችና እኔ ወደ ቤተክርስቲያን ሄደን ብዙ ጸለይን። ወደ ቤት ከሄድን በኋላ ግን ጓደኞቼ በፕሮግራሙ ሰዓት ሌሎች ነገሮችን ስለሚያደርጉ እኔም ከነሱ ጋር መሆን ጀመርሁ።
መሪው: ብዙ ሰዎች እንደዚያ ያደርጋሉ። ብዙውን ጊዜ ዋስትና የሌላቸው ሰዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው የሚጮኹቱ ናቸው። ሁልጊዜ ሳይሆን፣ አንዳንድ ጊዜ። ይህን የሚያደርጉት አንድ አዲስ ድጋፍ እንዳገኙ ለሰዎች ለማሳየት ነው። ነገር ግን አዲሱ ድጋፍ ክርስቶስ አይደለም። ብዙውን ጊዜ የአገልጋዮች አድናቆት ወይም ሌሎች የሚጸልዩ ጓደኞቻቸው ይሆናሉ። ክርስቲያንነትሽን ወይም ወደ ቤተክርስቲያን መሄድሽን ጓደኞችሽ ሳያደንቁ ሲቀሩ ይህንኑ ከማድረግ እንደምትቆጠቢ አንቺ ራስሽ ተናግረሻል። ይኼ ክርስትና አይደለም! አንድ ሰው ክርስቲያን በሚሆንበት ጊዜ፣ ለሰዎች ድጋፍ የሚሰጠው ስፍራ መቀነስ ይጀምራል። ከዚያ በኋላ ደስታሽ የሚወሰነው ሰዎች ስላንቺ በሚሰጡት ግምት ላይ አይሆንም።
ሣጥን: የብዙ ሕዝብ ድጋፍ መኖር ወይም አለመኖር ለውጥ የለውም ነው የምትለው? አሁንም ደስተኛ ልሆን እችላለሁ?
መሪው: አሁንም ቢሆን ሰው ነሽ። ክርስቶስ ወዳጆቹ በተለዩት ጊዜ ኃዘን ተሰምቶት ነበር። ነገር ግን እነዚህ ነገሮች ሁሉ በሚለዩን ጊዜ ዋናው የሰላምና የዋስትና ምንጫችን ክርስቶስ ከሆነ፣ ሰላማችንና ዋስትናችን አይወሰድብንም። ራሳችንን እንዴት መውደድ እንዳለብን ያስተምረናል።
ሣጥን: ራሳቸውን የሚወዱ ሰዎች አጋጥመውኛል። እንደነሱ ከመሆን እኔ ወደ ሣጥኔ ተመልሼ ብገባ እመርጣለሁ።
መሪው: ይኼኛው ለየት ያለ ነው። ራስሽን መውደድ ማለት ምን ያህል ዋጋ እንዳለሽ መገንዘብ ነው። አንቺ የእግዚአብሔር ልጅ ነሽ። አንቺን በዚህ መልኩ የፈጠረሽ እግዚአብሔር ዓላማ ስላለው ነው።

ሣጥን፡ እግዚአብሔር እኔን የፈጠረበት ዓላማማ ቀልድ አዋቂነቱን ለሰዎች ለማሳየት ነው።

*መሪው፡* የለም! ዓላማውን ለማወቅ የምትችዪው ሕይወትሽን ለርሱ አሳልፈሽ ስትሰጭና እርሱ ዋስትናሽ እንዲሆን ስትፈቅጅለት ነው።

ሣጥን፡ ነገሩ ቀላል ይመስላል።

*መሪው፡* ውሳኔ ማድረጉ ቀላል ነው። ነገር ግን ሕይወትሽን ዋስትና ከሌለበት ሁኔታ ዋስትና ወዳለበት መስመር መመለሱ ጥረትን ይጠይቃል። ይኼ በሂደት የሚቀጥል ነው። ይህም ከእንግዲህ ሕይወትሽን በአካባቢሽ ያሉ ሰዎች በሚያስቡት፣ በሌሎች ጓደኞችሽ ተፅዕኖ ላይ ተመሥርተሽ መምራት እንደሌለብሽ የሚያመለክት አስደሳች የዕድገት ሂደት ነው። አሁን የሚያሳስብሽ አንድ ነገር ብቻ ይሆናል። ይኸውም «ሕይወቴ ክርስቶስን በትክክል እያንጸባረቀው ነው ወይ?» የሚለው ነው። ውሳኔው ቅጽበታዊ ቢሆንም፣ የአኗኗር ለውጡ ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ግን...

ሣጥን፡ ግን ምን?

*መሪው፡* ግን ከዚያ ሣጥን በጣም የተሻለ ነው።

ሣጥን፡ *(ወደ ሣጥኑ ተመልክታ ለአፍታ ዝም ካለች በኋላ)፡* አዎ፣ ትክክል ሳትሆን አትቀርም። ሞት ወይም ሕይወት ወይም መላእክት ወይም እነዚያ ነገሮች ሁሉ ለማይለዩት የክርስቶስ ፍቅር ለመኖር እጀምራለሁ። *(ዝምታ)* ቀለል ብሎኛል። ያ ሣጥን ሁልጊዜም እያነሰ ይሄድ ነበር። *(ሣጥኑን ጎትታ ትወጣለች።)*

*መሪው፡* ይኼን ነገር ወዴት እየወሰድሽው ነው?

ሣጥን፡ ይቅርታ... ከሰዓቴ ጋር የተያያዘ ይመስለኛል።

***የመልእክቱ ማጠቃለያ***

ብዙዎቻችሁ እንደ የወንድ/የሴት ጓደኛ፣ ገንዘብ፣ ልብስ በመሳሰሉት ነገሮች ዋስትና ለማግኘት የሚጥሩ ጓደኞች አሏችሁ። በነዚህ ነገሮች ላይ ዋስትናችንን ስናሳርፍና እነዚህ ነገሮች ድንገት ከኛ ሲወሰዱ፣ ዋስትናችን ከኛ ይርቃል። እግዚአብሔር የዋስትናችን ምንጭ ለመሆን የሚፈልገው ለዚህ ነው። ዋስትናችንን በክርስቶስ ላይ በምናደርግበት ጊዜ፣ በፍጹም ሊነቃነቅ በማይችል ዓለት ላይ ዋስትናችንን አሳርፈናል ማለት ነው። በመክብብ ምዕራፍ ሁለት ውስጥ በመጠጥ፣ በትምህርት፣ በሴቶችና በሌሎች ብዙ ነገሮች ዋስትና ለማግኘት ስለሞከረ ሰው የተጻፈ ቃል እናነባለን። በአሥራ ሁለተኛው ምዕራፍ ውስጥ ይኸው ሰውዬ ፍለጋውን አብቅቶ ዋስትናውን በእግዚአብሔር ላይ ሲጥል እንመለከታለን። አንዳንዶቻችሁ ዋስትናችሁን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ አላደረጋችሁም። ዛሬ ይህንኑ ልታደርጉ ትችላላችሁ። ሁሉም ነገር ነፋስ እንደነፈሰበት አቧራ በኖ በሚጠፋበት ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ያላችሁ ግንኙነት በስፍራው ይቆያል። ይኼ አስተማማኝ እውነት ነው! የሰዎችን



**ፍላጎቶች ማሟላት ስልችቷችኋል? ዛሬ እግዚአብሔር የዋስትና እጆቹን ለናንተ ይዘረጋል።**

***መዝጊያ***

**(ወጣቶች ክርስቶስን ለመቀበል ወይም ከርሱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማጥበቅ እንዲወስኑ ጥሪ አድርግላቸው።)**

## አማራጭ የመክፈቻ እንቅስቃሴዎችና ጨዋታዎች

(እነዚህን ጨዋታዎች ከአካባቢህና ከወጣቶችህ ሁኔታ አንጻር አመቻችተህ ልትጠቀም ትችላለህ::)

1. ሰልፍ:: እንደ ቡድንህ አባላት ብዛት፣ ይህ እንቅስቃሴ በአንድ ቡድን ወይም በሁለትና ከዚያ በሚበልጡ ቡድኖች መካከል በሚደረግ ውድድር ሊካሄድ ይችላል:: «ከአሁን ጀምሮ በተቻለ ፍጥነት በቁመታችሁ ተሰለፉ» በላቸው:: በተጨማሪም፣ በልደት ቀናቸው፣ በስማቸው ፊደል ቅደም ተከተልና ከዚያም በመቆም .. በዚህ ጊዜ ከረገኙሞች ወደ አጫጭሮች እንዲሰለፉ ማድረግ ትችላለህ:: (ይህ ከ4 እስከ 6 ቡድኖች መካከል ሊደረግ ይችላል::)
2. ትክክል ወይም ስሕተት:: አምስት ጥያቄዎችን ድምጽህን ከፍ አድርገህ አንብብላቸውና መልሶቻቸውን በወረቀት ላይ እንዲጽፉ ጠይቃቸው:: ለአራቱ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሶችን፣ ለአንደኛው ጥያቄ ግን ሆን ብለው የተሳሳተ መልስ እንዲጽፉ ንገራቸው:: ወጣቶቹ መልሶቻቸውን በሚያነቡበት ጊዜ ሌሎቹ የተሳሳተው መልስ የትኛው እንደሆነ ይገምቱ::
3. ይህን ዓረፍተነገር ጨርሱልኝ: ወጣቶቹ ዓረፍተነገሩን እንዲጨርሱልህ ጠይቃቸው:: «እናቴ ወይም አባቴ ብትሆን ኖሮ...» ዓረፍተነገሩን በፈለጉት መንገድ እንዲጨርሱ ፍቀድላቸው:: በዚህ ላይ ትክክለኛና ትክክለኛ ያልሆነ መልስ ማግኘት አይቻልም::
4. የወጣቶችን አገልግሎት መሪ ምስል ሣሉ: ይህንን ተግባር ሦስት አባላት በሚገኙባቸው ቡድኖች ተከፋፍላችሁ አከናውኑት:: በአንድ ቡድን ውስጥ ከሚገኙት ሦስት ልጆች አንዱ የመሪውን (ወይም የፈለጋችሁትን የሌላ ሰው) ራስና አንገት በወረቀት ላይ ይሣል:: በተመሳሳይ ጊዜ ሁለተኛው ልጅ ከትከሻው እስከ ወገቡ፣ ሦስተኛው ልጅ የተቀሩትን የአካል ክፍሎችና እግሮች በራሱ ወረቀት ላይ ይሣል:: (ሁሉም ልጆች የሚሥሉት በተመሳሳይ ጊዜ በየራሳቸው ወረቀት ላይ ይሆናል::) ሦስቱም ሠርተው ሲጨርሱ፣ ወረቀቶቹን ሰብስበህ በማያያዝ ሙሉውን ሥዕል በክፍሉ ውስጥ ለሚገኙ ልጆች አሳይ::
5. የክፍሉን ወጣቶች በቡድን ከፋፍል:: የቡድኑ አባላት ቁጥር በጠቅላላው የአባላት ቁጥር የሚወሰን ይሆናል:: (በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ቢያንስ ከ4-5 ወጣቶች ሊኖሩ ይገባል::) ለእያንዳንዱ ቡድን አንድ ወረቀትና አንድ እርሳስ አድል:: ከዚያም ከእያንዳንዱ ቡድን አንድ ሰው ወደ መሪው በመሄድ ቡድኑ ምን እንደሚሥል ይሰማል:: (ለምሳሌ፣ ካልሲ፣ ቅርጫት፣ ጫጩት፣ ዛፍ፣ ወዘተ.) ከየቡድኑ ወደ መሪው የሄዱት ሰዎች ምን እንደሚስሉ ከሰሙ በኋላ ወደ ቡድኑ ሩጠው በመመለስ የታዘዙትን ይሥላሉ:: ምንም ዓይነት ቃላት መናገር ወይም መጻፍ የለባቸውም:: በመጀመሪያ የተሣለውን ነገር የገመተ ቡድን ነጥብ ያገኛል::
6. የምትወደኝ ከሆነ ፈገግ በልልኝ:: ሁሉም ክብ ሠርተው እንዲቀመጡና አንድ ሰው እንዲመርጡ አድርግ::

የተመረጠው ሰው ከክቡ መሀል ተቀምጦ አንድ ሰው ፈገግ እንዲልለት ማድረግ አለበት:: ፈገግ ያለው ሰው ወደ ክቡ መሀል በመሄድ ያስፈገገውን ግለሰብ ቦታ ይወስዳል:: እሱም በተራው በክቡ ዙሪያ ወዳሉት ሰዎች በየተራ እየሄደ፣ «የምትወደኝ ከሆነ እባክህን ፈገግ በልልኝ» በማለት ምላሽ ለማግኘት ይጥራል:: (ፈገግ ለማስባል የሚችለውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል::) የተጠየቀው ሰው ከክቡ መሀል ወዳለው ግለሰብ በመመልከት፣ «እወድሃለሁ:: ግን ፈገግ ማለት አልችልም» ሲል ሳይስቅና ፈገግ ሳይል ይመልስለታል:: መሀል ላይ ያለው/ያለችው ልጅ ግን ጥረቱን መቀጠል ይኖርበታል/ባታል::

7. በማምት ማወቅ:: እያንዳንዱ ወጣት ለሌሎች ሳያሳይ ራሱ ብቻ የሚያውቃቸውን የራሱን ምሥጢሮች (ለምሳሌ፣ ለሞኑን አንድ ከአሜሪካ የመጣ ሰው አጋጥሞኛል:: አንድ ጊዜ አንድ ዶሮ ውጥ ብቻዬን ግጥም አድርጌ በልቻለሁ) በወረቀት ላይ እንዲጽፍ አድርግ:: ወረቀቶቹን ሰብስብና እያንዳንዱ ሰው የጻፈውን አንብብ:: ከዚያም የክፍሉ ወጣቶች ዝርዝሮቹን ማን እንደጻፋቸው እንዲገምቱ ጠይቃቸው::
8. ታሪክ:: የመክፈቻ እንቅስቃሴ ከመጀመሩ በፊት፣ ከመጽሔቶች ወይም ጋዜጦች የሰዎችንና የቦታዎችን ሥዕሎች ቆርጠህ በመውጣት በወረቀቶች ላይ ለጥፋቸው:: አንድ ሥዕል በአንድ ወረቀት ላይ ለጥፍ:: ወጣቶቹን በአነስተኛ ቡድኖች በመከፋፈል ለእያንዳንዱ ቡድን ስምንት ሥዕሎችን አድል:: እያንዳንዱ ቡድን ስምንቱንም ሥዕሎች ተጠቅሞ አንድ ታሪክ እንዲያዘጋጅ ንገራቸው:: እያንዳንዱ ቡድን በክፍሉ ውስጥ ለሚገኙ ወጣቶች ያዘጋጀውን ታሪክ እንዲናገርና ከሁሉም የተሻለው ታሪክ በድምጽ ብልጫ እንዲመረጥ አድርግ::
9. በድምጽ ብቻ መመራት:: የቡድንህን አባላት ሁለት ሁለት አድርገህ ክፈል:: ከሁለቱ የአንዱን ዓይን በመሸፈን ሌላኛው እንዲመራው አድርግ:: መሪው ለጓደኛው የት መሄድ እንዳለበት ይነግረዋል እንጂ በእጁ ሊነካው አይችልም:: በክፍሉ ውስጥ ወይም ከክፍሉ ውጭ የሆነ መሰናክል አስቀምጥ:: ከሁሉም በፊት መንገዱን የሚጨርስ ቡድን አሸናፊ ይሆናል::
10. ቡድኖች:: ሙዚቃ እያጫወትህ ወጣቶቹ በሙሉ ክብ ሠርተው በክፍሉ ዙሪያ እንዲንቀሳቀሱ አድርግ:: ጨዋታው በሚካሄድበት

ጊዜ መሪው ሙዚቃውን በማስቆም የሆነ ነገር (ለምሳሌ፣ ቆርቆሮ) ሙክ አድርጎ ይመታል። በዚህ ጊዜ ወጣቶቹ በፍጥነት የተመታውን ቁጥር ያህል አባላት የሚገኙባቸውን ቡድኖች ይሠራሉ። ለምሳሌ ያህል፣ የወጣቶቹ ቁጥር 15 ቢሆንና መሪው ቆርቆሮውን ሰባት ጊዜ አከታትሎ ቢደበድብ፣ 7 አባላት የሚገኙ ባቸው ሁለት ቡድኖች ይፈጠሩና አንድ ሰው ይተርፋል። የተረፈው ሰው ከጨዋታ ውጭ ይሆናል። ሁለት ሰዎች ብቻ እስኪቀሩ ድረስ ጨዋታው ይቀጥልና ከጨዋታ ውጭ ሳይሆኑ የቆዩት ሁለቱ አሸናፊዎች ይሆናሉ።

11. **ከሙዚቃው ጋር መሄድ።** ወንበሮችን በክብ ቅርጽ ደርድር። የወንበሮች ቁጥር ከወጣቶቹ በአንድ ማነስ እንዳለበት አረጋግጥ። ይህ ቀላል ጨዋታ ነው። ሙዚቃው እየተጫወተ ሳለ (የቴፕ መዝሙር የሚጀምርና የሚያስቆም አንድ ሰው መድብ።) ሁሉም ሰው በወንበሮቹ ዙሪያ ይጓዛል። ሙዚቃው በሚቆምበት ጊዜ ሁሉም ሰው መቀመጥ አለበት። ሙዚቃው በቆመ ጊዜ ሁሉ አንድ ሰው ከጨዋታ ውጭ ይሆናል። ሙዚቃው በቆመ ጊዜ ሁሉ አንድ ወንበር መቀነስ እንዳለብህ አትዘንጋ። ጨዋታው አንድ ሰው ብቻ እስኪቀር ድረስ ይቀጥላል። ለአሸናፊው ሽልማት ወይም ለቡድኑ ነጥብ ስጥ።

12. **አፍ ውስጥ ዳቦ ማጨቅ።** አራት ወንዶችና አራት ሴቶች ወጣቶች ምረጥ። ወንዶቹ ጎን ለጎን ቆመው ወደተቀሩት ወጣቶች ፊታቸውን ማዞር ይኖርባቸዋል። ሴቶቹ ለወንዶቹ ዳቦ ያጎርሳሉ። ወንዶቹ ዳቦ ወደ አፋቸው በተጨመረ ቁጥር፣ «ጸጉራም ጥንቸል» ማለት አለባቸው። «ጸጉራም ጥንቸል» ማለት ካልቻሉ፣ የጎረሱትን ዳቦ ከተፉ ወይም ከዋጡ ከጨዋታው ውጭ ይሆናሉ። በመጨረሻው ላይ ብዙ ዳቦ በአፉ ውስጥ ይዞ የተገኘ ልጅ ያሸንፋል። ከዚያ በኋላ ወንዶቹ ሴቶቹን እንዲያጎርሱ በማድረግ፣ ሴቶቹ ምን ያህል ምግብ በአፋቸው ሊይዙ እንደሚችሉ ልትመለከት ትችላለህ።

13. **ዳቦ በስቲኪኒ የማስተላለፍ ጨዋታ።** ከተቻለ፣ እኩል አባላት የሚገኙባቸውን ሁለት ቡድኖች መርጠህ አሰልፋቸው። ለሁለቱም ቡድኖች አባላት በሙሉ ስቲኪኒዎችን አድልና ለእያንዳንዱ ቡድን አንዳንድ አነስተኛ ዳቦ ሰጣቸው። ይህንን ጨዋታ ለማካሄድ በሁለቱም ቡድኖች ውስጥ የሚገኙት ልጆች በሙሉ ስቲኪኒዎቻቸውን በአፋቸው እንዲይዙ ማድረግ ያሻል። አብዛኛው የስቲኪኒው አካል ከአፍ ውጭ ይሆናል። ዳቦው በመጀመሪያው ልጅ ስተኪኒ ላይ ይደረጋል። እሱም እጁን ሳይጠቀም ዳቦውን ወደሚቀጥለው ልጅ ስቲኪኒ ላይ ያስቀምጣል። ዳቦውን ለቀጣዩ ልጅ በሚያስተላልፍበት ጊዜ ስቲኪኒውም አብሮ ይሄዳል። ሁለተኛውም ልጅ በተመሳሳይ



ሁኔታ ዳቦውን ለቀጣዩ የቡድኑ አባል ያስተላልፋል። አሸናፊው ቡድን ዳቦውን ወደ መጨረሻው የቡድኑ አባል በቀዳሚነት ያስተላለፈ ይሆናል። በዚህም ጊዜ የመጨረሻው ልጅ ዳቦውን ብቻ ሳይሆን የቡድኑን አባላት ስቲኪኒዎች ሁሉ ከዳቦው ላይ ያገኛል።

14. **የዳቦ ውርወራ።** አራት ጥንድ ወጣቶችን ምረጥ። ከእያንዳንዱ ጥንድ ቡድን አንደኛው ልጅ ዳቦ ወርዋሪ፣ ሁለተኛው የተወረወረውን ዳቦ የሚቀበል ይሆናል። ዳቦ ወርዋሪዎቹ ጎን ለጎን እንዲሰለፉ አድርግ። ዳቦ ተቀባዮቹ ቢያንስ ሦስት ሜትር ያህል ከወርዋሪዎቹ ርቀው ይሰለፋሉ። ለወርዋሪዎቹ ለእያንዳንዳቸው 10 ዳቦዎች ስጣቸው። ዳቦ ተቀባዮቹ የሚወረወሩላቸውን ዳቦዎች በአፋቸው ይይዛሉ። እጆቻቸውን መጠቀም አይችሉም። አሸናፊው ቡድን ብዙውን ዳቦ የያዘው ይሆናል።

15. **የተወሰኑ ቁጥሮች ሲያጋጥሙ መቆም።** የቡድኑ አባላት በክብ ቅርጽ እንዲቀመጡ ንገራቸው። አንድ ሰው «1» ቁጥርን እንዲጠራ ጠይቅና እስከ «20» ቁጥር ድረስ በክቡ ዙሪያ የሚገኙ ልጆች ተራ በተራ እንዲጠሩ አድርግ። ሁለት ወይም ከዚያ የሚበዙ ቡድኖች ካሉ፣ ማን ከሁሉም ፈጥኖ እንደሚፈጽም ተመልከት። ይህንን ካደረግህ በኋላ፣ አሁን ሲጠሩ የተዘጋጁት ቁጥር በ«ሰ» ወይም በ«አ» የሚጀምር ከሆነ እንዲቆሙ ትነግራቸዋለህ። (ቁጥሩን ሳይጠሩ መነሣት አለባቸው።) ሁለት ወይም ከዚያ የሚበልጡ ቡድኖች ካሉ፣ የትኛው ቡድን ከሌሎች ፈጥኖ ይህንኑ እንደሚያደርግ ተመልከት። በሚሳሳቱበት ጊዜ ሁሉ እንደገና ይጀምራሉ።

16. **ራስን የመቆጣጠር ጨዋታ።** ከወጣቶቹ አንዱን ፊት ለፊት አስቀመውና በምንም ዓይነት ፈገግ ማለት እንደማይችል ንገረው። ከዚያም ለአንድ ደቂቃ ያህል በክፍሉ ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች እሱን ፈገግ ለማሰኘት የሚችሉትን ጥረት ሁሉ እንዲያደርጉ ንገራቸው። ወጣቶቹ ልጁን ከመንካት (ከመኮርኮር) ውጭ የመሰሏቸውን ቃላትና ድርጊቶች ሁሉ በመጠቀም ፈገግ እንዲልላቸው ሊሞክሩ ይችላሉ። አንዷ ደቂቃ እስክትጠናቀቅ ድረስ ፈገግ ሳይል ለቆየ ልጅ ሽልማት ስጠው።

17. **የመተማመን ጉዞ።** ለቡድንህ ወጣቶች መተማመን የመጨነቅ ተቃራኒ መሆኑን አብራራላቸው። ከመጨነቅ ይልቅ መተማመን ምን እንደሆነ ለመገንዘብ ይህ ጨዋታ ያግዛቸዋል። ወጣቶቹ ሁለት ሁለት እየሆኑ ቡድን እንዲፈጥሩ ንገራቸው። ከሁለቱ አንደኛው ዓይኖቹን በጨርቅ ይሸፈናል። (ወይም በእምነት ዓይኖቹን እንዲጨፍን ማድረጉ ብቻ በቂ ሊሆን ይችላል።) ሌላኛ ው ልጅ በመተማመን ጉዞ ላይ «ዓይነስውሩን» ይመራዋል።

የማያየው ልጅ ወዴት እንደሚሄድ አያይም። የሚያየውን ልጅ ሊነካው ወይም ሊይዘው አይችልም። መሪው ድምጹን በማሰማት ብቻ ይመራዋል። ይህ ጨዋታ ሌላውን ሰው በመተማመን ሙሉ በሙሉ በሱ ምሪት ላይ መደገፍ ምን ማለት እንደሆነ ለወጣቶቹ ጠቃሚ ትምህርት ይሰጣል። ለሁሉም ወጣቶች የአምስት ደቂቃ ጊዜ ስጣቸው።

18. የጋዜጣ ላይ አሰሳ። ወጣቶቹን በቡድን ከፋፍለህ ተመሳሳይ ጋዜጦችን ስጣቸው። ክፍለጊዜው ከመጀመሩ በፊት፣ በጋዜጣው ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች ዘርዝር። ዝርዝሩ የሰዎችን ስሞች፣ ፎቶች፣ መረጃዎች፣ ማስታወቂያዎች፣ ወዘተ. ሊያካትት ይችላል። ዝርዝሩን ለሁሉም ቡድኖች ስጣቸው። የተዘረዘሩትን ነገሮች በቀዳሚነት ከጋዜጣው ላይ ያገኘ ቡድን አሸናፊ ይሆናል።

19. የጋዜጣ ውድድር። ወጣቶቹ ከመነሻ መስመር ኋላ በሁለት ሰልፎች እንዲቆሙ አድርግ። ከክፍሉ ጥግ የግብ መስመር አብጅ። እያንዳንዱ የቡድን አባል (አንድ ጊዜ አንድ ሰው) በጋዜጦቹ ላይ እየተረማመደ ወደ ግቡ ይሄዳል። ለእያንዳንዱ ቡድን ሁለት ገጽ ጋዜጦች ይሰጡታል። አንደኛውን ገጽ ሲረግጡ ሁለተኛውን ከፊታቸው ትዘረጋላቸዋለህ። እግራቸው ከጋዜጣው አልፎ መሬት ከረገጠ ከእንደገና ይጀምራሉ። ከግቡ መስመር ላይ ከደረሱ፣ ሁለቱንም ጋዜጦች ይዘው በመመለስ ለተረኛው የቡድናቸው አባል ይሰጡታል። በቀዳሚነት ሁሉም አባላቱ ከግቡ መስመር የደረሱለት ቡድን አሸናፊ ይሆናል።

20. ጥያቄዎችና መልሶች። ለሁሉም ወጣቶች አንዳንድ ወረቀት ስጣቸው። ግማሾቹ ወጣቶች «እንዴት» የሚል ቃል የታከለባቸውን ጥያቄዎች እንዲጽፉ ንገራቸው። (ለምሳሌ፣ ሙዝ እንዴት ትልጣለህ?) የተቀሩት ግማሽ ወጣቶቹ ለማያውቁት ጥያቄ መልስ ይጽፋሉ። (ለምሳሌ፣ በሞቀ ውኃ ውስጥ በመጨመር።) የሁለቱንም ቡድኖች ሥራዎች በመሰብሰብ፣ አንድ ጥያቄና አንድ መልስ እያከታተልህ አንብብ። ውጤት በጣም አስቂኝ ሊሆን ይችላል። እንደገና ጥያቄዎቹን መልሶች፣ መልሶቹን ጥያቄዎች በማድረግ ልትዝናኑ ትችላላችሁ።

21. በኃይል መንፋት። በያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ከአራት እስከ ስምንት ተጨዋቾች እንዲኖሩ አድርገህ ወጣቶችን ከፋፍል። ለእያንዳንዱ ቡድን መሪ አንድ የመጸዳጃ ወረቀት አድል። የመጸዳጃ ወረቀቱ ድርብ ከሆነ፣ ይህንን ጨዋታ ቀለል ባለ ወረቀት ማካሄዱ ስለሚቀል ነጣጥለህ ስጣቸው። ምልክት በምትሰጥበት ጊዜ፣ የቡድን መሪዎቹ ከወንበር ላይ ወጥተው የመጸዳጃ ወረቀቶቹን ከቡድኑ አባላቱ ከፍ አድርገው ይጥላሉ። የጨዋታው ዓላማ የትኛው ቡድን ወረቀቱን በትንፋሽ እየነፋ በአየር ላይ ብዙ እንደሚያቆይ መመልከት ነው። ወረቀቱ ከሰው



ላይ ካረፈ፣ በሁለት ሰከንዶች ውስጥ ተነፍቶ መነሣት አለበት። ካልሆነ ቡድኑ ከጨዋታ ውጭ ይሆናል።

22. ተለጣጭ ላስቲክ። ስለ ውድድሩ ማብራሪያ ከመስጠትህ በፊት እያንዳንዱ ቡድን ሁለት ሁለት ተጨዋቾችን እንዲመርጥ ጠይቅ። ተጨዋቾቹ በክፍሉ ውስጥ ወዳሉት ወጣቶች ፊታቸውን አዙረው በመድረኩ ላይ ይሰለፉ። የአንድ ቡድን ተጨዋቾች አጠገብ ለአጠገብ መቆም አለባቸው። ለእያንዳንዱ ተጫዋች የሚለጠጥ ላስቲክ አድል። ተጨዋቾቹ እነዚህን ላስቲኮች በራሳቸው ላይ ያደርጋሉ። ከኋላ በኩል ተለጣጭ ላስቲኩ እስከ አንገታቸው ድረስ መውረድ አለበት። ከፊታቸው በኩል እስከ አፍንጫቸው ጫፍ ድረስ መድረስ አለበት። የጨዋታው ዓላማ ራስን በማወዛወዝ ላስቲኩን ከአንገት ላይ ማውረድ መቻል ነው። ጨዋታው አንተ በምትሰጣቸው ምልክት ይጀመራል። ከእያንዳንዱ ቡድን ሁለት ሰዎች በተሳካ ሁኔታ ላስቲኩን አንገታቸው ላይ እስኪያወርዱ ድረስ ውድድሩ እንደሚቀጠል አስረዳቸው።

23. ስም የመጥራት ጨዋታ። ይህን ጨዋታ ለማካሄድ የወጣቶቹ ቁጥር ቢበዛ ወይም ቢያንስ ችግር የለውም። ሁኔታው አመቺ ከሆነ ወጣቶቹ በክብ ቅርጽ ይቀመጡ። የመጀመሪያው ልጅ የአንድን ሰው ስም ከነአባቱ ይጠራል። ቀጣዩ ልጅ በሦስት ደቂቃዎች ውስጥ የመጀመሪያው ልጅ በጠራው ሰው አባት ስም የመጀመሪያ ፊደል የሚጀምር ስም እስከነ አባት ይጠራል። (ለምሳሌ፣ የመጀመሪያው ልጅ «ኤልሺስ ፕሬስሊ» የሚል ስም ቢጠራ፣ ሁለተኛው ልጅ «ፕሬይዝ ንደሉሹ» ሊል ይችላል።) በሦስት ሰኮንዶች ውስጥ ይህን መርህ በተከተለ መንገድ ስም ለመጥራት ያልቻለ ሰው ከጨዋታ ውጭ ይሆናል። ጊዜ ካለህ አንድ ሰው ብቻ እስኪቀር ድረስ ጨዋታውን ልትቀጥል ትችላለህ። እስከ መጨረሻው ከጨዋታ ውጭ ሳይሆን የቀረው ልጅ አሸናፊ ይሆናል።

24. እጅ ለእጅ መያያዝ። ተማሪዎቹ ክብ ሠርተው እንዲቆሙ አድርግ። (ከ12 የሚበልጡ ወጣቶች ካሉህ፣ ከ8 እስከ 10 የሚበልጡ ተማሪዎች በአንድ ቡድን ውስጥ እንዲገቡ አድርገህ ከፋፍል።) አንድ ልጅ የሌሎች ሁለት ልጆችን እጆች ይይዛል። ሁለቱ እጆች ከግራውና ከቀኙ ያሉት ልጆች እጆች መሆን አለባቸው። ተማሪዎቹ እንደተያያዙ አንድ ክብ እንዲሠሩ ንገራቸው።

25. በአንድ እግር እየዘለሉ መሮጥ። ቡድኖቹ በአንድ እግራቸው ከክፍሉ አንደኛ ጥግ እስከ ሌላኛው ድረስ እየዘለሉ እንዲሄዱ ንገራቸው። ከጥጉ ላይ ሲደርሱ የግራና የቀኝ እግር ጫማዎቻቸውን አውልቀው ይቀያይራሉ። ከዚያም ቅድም

በዘለሉበት ሳይሆን በሌላኛው እግራቸው እየዘለሉ ወደ ተቃራኒው ጥግ ይመለሳሉ። ቀድሞ የደረሰ ቡድን አሸናፊ ይሆናል።

26. ብርቱካን ማስተላለፍ። ለእያንዳንዱ ቡድን አንድ ብርቱካን አድል። ቡድኖቹ በሰልፍ መቆም አለባቸው። ከሰልፉ መጀመሪያ ላይ ላለው ሰው አንድ ብርቱካን ስጠው። ግለሰቡ ብርቱካኑን ከአገጩ ሥር አድርጎ ይቆይና ምልክት በሚሰጠው ሰዓት ለቀጣዩ ሰው እጁን ወይም ክንዱን ሳይጠቀም ያስተላልፋል። ብርቱካኑ ከአገጭ ወደ አገጭ እየተላለፈ ሰልፉን አዳርሶ መመለስ አለበት። አንድ ቡድን ብርቱካኑን ከጣለ ወይም በእጁና በክንዱ ከነካ፣ ከእንደገና መጀመር አለበት። ቀድሞ የጨረሰ ቡድን ነጥብ ያገኛል።

27. ቀይና አረንጓዴ መብራት። ሁሉም ሰው ወደ መሪው ፊቱን አዙሮ ይቆማል። መሪው ፊቱን አዙሮ፣ «አረንጓዴ መብራት» ይላል። ይህን በሚልበት ጊዜ ሁሉም ሰው ወደ ፍጻሜው መስመር ለመድረስ መንቀሳቀስ አለበት።። «ቀይ መብራት» በሚልበት ጊዜ ሁሉም ሰው በያለበት ይቆማል። መሪው በፍጥነት ፊቱን አዙሮ ሲመለከት በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ሰው ካየ እንደገና እንዲጀምር ይነግረዋል። የቡድን መሪው «አረንጓዴ ጠብ! አረንጓዴ ንክሹ - -» እያለ ቡድኖቹን ሊያሳስት ይችላል። ቀድሞ ለጨረሰ ቡድን ነጥብ ስጠው።

28. ኦክተፐስ (Octopus)። የጨዋታውን አካባቢ ለይተህ ምልክት አድርግ። አንደኛው ልጅ ኦክተፐስ (ሳምንት እጆች ያሉት አውሬ) ይሆናል። ሁሉም ልጆች በአንድ መስመር ይሰለፋሉ። ኦክተፐስ መሀል ላይ ይቆማል። ኦክተፐስ ከአንድ እስከ ሦስት በሚቆጥርበት ጊዜ ሁሉም በኦክተፐስ ሳይያዝ ወደ ሌላኛው የሜዳው ጫፍ ሩጠው መሄድ አለባቸው። ኦክተፐስ የነካው ሁሉ የኦክተፐስ ቡድን አባል ይሆንና ሌሎችን በመንካት «ለመማረክ» ይጥራል። ነገር ግን እግሮቻቸውን ማንቀሳቀስ አይችሉም። በተነኩበት ቦታ መቆም አለባቸው። ከአንድ እስከ ሦስት ሲቆጠር፣ ሁሉም እንደገና ወደ ሌላኛው ጫፍ ይሮጣሉ። ኦክተፐስና «እጆቹም» ሊይዟቸው ይሞክራሉ። (የኦክተፐስ «እጆች» እግሮቻቸውን ሊያንቀሳቅስ እንደማይችሉ አትዘንጋ!) ሁሉም ሰው ተነክቶ እስኪዳረስ ጨዋታው ይቀጥላል።

29. የፍራፍሬ ስም በመጥራት የሚካሄድ ውድድር። ልጆቹ በክብ ዙሪያ እንዲቀመጡ አድርግ። የብዙ ፍራፍሬዎች ስሞች ይመረጡና የአንድ ፍራፍሬ ስም ከ3-4 ለሚሆኑ ተጨዋቾች ይሰጣል። ለእያንዳንዱ ተጨዋች አንድ ፍራፍሬ ይሰጠዋል። የፍራፍሬዎቹን ስም የሚጠራ አንድ ሰው ከክቡ መሀል ይገባል። ልጁ የአንድን ፍራፍሬ ስም በሚጠራበት ጊዜ፣ የተጠራው የፍራፍሬ ስም የተሰጣቸው ተጨዋቾች ከክቡ መሀል ያለው ልጅ



ወንበር ከማግኘቱ በፊት ሌላ መቀመጫ ማግኘት ይኖርባቸዋል። ከተጨዋቾቹ መካከል ወንበር ሳያገኝ የቀረው ልጅ መሀል ይገባል። መሀል ያለው ልጅ «የፍራፍሬ ቅርጫት ገለበጡ» ካለ፣ ሁሉም ተጨዋቾች ወንበር ይቀይራሉ።

30. የጭብጨባ ፈተና። መሪው እጆቹን ሲያጣምር ወጣቶቹ ያጨበጭባሉ። ሳያጣምር ካጨበጨቡ ወይም አጣምሮ ሳለ ካላጨበጨቡ ከክፍሉ ይወጣሉ።

31. ፊኛ የማፈንዳት ውድድር። በእያንዳንዱ ልጅ ቁርጭምጭሚት ላይ ፊኛ እሰር። የጨዋታው ዓላማ ልጆቹ የራሳቸውን ፊኛዎች ከመፈንዳት እየተከላከሉ የሌሎቹን ፊኛዎች ማፈንዳታቸው ነው። ለተለያዩ ቡድኖች የተለያዩ ቀለሞች ያሏቸውን ፊኛዎች በመስጠት ይህንን ጨዋታ በቡድን መልክ ማካሄድ ይቻላል።

32. ኤሌክትሪሲቲ። ሁለት ቡድኖች ፊት ለፊት ይቀመጣሉ። የቡድን አባላቱ እጅ ለእጅ ይያያዛሉ። ከሁለቱም ቡድኖች ከመጀመሪያው መስመር ላይ የሚገኙ ልጆች መሪው እሥር ሣንቲም ሲወረውር ያያሉ። ሣንቲሙ የወደቀው በአንበሳው በኩል ከሆነ፣ የመጀመሪያው ልጅ ከሱ ቀጥሎ ያለውን ልጅ እጅ ይይዛል። እሱም የቀጣዩን... እያለ ይቀጥላል። የመጨረሻው ልጅ እጁ በሚያዝበት ጊዜ ከሰልፉ መጨረሻ ላይ የሚገኘውን ነገር ይይዛል። የኤሌክትሪክ መስመሩን በመፍጠር ቀዳሚ የሚሆነውና ከሰልፉ መጨረሻ የሚገኘውን ነገር የሚይዘው ቡድን አሸናፊ ይሆናል። ከዚያም የአሸናፊው ቡድን የመጨረሻው ልጅ ወደ ሰልፉ መጀመሪያ ይሄዳል። አባላቱ ተቀያይረው ሲያበቁ ጨዋታው ይጠናቀቃል። (የቡድኑ አባላት ተገቢ ባልሆነ ጊዜ የጓደኞቻቸውን እጆችና ከሰልፉ መጨረሻ ላይ ያለውን ነገር በሚይዙበት ጊዜ በተቃራኒ አቅጣጫ መዞር አለባቸው። ይህም ማለት ከሰልፉ በመጀመሪያው መስመር ላይ የነበረው ልጅ ወደ መጨረሻው ይሄዳል። በተጨማሪም፣ ልጆቹ የሰልፉን የመጨረሻ መስመር እንጂ የመጀመሪያ መስመር መመልከት የለባቸውም።)

33. ከሌሎች ቀድሞ መቀመጥ። ሁሉም ልጆች በክብ መልክ በወንበሮች ላይ ይቀመጣሉ። አንድ ልጅ ይመረጥና ወደ መሀል ገብቶ ይቆማል። በዚህ ጊዜ አንድ ባዶ ወንበር ይኖራል ማለት ነው። የጨዋታው ዓላማ መሀል ገብቶ የቆመው ልጅ በባዶ ወንበሩ ላይ ከሌሎች ቀድሞ መቀመጥ መቻሉ ነው። ሌሎች ልጆች ወደዚያ ወንበር ፈጥነው በመቀመጥ ልጁ ባዶ ቦታ እንዳያገኝ ይከላከሉታል። ልጁ ወንበር አግኝቶ ከተቀመጠ ከወንበሩ በስተግራ ያለው ልጅ መሀል ይገባል።

34. መያያዝ። አንድ ሰው ከጓደኛው ጋር አንድ ክንዱን ያያይዛል። ሁሉም ጥንዶች በትልቅ ክብ ዙሪያ ይቆማሉ። ከዚያም አብረው የተያያዙ ሁለት ልጆች ተፈተው ከመሀል ይገባሉ። አንዱ ሌላኛ

ውን ያሳድደዋል። ተሳዳጁ ልጅ አሳዳጁ ሳይዘው በፊት ተያይዘው ከሚገኙ ሌሎች ጥንዶች ጋር ለመጣመር ይጥራል። ከሌላ ቡድን ጋር በሚጣመርበት ጊዜ፣ ሦስተኛ ሆኖ የሚቀረው ልጅ ሌላ ተጣማሪ መፈለግ አለበት። አሳዳጁ ከያዘው ግን ተሳዳጁ ወደ አሳዳጅነት ይቀየራል።

35. የዓይን ጥቅሻ። ሴት ልጆች በክብ ቅርጽ ይቀመጣሉ። ከእያንዳንዷ ሴት በስተጀርባ አንድ ወንድ ይኖራል። ከአንድ ልጅ ፊት አንድ ባዶ ወንበር ይቀመጣል። የጨዋታው ዓላማ ልጁ በዓይኑ በሚያስተላልፍላት ምልክት (ጥቅሻ) መሠረት ከሴት ልጆች አንዷ ከኋላዋ ያለው ልጅ ሳይነካት በፊት ከባዶው ወንበር ላይ እንድትቀመጥ ማስቻል ነው። ከሴቶቹ ኋላ ያሉት ወንዶች ባዶ ወንበር ያለው ልጅ ለሴቶቹ የዓይን ምልክት መስጠታቸውን ሳይመለከቱ ቢችሉም፣ ከፊታቸው ያሉት ሴቶች በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ለመንካት መጣር አለባቸው።

36. የመጨባበጥ ጨዋታ። መጀመሪያ አንድ ልጅ ይመረጣል። ከዚያ በኋላ ልጆቹ የሌሎችን እጆች እየጨበጡ ራሳቸውን ያስተዋውቃሉ። ተመራጩ ልጅ ሦስት ጊዜ በመጨበጥ ልጆቹን ከጨዋታ ውጭ ያደርጋቸዋል። ተመራጩ ሦስት ጊዜ የጨበጠው ልጅ ሦስት ሰዎችን በመጨበጥ ከጨዋታው ውጭ ይሆናል። ዓላማውም ተመራጩ ልጅ ልጆቹ ተመራጩ ማን እንደሆነ ከመገመታቸው በፊት ከጨዋታ ውጭ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። አንድ ልጅ ተመራጩን በትክክል ካላወቀ ከጨዋታው ውጭ ይሆናል።

37. የመጨባበጥ ጨዋታ። ልጆቹ እጅ ለእጅ ተያይዘው በክብ መልክ ይቀመጣሉ። ከዚያ በፊት ግን አንድ ልጅ ይመረጣል። የተመረጠው ልጅ የተወሰነ ጊዜ በመጨበጥ ልጆችን ከቡድኑ ውስጥ ያስወጣል። ከበስተቀኙ ያለውን ልጅ ሦስት ጊዜ ከጨበጠ፣ ያ ልጅ ከሱ ቀጥሎ ያለውን ልጅ ሁለት ጊዜ ይጨብጠዋል። እሱም በበኩሉ ከአጠገቡ ያለውን ልጅ አንድ ጊዜ ይጨብጠዋል። አንድ ጊዜ ብቻ የሚጨበጡ ልጆች ከጨዋታው ውጭ ይሆናሉ። ዓላማውም ተመራጩ ልጅ ልጆቹ ተመራጩ ማን እንደሆነ ከመገመታቸው በፊት ከጨዋታ ውጭ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። አንድ ልጅ ተመራጩን በትክክል ካላወቀ ከጨዋታው ውጭ ይሆናል። ይህ ጨዋታ በጨለማ ወይም መጠነኛ ብርሃን ብቻ ባለበት ቦታ ቢካሄድ መልካም ነው።

38. ምርኮ። ሁለት ቡድኖች በአንድ ብርድልብስ ተጋርደው ወዲያና ወዲህ ይቆማሉ። ሁለቱ ቡድኖች የሚጋረዱበትን ብርድልብስ ይዘው የሚቆሙት ከእያንዳንዱ ቡድን የተመረጡ ሁለት ልጆች ይሆናሉ። 1፣ 2፣ 3! ተብሎ ሲቆጠር፣ ብርድልብሱ ይለቀቅና ሁለቱ ቡድኖች ፊት ለፊት ይፋጠጣሉ። በዚህ ጊዜ ከፊታቸው



የቆሙትን ልጆች ስም በትክክል የሚጠሩ ልጆች አሸናፊዎች ይሆናሉ። ተሸናፊዎቹ ልጆች ወደ አሸናፊዎቹ ቡድን ይገባሉ። የአንድ ቡድን አባላት በሙሉ ወደ ሌላኛው ቡድን ገብተው በሚያልቁበት ጊዜ ጨዋታው ይጠናቀቃል።

39. ድርደራ። ሁሉም በክብ መልክ ይቀመጣሉ። መሪው አንድ ገለጻ ያነባል። ገለጻው ከሁኔታው ጋር የተመሳሰለበት ሰው ወደ ቀኝ አንድ መቀመጫ ይጠጋል። ለምሳሌ፣ መሪው ረዥም ጸጉር ካለህ፣ ወደ ቀኝህ አንድ መቀመጫ ተጠጋ ሊል ይችላል። አረንጓዴ ካልሲ ያደረገ ሰው ካለ አንድ መቀመጫ ወደ ቀኙ ይጠጋ። ከቀኛቸው ባለው ወንበር ላይ ሰው ካለበት ሊያንቀሳቅሱት አይችሉም። ነገር ግን በተቀመጠው ልጅ ታፋ ላይ ይቀመጣሉ። በአንድ ወንበር ላይ 3፣4፣5 ወይም ከዚያ የሚበዛ ሰው ሊቀመጥ ይችላል። ለእያንዳንዱ ጨዋታ ከ15-20 ገለጻዎችን አንብብ።

40. ምርኮ። ሁለት ቡድኖች ከመሃል ይሰለፋሉ። (ለቡድኖቹ ስሞች ይሰጣቸዋል።) ከአንድ እስከ ሦስት በሚቆጠርበት ጊዜ፣ መሪው ከሁለቱ ቡድኖች የአንደኛውን ስም ይጠራል። የቡድናቸው ስም የተጠራባቸው ልጆች ፈጥነው በመሮጥ የተቃራኒያው ቡድን ልጆች ከመስመሩ ላይ ሳያደርሱ ለመያዝ ይሞክራሉ። የተያዘው ልጅ ሁሉ በምርኮኛነት የአሸናፊው ቡድን አባል ይሆናል። ከዚያም ቡድኖቹ እንደገና ተሰልፈው ተመሳሳይ ነገር ያደርጋሉ። አንዱ ቡድን የሌላኛውን ቡድን አባላት በሙሉ በሚማርክበት ጊዜ ጨዋታው ይጠናቀቃል።

41. ጎሪላ፣ ጠመንጃ፣ ሴት። አንድ የመሀል መስመርና ሁለት የመጨረሻ መስመሮችን ሥራ። የመጨረሻ መስመሮች ከመሀል መስመር 15 ሜትሮች ያህል መራራቅ አለባቸው። እያንዳንዱ ቡድን ከመስመሩ ላይ ሆኖ ለመሆን የሚፈልገውን ይወስናል። ጎሪላዎች ሴቶችን ያሳድዳሉ። ጠመንጃ ጎሪላዎችን ያሳድዳል። ሴቶች ጠመንጃን ያሳድዳሉ። እያንዳንዱ ቡድን ምን ለመሆን እንደሚፈልግ ከወሰነ በኋላ፣ ወደ መስመሩ ይጠጋል። ከአንድ እስከ ሦስት በሚቆጠርበት ጊዜ፣ እያንዳንዱ ቡድን የመረጡትን ነገር ለመምሰል ይጥራል። (ሴቶች እንደ ሴት እጆቻቸውን ከራሳቸውና ከዳሌያቸው ላይ ያደርጋሉ። ጎሪላዎች እንደ ሀይለኛ ጎሪላ ይውረገረጋሉ። ጠመንጃዎች የሌባ ጣቶቻቸውን በመቀሰር ሽጉጥ የሚተኩሱ ይመስላሉ።) አሸናፊው ቡድን ሌላውን ቡድን ሲያሳድድ፣ ተሸናፊው ቡድን ግን ከመስመሩ መጨረሻ ለመድረስ የሚችለውን ያህል በፍጥነት ይሮጣል። የአሸናፊው ቡድን አባላት ተሸናፊዎቹ ከመስመሩ ላይ ሳይደርሱ በፊት ቢይዟቸው፣ የቡድናቸው አባላት አድርገው ይማርኩዋቸዋል። ከዚያ በኋላ ቡድኖቹ ተመካክረው ምን ለመሆን እንደሚፈልጉ ይመርጡና

ይወዳደራሉ። አንዱ ቡድን ሙሉ በሙሉ ተማርኮ በሚያልቅበት ጊዜ ጨዋታው ይጠናቀቃል።

42. **መቁጠር**። ሁለት ልጆች እጆቻቸውን ወደ ኋላ አድርገው ፊት ለፊት ይቆማሉ። እስከ ሦስት በሚቆጠርበት ጊዜ፣ እጆቻቸውን ወደፊት በማምጣት የተወሰኑ ጣቶቻቸውን ወደ ላይ ከፍ አድርገው ያሳያሉ። የጨዋታው ዓላማ ወደላይ የሚያመለክቱትን ጣቶች ድምር በቀዳሚነት ማወቅ ይሆናል። ሦስት ያህል ጨዋታዎችን አካሂድና ከእያንዳንዱ ጥንድ አሸናፊ የሆኑትን ከሌሎች አሸናፊዎች ጋር አወዳድር። ተሸናፊዎቹ ከጨዋታ ውጭ ይሆናሉ። አንድ አሸናፊ እስኪቀር ድረስ ውድድሩን ቀጥል።

43. **መደበቅ**። አንድ ልጅ ተመርጦ ይደበቅና የተቀሩት ሁሉ ይፈልጉታል። ልጁን ካገኙት በኋላ አብረውት ይደበቃሉ። ከሁሉም በኋላ መጀመሪያ የተመረጠውን ልጅና ከሱ ጋር የተደበቁትና ያገኘው ልጅ ለሚቀጥለው ጨዋታ በቀዳሚነት ይደበቃል።

44. **የከበሮ ወይም የድራም ድለቃ**። ብዙ ወጣቶች ላሉበት ቡድን የሚስማማ ጨዋታ። ሙዚቃ እየተጫወተ ቡድኑ በቡድን ይጓዛል። ሙዚቃው ሲቆም መሪው ከበሮ ወይም ድራም ወይም ሌላ ነገር የተወሰነ ያህል ጊዜ እከታትሎ ይደልቃል። ልጆቹም እሱ የደለቀውን ቁጥር በሚያሟሉ አባላት ይቧደናሉ። ለምሳሌ፣ ከበሮውን ሦስት ጊዜ ቢደልቅ ሦስት አባላት የሚገኙባቸውን ቡድኖች ይመሠርታሉ። ቶሎ ቡድን ያልመሠረቱ ወይም ትክክለኛ የቡድን አባላት የሌሏቸው ልጆች ከጨዋታው ውጭ ይሆናሉ። ከዚያም ሙዚቃው ተከፍቶ ጨዋታው ይቀጥላል።

45. **የውኃ ፊኛ ቮሊቦል**። ለእያንዳንዱ ቡድን አንድ ትልቅ አንሶላ አድል። በቮሊቦል ኳስ ምትክ በውኃ የተሞላ ፊኛ ተጠቀም። ልጆቹ ኳሱን በመምታት ፋንታ የውኃውን ፊኛ በአንሶላቸው ላይ አድርገው በጋራ እየተጫወቱ ከመረብ ውስጥ መጨመር ይኖርባቸዋል። ሌላው ቡድን የውኃ ፊኛውን በአንሶላው ይይዛል። ማንም የውኃ ፊኛውን በእጁ መንካት አይችልም። ነጥቦቹ የሚሰጡት በመደበኛው የቮሊቦል ጨዋታ ደንብ ይሆናል።

46. **እሳዶ መያዝ**። ሰፊ የጨዋታ ስፍራ አዘጋጅ። አንድ ሰው ይመረጥና ሌሎችን እንዲያሳድድ ይደረጋል። አንድን ልጅ አሳዶ በሚይዝበት ጊዜ ከልጁ ጋር ግንባር ይፈጥሩና ሌሎችን ለመያዝ ይሞክራሉ። የተያዘው ሰው ሁሉ የነሱ አባል በመሆን ሌሎችን ያሳድዳል። አሳዳጆቹ እየበዙ ሲሄዱ በፍጥነት ለመሮጥ ሊያስቸግር ይችላል። ግን ያልተያዙትን ልጆች በቀላሉ ሊይዙ ይችላሉ። የጨዋታው ዓላማ አሳዳጆቹ ተሳዳጆቹን ሁሉ



እንዲይዙ ማድረግ ነው። መጨረሻ ላይ የተያዘው ልጅ የጨዋታው አሸናፊ ይሆናል።

47. **መሪውን መገመት**። ስለ ጨዋታው ማብራሪያ ካደረግህ በኋላ ፈቃደኛ የሆነ አንድ ሰው ወደ ውጭ እንዲወጣ አድርግ። ከዚያ በኋላ የተቀሩት ወጣቶች ክብ ሠርተው በመቆም አንድ መሪ ይመርጣሉ። ቡድኑ መሪው የሚያደርገውን ነገር ያደርጋል። ወደ ውጭ የወጣው ልጅ ተመልሶ ከክቡ ውስጥ በመቆምና ወጣቶቹ የሚያከናውኑትን ተግባር በመመልከት መሪው ማን እንደሆነ ይገምታል። ሦስት ዕድሎች ይሰጡትና መሪውን ካወቀ መሪ የነበረው ልጅ ወደ ውጭ እንዲወጣ ይደረጋል። ከሦስት ሙከራዎች በኋላ መሪውን ካላወቀ፣ ወደ ውጭ የሚወጣ ሌላ ሰው ይመርጣል።

48. **የዜማ ምት**። 15 ወይም ከዚያ የሚያንሱ ልጆች ሊጫወቱ ይችላሉ። ሁሉም በክብ ተቀምጠው በአንድነት አንድ ጊዜ እግሮቻቸውን በጥፊ በመምታት፣ አንድ ጊዜ በማጨብጨብ፣ የግራ እጆቻቸውንና ከዚያም የቀኝ እጆቻቸውን ጣቶች በማፋጨት ይጫወታሉ። ሁሉም ልጆች ይህን ጨዋታ የዜማ ምቱን በጠበቀ ሁኔታ መከናወን አለባቸው። መጀመሪያ ቀዳሚው ልጅ ይጫወታል። የቀኝ ጣቶቹን ስንት ጊዜ እንዳፏጨና ሌላው ልጅ የግራ ጣቶቹን ስንት ጊዜ እንዳፏጨ ይናገራል። ከዚያም እሱ የጠቀሰው ልጅ ምቱን ሳያቋርጥ የራሱን የቀኝ ጣቶችና የሌላውን ልጅ የግራ ጣቶች ፋጨት ስንት እንደሆነ ይናገራል። አንድ ልጅ ትክክል ያልሆነ የጣት ማፏጨት ቁጥር ቢናገር ወይም ምቱን ቢያቋርጥ፣ በክቡ ውስጥ የነበረውን ስፍራ በማጣት ወደ ክቡ መጨረሻ ይሄዳል። ሁሉም ልጆች በዚሁ መሠረት ቁጥራቸውን ይቀይራሉ። የጨዋታው ዓላማ ከቁጥር አንድ ስፍራ መድረስ ነው።

49. **ኳስን ከተቃራኒ ቡድን ግብ ወርውሮ የማስገባት ውድድር**። ሁለት ቡድኖችን መሥርት። የጨዋታው ዓላማ ኳስን ወይም ሌላ ነገር ከተቃራኒ ግብ ውስጥ ማስገባት ነው። ይህም የሚከናወነው ኳሱን በመወርወር ብቻ ነው። የአንድ ቡድን አባል ኳሱን ከተቀበለ በኋላ ሁለት እርምጃዎች ይሄድና (የተቃራኒው ቡድን ተጨዋቾች ሊነጥቀው እየሞከረ) ለጓደኛው ያቀብላል። ኳሷ ከወደቀች ቀረብ ብሎ ላለው የተቃራኒ ቡድን ተጨዋች ትሰጣለች። ግብ ከተቆጠረ በኋላ፣ ኳሷ ለተቃራኒው ቡድን ትሰጥና ለማስገባት ይሞክራሉ። ብዙ ግብ ያስቆጠረ ቡድን የጨዋታው አሸናፊ ይሆናል።

50. **የጭራ ጉተታ**። በያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ከ5-10 አባላት እንዲኖሩ አድርገህ አከፋፍላቸው። የቡድኑ አባላት እጅ ለእጅ ይያያዛሉ። ከቡድኑ በአንደኛው ጫፍ በኩል ያለው መሪ (ራስ)፣

በሌላኛው ጫፍ በኩል ያለው ደግሞ ጅራት ይሆናል። የሁሉም ቡድኖች ጅራቶች ከልብሳቸው ጋር የሚያያዝ ጭራ ነገር ከኋላቸው እንዲያስሩ አድርግ። የጨዋታው ዓላማ የሁሉም ቡድን መሪዎች የራሳቸውን ቡድኖች ጭራዎች እየተከላከሉ የሌሎቹን ቡድኖች ጭራዎች ነትተው መውሰድ መቻላቸው ነው። ጭራው የጠፋበት ወይም የተቀደደበት ቡድን ከጨዋታ ውጭ ይሆናል። እስከመጨረሻው ጭራውን ይዞ የቆየ ቡድን አሸናፊ ይሆናል።

51. ግርግር። ለዚህ ጨዋታ እኩል አባላት ያሏቸው አራት ቡድኖች ያስፈልጋሉ። ሁሉም ቡድኖች ወደ ክፍሉ አንድ ጥግ ወይም የመጫወቻ ሜዳ ይሄዳሉ። ምልክት በሚሰጥበት ጊዜ እያንዳንዱ ቡድን አባላቱን ሳይነጣጥል የታዘዘውን እንቅስቃሴ እያደረገ በተቻለው ፍጥነት ዝግዛግ (ሰያፍ) ወደ ተቃራኒ ጥግ ይሄዳል። ሁሉም አባሎቹ ቀድመው ወደዚያኛው ጥግ የደረሱለት ቡድን የዙሩ አሸናፊ ይሆናል። የመጀመሪያው ዙር ወደዚያኛው ጥግ ዝም ብሎ ሩጦ መድረስ ሊሆን ይችላል። ከዚያ በኋላ እንደ ወደኋላ መራመድ፣ ሌሎችን ከጀርባ ላይ አዝሎ መሄድ፣ እንደ እንቁራሪት መዝለል፣ ያሉትን እንቅስቃሴዎች ሊያደርጉ ይችላሉ። ከክፍሉ መሀል ላይ ቡድኖቹ ሌሎቹን ቡድኖች አቋርጠው ለማለፍና አሸናፊ ለመሆን በሚሞክሩበት ጊዜ ከፍተኛ ግርግር እንደሚፈጠር ግልጽ ነው።

52. ከተፈጩ ድንች ውስጥ ክብ ነገር መፈለግ። ክፍለጊዜው ከመጀመሩ በፊት፣ ሦስት ጎድጓዳ ሳሕን የሚሆን የተፈጨ ድንች (ወይም ሌላ ለስላሳና የሚጣበቅ ነገር) አዘጋጅ። እያንዳንዱ ጎድጓዳ ሳሕን የልጆቹን ፊት ለማስገባት የሚችል ሰፊ መሆን አለበት። ከእያንዳንዱ ጎድጓዳ ሳሕን ሥር አንዳንድ አነስተኛ ክብ ነገር አስቀምጥና ከላዩ ላዩ የተፈጨውን ድንች ክምር። እያንዳንዱ ቡድን አንድ ተሳታፊ እንዲመርጥ ጠይቅ። እያንዳንዱ ተሳታፊ እጁን ወደ ኋላ ዘርግቶ ከጎድጓዳ ሳሕኑ ፊት እንዲንበረከክ ጠይቅ። ምልክት በምትሰጥበት ጊዜ፣ አፋቸውን ወደ ጎድጓዳ ሳሕኖቹ ውስጥ በተው ክቧን ነገር መፈለግ ይኖርባቸዋል። ባገኟት ጊዜ በአፋቸው ይዘው ያወጧታል።

53. የቀለበት ቅብብሎሽ። እኩል አባላት የሚገኙባቸውን ሁለት ቡድኖች አሰልፍ። ለሁለቱም ቡድኖች አባላት በሙሉ ስቲኪኒዎችን አድልና ለእያንዳንዱ ቡድን አንዳንድ አነስተኛ ቀለበት ሰጣቸው። ይህንን ጨዋታ ማካሄድ የሚቻለው በሁለቱም ቡድኖች ውስጥ የሚገኙት ልጆች በሙሉ ስቲኪኒዎቻቸውን በአፋቸው እንዲይዙ በማድረግ ነው። አብዛኛው የስቲኪኒው አካል ከአፍ ውጭ ይሆናል። ቀለበቱ በመጀመሪያው ልጅ ስቲኪኒ ላይ ይደረጋል። እሱም እጁን ሳይጠቀም ወደሚቀጥለው ልጅ



ስቲኪኒ ላይ ያስቀምጠዋል። ሁለተኛውም ልጅ በተመሳሳይ ሁኔታ ቀለበቱን ለቀጣዩ የቡድኑ አባል ያስተላልፋል። ቀለበቱ ከወደቀ ቡድኑ ጨዋታውን ከመጀመሪያው ልጅ ይጀምራል። አሸናፊው ቡድን ቀለበቱን ወደ መጨረሻው የቡድኑ አባል በቀዳሚነት ያስተላለፈ ይሆናል።

54. መዝገበ ቃላት። ተማሪዎችህ የማያውቋቸውን ከ5-10 የሚሆኑ ቃላት ከመዝገበ ቃላት ምረጥና ሁሉም ሊያዩ በሚችሉበት ስፍራ (ጥቁር ሰሌዳ ላይ) ጻፍ። ከዚያም ለእያንዳንዱ ተማሪ ወረቀቶችን አድል። ተማሪዎቹ የቃላቱ ፍች ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን ነገሮች እንዲጽፉ ንገራቸው። ወረቀቶቹን ሰብስብና ተመሳሳይ የሆኑትን ቃላት አንድ ላይ አድርግ። ትክክለኛ ፍች የተሰጣቸውን ከ4-5 የሚሆኑ ጽሑፎች በክፍሉ ውስጥ አንብብ። ተማሪዎቹ ትክክለኛውን ፍች እንዲገምቱ ጠይቃቸው።

55. የስሜት መግለጫ። ተማሪዎችህን ከ4-6 አባላት እንዲኖራቸው አድርገህ ከፋፍል። ከዚያም እንድን ስሜት ጥቀስ (እንደ ፍቅር፣ ጥላቻ፣ ቁጣ፣ ፍርሃት ባሉት ግልጽ ስሜቶች ጀምር።) እንዳንዱ ቡድን የተነገረውን ስሜት በአባላቱ ሰውነት ተጠቅሞ በቅርጻቅርጽ መልክ (አብስትራክት ወይም ግልጽ) ያሳይል። ቡድኖቹ ቅርጻቅርጻቸቸውን እንዲያሳዩ በቂ ጊዜ ስጣቸው። ከዚያም ተራ በተራ ቡድኖቹ ቅርጻቅርጻቸቸውን እንዲያቀርቡ አድርግ። ከዚያም ሌላ ስሜታቸውን የሚገልጹበትን ቃል ስጣቸው።

56. መረብ። ሁሉም ቡድኖች በክብ ዙሪያ እንዲቆሙ አድርግ። ሰዎች ቢበዙ ጥሩ ስለሚሆን፣ መሪዎችንም ጨምር። ከእያንዳንዱ ቡድን ለአንድ ልጅ አንድ የተጠቀለለ ሲባጎ ወይም ክር አድል። ሲባጎውን የተቀበለው ልጅ አንድ የሚያስደስተውን (ወይም የሚሳዝውን፣ ወይም የሚያስለቸውን፣ ወዘተ.) ነገር ለቡድኑ እንዲናገር ጠይቀው። ይህ ልጅ የሲባጎውን ጫፍ ይይዝና ጥቅልሉን ለሌላ የቡድኑ አባል ይወረውራል። እሱም እንደዚያው ያደርጋል። በዚህ ዓይነት መረብ መፍጠር ይቻላል።

57. ኪሶችን ባልዲዎች ውስጥ ማንጠር። ከ5-6 የሚሆኑ የተለያየ መጠን ያላቸው ባልዲዎችን አሰልፍ። ከአስቸጋሪነት አንጻር ለእያንዳንዱ ነጥብ ስጥ። እያንዳንዱ ተማሪ ከባልዲዎቹ ከ2-3 ሜትር ርቆ እንዲቆም አድርግና ትንሽ ኳስ ስጠው። የጨዋታው ዓላማ ኳሱ ከባልዲዎቹ አንዱ ውስጥ ገብቶ እንዲነጥር ማድረግ ነው። ተማሪው ነጥብ የሚያገኘው ኳሱ ባልዲው ውስጥ ገብቶ ቢያንስ አንድ ጊዜ ከነጠረና እዚያው ከቀረ ብቻ ይሆናል። ኳሶቹ ተለይተው እንዲታወቁና ብዙ ልጆች በአንድ ጊዜ ብዙ ልጆች እንዲጫወቱ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ኳሶቹን የተለያየ ቀለም ቀባቸው። ሁሉም ትልቅ ነጥብ በሚያስገኘው ባልዲ ውስጥ

ኪሱን ለማንጠር በሚጥርበት ጊዜ፣ ኪሶቻቸው እርስበርስ ይማታሉ::

58. የዚፕ-ዛፕ ጨዋታ:: ይህ ስም የመጥራት ጨዋታ የተዘጋጀው የቡድኑ አባላት የጓደኞቻቸውን የመጀመሪያ ስሞች መጥራት እንዲለምዱ ለማበረታታት ነው:: የቡድኑ አባላት በክብ ዙሪያ ተቀምጠው ሳሉ መሪው ወደ አንድ ልጅ በማመልከት፣ «ዚፕ፣ አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት» ወይም «ዛፕ፣ አንድ፣ ሁለት...» ይላል:: ልጁ ከአንድ እስከ አምስት ሳይቆጠርበት «ዚፕ» ለሚለው ከበስተቀኙ ያለውን ልጅ የመጀመሪያ ስም፣ «ዛፕ» ለሚለው ከበስተግራው ያለውን ልጅ የመጀመሪያ ስም በፍጥነት መናገር አለበት:: እስከ አምስት ከተቆጠረበት ግን ወደ ክቡ መሀል ይገባል:: የአብዛኞቹ ልጆች ስሞች እስኪጠሩ ድረስ ጨዋታውን ቀጥል:: በጨዋታው ጊዜ ለለውጥ ያህል ልጆቹ ቦታ ተለዋውጠው እንዲቀመጡ ልታደርግ ትችላለህ::

59. ከ... በስተቀር ሁላችሁንም እወዳችኋለሁ:: የቡድኑ አባላት በክብ ዙሪያ ተቀምጠው ሳለ (ትርፍ ወንበር አይኖርም) መሪው፣«ከ... በቀር ሁላችሁንም እወዳችኋለሁ» ይላል:: ይህን ሲል ቢያንስ ከክፍሉ ተማሪዎች ሁለት ሰዎችን የሚያመለክት ባሕርይ መጥቀስ አለበት:: (ለምሳሌ፣ ካልሲ ከማያደርጉት ልጆች በቀር፣ ሰማያዊ ልብስ ከሚለብሱ ልጆች በቀር፣ ወዘተ.):: ገለጻው የሚመለከታቸው ልጆች ከመቀመጫቸው ተነሥተው ወደ ባዶ ወንበሮች ይዛወራሉ:: ከክቡ መሀል ያለውም ልጅ የሚቀመጥበትን ባዶ ወንበር ለማግኘት ይጥራል:: ወንበር ያላገኘው ልጅ፣ «ከ... በስተቀር ሁላችሁንም እወዳለሁ» በማለት ጨዋታውን ይቀጥላል:: አጫዋቹ፣ «ሁላችሁንም እወዳችኋለሁ!» በማለት ልጆቹ ወንበር እንዲቀይሩ ማድረግ ይችላል::

60. በትራስ መደባደብ:: ስብሰባው ከመጀመሩ ቀደም ብለህ ሁለት ልጆች ከወለሉ ከፍ ብለህ የሚቆሙበትን ጣውላ አዘጋጅ:: ከእያንዳንዱ ቡድን አንዳንድ ተወዳዳሪ ምረጥ:: በአንድ ጊዜ ሁለት ሰዎች ከጣውላው ላይ እንዲወዳደሩ አድርግ:: ምልክት ስትሰጥ፣ ሁለቱ ተጋጣሚዎች በትራስ መደባደብ ይጀምራሉ:: የጨዋታው ዓላማ አንዱ ልጅ ሌላውን ከጣውላው ወደ መሬት እንዲጥለው ማድረግ ነው:: የየምድቡን አሸናፊ እያጋጠምህ የኋላ ኋላ አንድ አሸናፊ እንዲቀር አድርግ::

61. እግርን ከትራስ ልብስ ውስጥ አድርጎ የመሮጥ ውድድር:: ቡድኖቹን በአንድ መስመር አሰልፋቸው:: ምልክት ስትሰጥ፣ ከእያንዳንዱ ቡድን የመጀመሪያው ልጅ እግሩ ከትራስ ልብስ ውስጥ እንደገባ እየዘለለ ወደ ክፍሉ (ሜዳው) ሌላኛው ጫፍ ይሄዳል:: የመጀመሪያው ልጅ ውድድሩን ሲጨርስ የቡድኑ ተረኛ



የትራስ ልብሱን ተቀብሎ ውድድሩን ይቀጥላል ከሁሉም በፊት ውድድሩን የሚጨርስ ቡድን አሸናፊ ይሆናል::

62. የሰረገላ ውድድር:: ይህ ውድድር በክፍሉ ውስጥ ወይም ከክፍሉ ውጭ ሊካሄድ ይችላል:: ሁለት ልጆች እጆቻቸውን አይይዘው እንዲቆሙና ሦስተኛው ልጅ በሁለቱ ልጆች ላይ እንዲወጣ አድርግ:: ከዚያም ቡድኖቹ የሩጫ ውድድሬ ያካሂዳሉ::

63. እንቁላል በማንኪያ ይዞ የመሄድ ውድድር:: ለእያንዳንዱ ቡድን የተቀቀለ እንቁላልና ማንኪያ አድል:: ቡድኖቹን በአንድ መስመር አሳልፋቸው:: ምልክት በምትሰጥበት ጊዜ፣ ከእያንዳንዱ ቡድን እያንዳንዱ ልጅ እንቁላሉን በማንኪያ ይዞ ወደ ግብ መስመሩ ይደርስና ይመለሳል:: እንቁላሉ ከወደቀበት ልጁ ከእንደገና ይጀምራል:: ከሁሉ አስቀድሞ የጨረሰ ቡድን አሸናፊ ይሆናል:: ለዓይነት ያህል ጥሬ እንቁላል መጠቀም፣ ልጆቹ ከመራመድ ይልቅ በፍጥነት እንዲሄዱ ወይም ዘለል ዘለል እያሉ እንዲጓዙ ልታደርግ ትችላለህ::

64. በቡድን ሰው ተሸክሞ የመሮጥ ውድድር:: እያንዳንዱ ቡድን ከአባሎቹ አንዱን ከራሱ ላይ በማውጣት አሥር ሜትር ያህል ይሮጣል:: (የመጨረሻው ሰፍራ ምልክት ሊደረግበት እንደሚገባ አስታውስ::) የቡድኖቹ አባላት ብዙ ከሆኑ፣ 8 ልጆች አንዱን ልጅ ተሸክመው እንዲሄዱና እንዲመለሱ፣ ከዚያም ቀሪዎቹ የቡድኑ አባላት ተመሳሳይ ተግባር እንዲፈጽሙ አድርግ:: ምልክት እስከተደረገበት ስፍራ ድረስ በቀዳሚነት አሥር ሰዎችን ተሸክሞ ያደረሰ ቡድን አሸናፊ ይሆናል:: ቡድኑ አሥር አባላት ከሌሉት አንዱን ልጅ ከአንድ ጊዜ በላይ ሊሸከም ይችላል::

65. የእግር ኳስን ማስተላለፍ:: የሚያስፈልገው ነገር: ለእያንዳንዱ ቡድን አንዳንድ የእግር ኳስ:: ቡድኖቹን እኩል ቁጥር እንዲኖራቸው አድርገህ በቀጥተኛ መስመር አሰልፋቸው:: በሰልፉ መጀመሪያ ላይ ሳለው ልጅ ኳስ ይሰጠዋል:: ኳሱ የተሰጠው ልጅ በቴስታ ይመልሳል (ትመልሳለች):: ቀጣዩ ልጅ በእግሮቹ መሀል ያሾልካል:: እንዲህ እያሉ ኳሷን በመጀመሪያ ከመጨረሻው ተሰላፊ ዘንድ ያደረሱ ልጆች አሸናፊዎች ይሆናሉ::

ለዓይነት:

ሀ. የተለያዩ መጠኖች ያሏቸውን የተለያዩ የእግር ኳሶች ተጠቀም

ለ. የሌሎች ስፖርቶችን የተለያዩ ኳሶች ተጠቀም::

66. እግርን አስሮ ኳስ መጫወት:: የሚያስፈልጉ ነገሮች: ኳስና እግር ላይ የሚታሰር ጨርቅ:: እያንዳንዱ ልጅ እግሮቹን በጨርቅ ያስርና እግሩን ከመሬት ሳያነሣ እያንሸራተተ ኳስ ይጫወታል::

67. የጭራቅ እርምጃ:: ወጣቶቹ ብዙ ከሆኑ፣ በተለመደው ቡድናችሁ ውስጥ እንዲገቡ ንገራቸው:: ወጣቶቹ ብዙ ካልሆኑ ግን ሁለት

ቡድኖችን አንድ ላይ ልታዋህድ ትችላለህ:: የመነሻና የመድረሻ መስመሮች ከ5-10 ሜትሮች መራራቅ አለባቸው:: የእያንዳንዱ ቡድን አባላት እጆቻቸውን በማያያዝ፣ ክንዶቻቸውን በማጠላለፍ፣ አንዱ ከሌላው ጀርባ ላይ በመሆን ወይም በሌሎች መንገዶች ሊጣመሩ ይችላሉ:: ብቸኛው ገደብ ቡድኖቹ ለጉዞው ሊጠቀሙ የሚችሏቸው የእግሮችና እጆች ብዛት ብቻ ነው:: በጉዞው ሂደት ውስጥ ቡድኖቹ ሊጠቀሙባቸው የሚችሏቸው እግሮችና እጆች በቡድኑ ውስት ካሉት ሰዎች ሁለት ከተቀነሰ በኋላ የሚቀሩትን ይሆናል:: ለምሳሌ፣ በቡድኑ ውስጥ ስድስት ሰዎች ካሉ በአንድ ላይ ተጣምረው የጭራቅ እርምጃ ሊያካሂዱ የሚችሉት አራት እግሮችንና አራት እጆችን በመጠቀም ይሆናል:: በመነሻው መስመር ላይ ቡድኖቹን ካሰባሰብህ በኋላ የማስጀመሪያ ምልክት ስትሰጣቸው ውድድሩ ይጀመራል::

68. ሙዚቃዊ ፊኛዎች:: ወጣቶቹ በክብ ዙሪያ እንዲቆሙ ንገራቸው:: ከአንደኛው በስተቀር ለሁሉም ልጆች ፊኛ ትሰጣቸዋለህ::አንድ ሰው ሙዚቃውን የሚከፍትና የሚዘጋ አንድ ሰው አዘጋጅ:: ሙዚቃው በሚከፈትበት ጊዜ ልጆቹ ፊኛውን ከአንዱ ወደ ሌላው ማስተላለፍ ይጀምራሉ:: ሙዚቃው በሚቆምበት ጊዜ ፊኛ ይዞ ያልተገኘ ልጅ ከጨዋታው ይወጣል:: ሙዚቃው ከቆመ በኋላ ሁልጊዜም አንዳንድ ፊኛ ይቀነሳል::

69. ቁጭ .. ብድግ:: ሁሉም ወጣቶች ተነሥተው እንዲቆሙ አድርግ:: የሚከተለውን ዓረፍተነገር ስታነብና ዓረፍተነገር ለነሱ እውነት ሲሆን ቁጭ ይላሉ:: ሌላ ዓረፍተነገር ስታነብና (ከተቀመጡ በኋላ) እሱም ለነሱ እውነት ከሆነ ተነሥተው ይቆማሉ:: ስለሆነም፣ ዓረፍተነገሮቹ እውነት እንደሆኑላቸው ያህል ሲቀመጡና ሲነሡ ይቆያሉ::

1) ወደዚህ የወጣቶስ ስብሰባ የመጣኸው ግዴታ ስለሆነበህ ነው:: 2) ትምህርት ቤት የምትሄደው በጓደኛህ ግፊት ነው:: 3) ባለፈው ሳምንት በራስህ ፍላጎት ሳይሆን በሌላ ሰው ገፋፊነት አንድ ነገር አድርገሃል:: 4) ዛሬ አንድ ጓደኛህ አንድ የማይፈልገውን ነገር እንዲያደርግ ገፋፍተኸዋል:: 5) በዚህ ወር ውስጥ ሌላ ነገር ለማድረግ ስትል ከቤተክርስቲያን ቀርተሃል:: 6) ዛሬ ከአንድ ብርጭቆ በላይ ቀዝቃዛ ነገር ጠጥተሃል:: 7) ባለፈኸው ሳምንት ባልተናገርሁ ብለህ የተጸጸትህበትን ነገር ተናግረሃል:: 8) ለነገው ትምህርት ቤት የቤት ሥራህ አላጠናቀቅህም:: 9) ትናንት ሌላ ቦታ ለመሄድ ስለቸኮልህ አልጸለህይም::

70. ተጽዕኖ:: ከስብሰባው በፊት ይህን ጨዋታ ለማካሄድ እንደዲያግዙህ አራት ወጣቶች ምረጥ:: ስብሰባው በሚጀመርበት



ጊዜ ከተሰብሳቢዎቹ መካከል አንድ ፈቃደኛ ወጣት ጠይቅና ቀደም ሲል ከመረጥሃቸው አራት ወጣቶች ጋር ወደ ውጭ እንዲወጡ አድርግ:: ቀደም ሲል የመረጥሃቸው አራቱ የጨዋታ ዕቅድህን ያውቃሉ:: አምስተኛው ልጅ ግን አያውቅም:: ከቡድኑ አባላት አንዳንዶቹ ጫማዎቻቸውን (ወይም ሌላ ነገር) አውልቀው ከክፍሉ ፊት ለፊት እንዲከምሩ አድርግ:: የተከመሩትን ጫማዎች ቁጠር:: ወደ ውጭ የሄዱት ልጆች ወደ ክፍሉ እንዲመጡ ጥራቸው:: በፍጥነት የተከመሩትን ጫማዎች እንዲቆጥሩ ጠይቃቸው:: (በ30 ሰከንዶች ውስጥ ጫማዎቹን ቆጥረው እንዲጨርሱና ከዚያ በኋላ ወደ ጫማዎቹ እንዳይመለከቱ ጠይቃቸው::) ከስብሰባው በፊት የመረጥሃቸው አራቱ ልጆች በተገኘው የጫማ ቁጥር ላይ አንድ ቁጥር መደመር እንዳለባቸው ያውቃሉ:: ለምሳሌ፣ የቆጠሯቸው ጫማዎች አሥር ከሆኑ፣ አሥራ አንድ ብለው ይመልሳሉ ማለት ነው:: የዚህ ጨዋታ ዓላማ አምስተኛው ግለሰብ ምን እንደሚል ለማወቅ ነው:: ጫማውን ቆጥሮ አሥር መሆናቸውን ያውቃል:: አሥር ጫማዎች እንዳሉ በመግለጽ ከሌሎቹ የተለየ አቋም ይይዛል ወይስ እንደ ሌሎቹ እሱም አሥራ አንድ ብሎ ይመልሳል? ጨዋታው ለወጣቶች ሌሎች ሰዎች እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩብን ለማሳየት የታቀደ ነው::

71. የሙዝ ውድድር:: ስለ ጨዋታው ማብራሪያ ከመስጠትህ በፊት እያንዳንዱ ቡድን የሚወክለው አንድ ተጨዋች እንዲመርጥ አድርግ:: የተመረጡት ተጨዋቾች ሁሉ ወደተቀሩት ወጣቶች ፊታቸውን አዞረው ከመድረኩ ላይ ከጠረጴዛ ኋላ እንዲቆሙ አድርግ:: ምልክት በምትሰጥበት ጊዜ እጆቻቸውን ወይም ክንዶቻቸውን ሳይጠቀሙ ሙዞቻቸውን በፍጥነት ልጠው መብላት አለባቸው:: ሙዞቹ ተበልተው ሲያልቁ አሸናፊው ማን እንደሆነ ይገለጻል::

72. የፈጠራ ስም መጠቀም:: ሁሉም ወጣቶች በክብ ቅርጽ እንዲቀመጡ አድርግ:: (ብዙ ወጣቶች ካሉ ሁለት ወይም ከዚያ የሚበልጡ ክቦች ሠርተው ሊቀመጡ ይችላሉ::) ይህን ጨዋታ የሚጀምር ሰው ለራሱ አንድ የፈጠራ ስም ይመርጣል:: ለምሳሌ፣ የመጀመሪያው ልጅ ስም ጆርጅ ከሆነ፣ ራሱን «ደጉ ጆርጅ» ብሎ ሊያስተዋውቅ ይችላል:: ከዚያም ሁለተኛይቱ ልጅ ራሷን ካስተዋወቀች በኋላ የመጀመሪያውን ልጅ ስም መናገር አለባት:: «ስሜ ደስተኛይቱ ሐና ይባላል:: እሱ ደጉ ጆርጅ ይባላል::» በክቡ ውስጥ ወደ መጨረሻው ልጅ በምትደርስበት ጊዜ፣ የመጨረሻው ልጅ ራሱንና ከመጀመሪያው ጀምሮ በክቡ ዙሪያ የሚገኙትን ልጆች በሙሉ ያስተዋውቃል::

73. ምሥጢራዊ ስሞች:: ሁለት ወረቀቶች፣ እርሳስና ማያያዣ ለሁሉም ወጣቶች አድል:: ለራሳቸው የምሥጢር ስም እንዲያዘጋጁ ጠይቃቸው:: ማንም ሳያያቸው ይህንን ከአንደኛው ወረቀት ላይ ይጻፉ:: ከዚያም ሁሉም ወጣቶች ወደ ግድግዳው ጥግ በመሄድ ምሥጢራዊ ስሞቻቸውን ከጀርባቸው ላይ ከለጠፉ በኋላ ጀርባቸውን ወደ ግድግዳው አዙረው እንዲቆሙ አድርግ:: ምልክት በምትሰጥበት ጊዜ ሁሉም ወጣቶች በክፍሉ ውስጥ በመዘዋወር ሊያዩ የሚችሏቸውን ምሥጢራዊ ስሞች ሁሉ ይጽፋሉ:: ይህንንም የሚያደርጉት ከጀርባቸው ላይ ያለው የራሳቸው ምሥጢራዊ ስም ለሌሎች እንዳይታይ በመጠንቀቅ ይሆናል:: ሁለት ደቂቃዎችን ያህል ስጣቸውና በዚህ ጊዜ ውስጥ ማን ብዙ ስሞችን ሊጽፍ እንደቻለ እወቅ::

74. የዓይነስውራን ሰልፍ:: ቡድንህን በፍጥነት በሁለት ወይም ከዚያ በሚበልጡ ቡድኖች ከፋፍል:: ይህን ጨዋታ ለማካሄድ በአንድ ቡድን ውስጥ ቢያንስ አራት አባላት ሊኖሩህ ይገባል:: በቡድኖች ከከፋፈልሃቸው በኋላ ወጣቶቹ ዓይኖቻቸውን እንዲጨፍኑ ጠይቃቸው:: «አጮልቆ ማየት አይቻልም!» እያልህ ደጋግመህ ንገራቸው:: ምንም ድምጽ ሳያሰሙ በቁመታቸው ቅደምተከተል (አጫጭሮች ፊት፣ ረዣዥሞች ኋላ) እንዲሰለፉ ንገራቸው! ቡድኖቹ ሰልፋቸውን ያጠናቀቁ ሲመስላቸው «ተሰልፈናል!» እንዲሉ ንገራቸው:: «ተሰልፈናል» ያለው ቡድን አባላት በትክክል በቁመታቸው ልክ ካልገቡ ሌሎቹ ቡድኖች ሰልፋቸውን ማስተካከላቸውን እንዲቀጥሉ ንገራቸው:: ከሌሎች አስቀድሞ *በቁመት ተራ* ለመሰለፍ የቻለ ቡድን የጨዋታው አሸናፊ ይሆናል::

75. ጓደኛውን ያጣ እንስሳ:: የእንስሳት ስም በሁለት የተለያዩ ወረቀቶች ላይ ጻፍ:: ከዚያም በአንድ ወረቀት ላይ «ዳክዬ» የሚል ስም ጻፍ:: ለሁሉም ተማሪዎች የጻፍሃቸውን ወረቀቶች አድል:: ከዳክዬ በስተቀር ሁሉም እንስሳት በሁለት ሁለት ወረቀቶች ላይ መጻፋቸውን አረጋግጥ:: ምልክት በምትሰጥበት ጊዜ ተማሪዎቹ ባገኙት ወረቀት ላይ የተጻፈውን እንስሳ ድምጽ በማሰማት ጓደኞቻቸውን ለማግኘት ይሞክራሉ:: ባገኟቸውም ጊዜ አብረዋቸው ከወለል ላይ ይቀመጣሉ:: «ዳክዬ» የተጻፈበትን ወረቀት ያገኘው ልጅ ግን ጓደኛውን ሳያገኝ በዳክዬ ድምጽ እየጮኸ መፈለጉን ይቀጥላል::

76. ለየት ያሉ ነገሮችን የማድረግ ውድድር:: ሁለት ሰዎች ወጣቶቹን በሁለት ቡድኖች እንዲያከፋፍሉ አድርግ:: ከክፍለጊዜው ቀደም ብሎ መጀመሪያ ሊመረጡ የሚችሉትን ልጆች ወደ መጨረሻ፣ በመጨረሻው ላይ ሊመረጡ የሚችሉትን በቀዳሚነት እንዲመርጡ ፍንጭ ስጣቸው:: እነዚህ ሁለት ቡድኖች ለየት ያሉ ነገሮችን የማካሄድ ውድድሮችን እንዲያከናውኑ አድርግ:: ሁለት ቦርሳዎችን በመውሰድ ለየት ያሉ አስቂኝ ነገሮችን ጽፈህ አስቀምጥባቸው:: *(እነዚህ ለየት ያሉ አስቂኝ ነገሮች ጸጉሩን የተላጨ ሰው ራስ ማከክ፣ በወለል ላይ እግርን አጣምሮ በመቀመጥ መዝሙር መዘመር! ጫማ አውልቆ የቀኙን ለግራ የግራውን ለቀኝ ማድረግ! አራቱንም የክፍሉን ጥጎች (ኮርነሮች) እየዞሩ መንካት፣ ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ::)* አስቂኝ ነገሮችን በወረቀቶች ላይ በመጻፍ በቦርሳዎቹ ውስጥ አኑር:: በሁለቱም ቦርሳዎች አንድ ዓይነት ነገሮች ጽፈህ ማስቀመጥ እንዳለብህ አትርሳ:: «በዚህ ጨዋታ ውስጥ አትሳተፍ:: የሆነ ቦታ ሄደህ ተቀመጥ» የሚል ትእዛዝ የተጻፈባቸውን ሁለት ወረቀቶች በሁለቱም ቦርሳዎች ውስጥ ጨምር:: (አንድ ወረቀት በአንድ ቦርሳ ውስጥ::) ምልክት በምትሰጥበት ጊዜ፣ ከየቡድኑ የመጀመሪያው ልጅ ቦርሳውን ከፍቶ አንድ ወረቀት ይወስድና በወረቀቱ ላይ የተጻፈውን ተግባር ይፈጽማል:: እሱ የተባለውን አከናውኑ ሲጨርስ፣ ቀጣዩ ልጅ ሌላ ወረቀት መዞ በማውጣት በወረቀቱ ላይ የሰፈረውን ትእዛዝ ይፈጽማል:: ጨዋታው እንዲህ እያለ ይቀጥላል:: በቦርሳው ውስጥ የሚገኙ ወረቀቶች የሚሰጧቸውን ትእዛዛት በቀዳሚነት አከናውኖ የሚጨርስ ቡድን የጨዋታው አሸናፊ ይሆናል::

77. ረድፎችን መሙላት:: ዘጠኝ ወንበሮችን (3x3) በሦስት ረድፍ አስቀምጥ:: ተማሪዎችህን በሁለት ቡድኖች ከፋፍል:: እያንዳንዱ ቡድን በየተራ አንድ አባሉን በመላክ ከወንበሮቹ በአንዱ ላይ እንዲቀመጥ ያደርጋል:: (ወንበሮቹ ሀ ወይም ለ የሚል መለያ ቢደረግላቸው ጥሩ ይሆናል::) በአንድ ረድፍ ሦስት አባላቱ ደርሰው የሚቀመጡለት ቡድን የጨቀታው አሸናፊ ይሆናል:: ወንበሮቹን ሀ ወይም ለ ብለህ ካልለየህ ጨዋታው ከምታስበው በላይ አስቸጋሪ ይሆንብሃል:: ጨዋታውን የበለጠ ከባድ ለማድረግ ከፈለግህ፣ ቡድኖቹ የሚንቀሳቀሱበትን ጊዜ ልትወስንና እርስበርሳቸው እንዳይመካከሩ ልትከለክል ትችላለህ::

78. ምን ታውቃለህ? ለስላሳ ኳስ ይዘህ ና:: ተማሪዎቹ በክብ ቅርጽ እንዲቀመጡ አድርግ:: ኳሱን ወደ አንድ ልጅ ወርውርና ዛሬ ስለምታስተምረው ትምህርት የሚያውቀውን እንዲነግርህ ጠይቀው:: ወይም ስለ አንድ ርእሰጉዳይ ጥያቄ አቅርብለት:: ልጁ ስለ ጉዳዩ የሚያውቀውን ከተናገረ በኋላ ኳሱን ወደ ሌላ ልጅ ይወረውራል:: እሱም እንደዚያው ያደርጋል:: መልሶች መደጋገም እስኪጀምሩ ድረስ ይህ ጨዋታ ለአምስት ደቂቃዎች ያህል እንዲቀጥል አድርግ::

79. ፊኛ የማፈንዳት ውድድር:: ለእያንዳንዱ ቡድን አንዳንድ ፊኛ አድል:: የጨዋታው ዓላማ የትኛው ቡድን ፊኛውን መጀመሪያ

እንደሚያፈነዳ መመልከት ነው (ትናንሽ ፊኛዎችን ምረጥ)። አንድ የቡድኑ አባል ፊኛውን አንድ ጊዜ ከነፋው በኋላ ለቀጣዩ ልጅ ያስተላልፋል። ፊኛው ከሰው ወደ ሰው በሚተላፍበት ጊዜ ከውስጡ የነበረው አየር ከቀነሰ፣ ቡድኑ ጨዋታውን እንዲቀጥል አበረታታ። የቡድኑ አባላት በሙሉ ከነፉ በኋላ ፊኛው ካልፈነዳ ከእንደገና ይጀምሩ። የማይፈነዱ ጠንካራ ፊኛዎች ሊያጋጥሙ እንደሚችሉ አትዘንጋ። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ካጋጠመህ ከሁሉም ትልቅ ሆኖ የተነፋ ፊኛ ያለው ቡድን አሸናፊ መሆኑን ተናገር።

80. **ቃላትን የመተወን ጨዋታ።** ወጣቶቹን በትናንሽ ቡድኖች ከፋፍላቸውና ሁሉም ቡድኖች ከአንተ በእኩል ርቀት ላይ እንዲቀመጡ አድርግ። ከዚያም ከየቡድኑ አንዳንድ ሰው ወደ አንተ እንዲመጣ ጋብዝ። ሲመጡም በተግባር (በተውኔት) የሚያሳዩትን ቃል ንገራቸው። ቃሉን ከአንተ ከሰሙ በኋላ ወደ ቡድናቸው ሮጠው በመሄድ ተውኔቱን ይሠራሉ። ቡድኑ ቃሉን በትክክል ከገመተ በኋላ፣ ተውኔቱን የሠራው ልጅ ተመልሶ ወደ አንተ ሲሮጥ ይመጣል። መጀመሪያው አንተ ጋ የደረሰው ልጅ የሚገኝበት ቡድን የዙሩ አሸናፊ ይሆናል።

81. **ኪስን የማስተላለፍ ጨዋታ።** ወንበሮችን በሁለት ረድፍ አድርገህ ደርድር (የሚቀመጡባቸው ሰዎች ፊት ለፊት እንደሚተያዩ አስተውል)። በሁለቱ ረድፎች መካከል የአንድ ሜትር ያህል ርቀት መኖር አለበት። ሁለቱ ቡድኖችህ ፊት ለፊት ተፋጠው እንዲቀመጡ አድርግ። የጨዋታው ዓላማ ቡድኖቹ ኪስ ወደ መጨረሻው የቡድናቸው አባል (ግብ) በፍጥነት ቀድመው ማድረሳቸውን መመልከት ነው። ሁሉም ሰው ክንዶቹን ከወንበሩ ኋላ ማድረግ አለበት። ኪሱን ከመስመሩ መሀል ላይ በመጣል ጨዋታውን ጀምር። ለቅድመጥንቃቄ ተማሪዎቹ ጫማቸውን እንዲያወልቁ ልታደርግ ትችላለህ።

82. **መሪውን ከውድቀት መጠበቅ።** ልጆቹን አራት ወይም አምስት አባላት በሚገኙባቸው ቡድኖች ከፋፍላቸው። እያንዳንዱ ቡድን በክብ መልክ ይቆማል። የየቡድኖቹ መሪዎችም ከክቡ መሀል ይቆማሉ። ከመሀል ያለው ልጅ ዓይኖቹን በመጨፈን ሰውነቱን ሳያጣጥፍ ወደኋላና ፊት እያለ ጊዜያት ለመውደቅ ይሞክራል። ቡድኑ ግን ልጁ እንዳይወድቅ ይዞ ወደ ቦታው ይመልሰዋል።





